“አቅቶኛል መሸከምም ከብዶኛል”

- አባት አቶ ከድር አህመድ የሱፍ



ገጽ 16

የፌደራል ፖሊስን የደንብ ልብስ ለዘረፉ

ገጽ 10

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 035 ጥቅምት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ሦስት ወራት፡-

- የጠላት የሽብር ሴራ ያነገቡ ከ3ሺህ በላይ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል
- ከ36 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል
- አምስት ሺህ የሚጠጉ የአቅመ ደካማ ቤቶች ታድሰዋል

ፍቃዱ ዴሪሳ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለፉት ሦስት ወራት የጠላትን ሴራ ያነገቡ 3ሺህ 303 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን አስታወቀ። አስተዳደሩ ከ36 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሩንና አምስት ሺህ ለሚጠጉ አቅመ ደካማ ዜጎችም የቤት እድሳት ማከናወኑን አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 2ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤው የከተማ አስተዳደሩ የ2015 በጀት አመት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች አፈፃፀምና የቀጣይ ትኩረት ነጥቦች ላይ ተወያይቷል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ለምክር ቤቱ ባቀረቡት የ2015 በጀት ዓመት ሦስት ወራት ሪፖርት የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራ መከናወኑን ጠቅሰው፣ በተለይም ሰላምን፣ አብሮነትንና ወንድማማችነትን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ተግባራት ሲከናወኑ መቆየታቸውን አንስተዋል።

ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማወክ ጠላት ከፍተኛ ዝግጅት ቢያደርግም የከተማዋን መዋቅር፣

በከተማ አስተዳደሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሴ






## የግዥ እቅድ ያላቀረቡ 60 የፌዴራል ተቋማት ጉዳይ ለፓርላማ ሊቀርብ ነው

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ፡- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ጨምሮ ወቅቱን ጠብቀው የግዥ እቅድ ያላቀረቡ 60 የፌዴራል ተቋማት ጉዳያቸውን ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፓርላማ ሊያቀርብ መሆኑን የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አስታወቀ። የተቋማቱ ሥም ዝርዝርም በሚዲያ በኩል ይፋ ሊደረግ እንደሚችልም ተጠቁሟል።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤

የግዥ እቅድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «አንዳንድ ምዕራባውያን ተደራደሩ የሚሉን ለእኛ አስበው ሳይሆን አሸባሪውን ትህነግ ለማዳን ነው»

- አቶ ጌታቸው ተፈራ
የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ከአሸባሪው የትህነግ ቡድን ጋር እንዲደራደር ግፊት እያደረጉ ያሉ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገራትና አማሪካዎች ድርድሩን የሚፈልጉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስበው ሳይሆን አሸባሪውን ትህነግ ለመታደግ መሆኑን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ የተግባር ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ጌታቸው ተፈራ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያን ትርምስና ማሽቆልቆል ለዘመናት ሲመኙና ለችግሩ ድንጋይ አቀባይ ሆነው የኖሩ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገራት አሁን ላይ ድርድር እንዲደረግ ግፊት እያደረጉ ያሉት አሸባሪው ቡድን ያበቃለት መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው።

ከዚህ በፊት ወያኔ ደብረብርሃንና ሰላ ድንጋይ ሲደርስ ያንን ሁሉ የአማራና የአፋርን ሕዝብ ጨፍጭፎና ደፍሮ ሳለ ለምን ተደራደሩ አላሉም? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጦር ሜዳ እስኪዘምቱ ድረስ የትኛውም አካል ተደራደሩ አላሉም። መከላከያ ሰራዊታችን ወያኔን ድባቅ ሲመታው ጠብቀው ተደራደሩ የሚሉት ለምን እንደሆነ ማጤን ተገቢ ነው ብለዋል።



እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ጥንታዊና ምስጢራዊ ሀብት ያላት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ምዕራባውያንም ሆኑ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ያንን ሀብት ለመቀራመት ሲሉ ያልማሱት ጉድጓድ የለም። አንዱ

«አንዳንድ ምዕራባውያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












38 ዓይነት ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ታገዱ

ገጽ 4



# ኬኔት ካውንዳ ለፓን አፍሪካኒዝም ላበረከቱት አስተዋጽኦ ተዘከሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ10ኛው የጣና ፎረም ቅድመ ጉባኤ የቀድሞ የዛምቢያ መሪና ፓን አፍሪካን አቀንቃኝ የነበሩት ኬኔት ካውንዳ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ተዘከረዋል።

የፓን አፍሪካ አቀንቃኙ ኬኔት ካውንዳ የአፍሪካ አገራት ነፃ እንዲወጡ ሲታገሉ እንደነበርምና ከነፃነት በኋላም ዛምቢያን በመምራት በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመትከል የሄዱበት ርቀት እንዲሁም ዕድገት እና ብልፅግናን ለማረጋገጥ በትጋት መሥራታቸው ለአፍሪካውያን ምሳሌ መሆኑ ተገልጿል።

የ10ኛ የጣና ፎረም ቅድመ ጉባኤ ውይይቶች ትናንት ሲካሄዱ የመጀመሪያውን ጽሑፍ ያቀረቡት የታሪክ ምሁሩ ዶክተር ሲሺዋ ሲሺዋ፣ የቀድሞው የዛምቢያ ፕሬዚዳንት ኬኔት ካውንዳ ለፓን አፍሪካኒዝም ባበረከቱት አስተዋፅኦ ሁሌም ሊዘከሩ የሚገባቸው ታላቅ መሪ ነበሩ ብለዋል።

ዛምቢያ በቅኝ ግዛት ውስጥ በወደቀችበት ወቅት በድፍረት ለነፃነት ሲታገሉ እንደነበር እና በዚህም ለእስር ተዳርገው ለአገራቸው መሥዋዕትነት መክፈላቸውን ጽሑፍ አቅራቢው ገልጸዋል።

በወቅቱ ለዛምቢያ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ የአፍሪካ አገራት ነፃ እንዲወጡ ሲታገሉ እንደነበርም ተጠቅሷል።

ከነፃነት በኋላም ዛምቢያን በመምራት በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመትከል እና ዕድገት እና ብልፅግናን ለማረጋገጥ በትጋት መሥራታቸው ተጠቅሷል። ፓን አፍሪካኒስቱ መሪ የሕይወት ተሞክሯቸው ለአፍሪካውያን ምሳሌ ነው ብለዋል።

የኬኔት ካውንዳ የልጅ ልጅ ሙንዳውላ ካውንዳ፣ አያታቸው ካውንዳ መላ ዛምቢያውያንን በእኩል ዐይን የሚያዩ፣ ለአፍሪካ አንድነት መጠናከር የተጉ መሪ እንደነበሩ በመድረኩ ገልጸዋል።

ፓን አፍሪካኒስቱ መሪ የሕይወት ተሞክሯቸው ለአፍሪካውያን ምሳሌ መሆኑም በመድረኩ ተጠቅሷል። ውይይቱን የጣና ፎረም ቦርድ አባል ፕሮፌሰር ፓትሪክ ሎቾ ኦቲዬኖ ሉሙምባ መርተውታል።

የቅድመ ጉባኤ ውይይቶቹ የቀድሞው የዛምቢያ ፕሬዚዳንት ኬኔት ካውንዳ ለፓን አፍሪካኒዝም መጠናከር ባበረከቱት አስተዋፅኦ ላይ በሚመክር የፓናል ውይይት ነው የተካሄደው።

በፓናል ውይይቱ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የኡጋንዳ ምክትል ፕሬዚዳንት ጄሲካ ሮዝ እንዲሁም ሌሎች መሪዎች እና የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

ከ300 በላይ የአገር ውስጥና የውጭ እንግዶች የሚሳተፉበት የዘንድሮው 10ኛው የጣና ፎረም ጉባኤ በባህር ዳር ከተማ በዛሬው ዕለት በይፋ ይከፈታል።

# ታግዶ የቆየው የመታወቂያ እድሳት በጥቅምት ወር መጨረሻ ይጀመራል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ታግዶ የቆየው የመታወቂያ እድሳት በተያዘው ጥቅምት ወር መጨረሻ እንደሚጀመር የከተማ አስተዳደሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጥራቱ በየነ ገለጹ።

በመዲናዋ በመታወቂያ አሰጣጥና እድሳት ዙሪያ የተስተዋሉ ብልሹ አሠራሮችን ዘላቂ እልባት በመስጠት ችግሩን ለመፍታት አገልግሎቱ በጊዜያዊነት እንዲቆም መደረጉ ይታወሳል። የከተማ አስተዳደሩ በብልሹ ተግባሩ ላይ ተሳታፊ የነበሩ አመራሮችና ሠራተኞችን በመለየት ተጠያቂ ማድረጉንም አስታውሰዋል።

አቶ ጥራቱ በጉዳዩ ዙሪያ ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር በተገናኘ ሕገ ወጥ ተግባር ሲፈፅሙ የነበሩ አመራርና ባለሙያዎች ተገኝተዋል ብለዋል።

በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተለይም ችግሩ ጎልቶ በታየባቸው 37 ወረዳዎች በጥብቅ ክትትልና ፍተሻ በሕገ ወጥ ተግባር ላይ ተሳታፊ የነበሩትን መለየት ተችሏል ነው ያሉት።

በዚህም በድምሩ 90 አመራሮችና ባለሙያዎችን ተጠያቂ የማድረግ ተግባር መከናወኑን ዋና ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል።

የክትትልና ቁጥጥር ሥራው አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸው፤ የተጠያቂነት አሠራር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ታግዶ የቆየው የመታወቂያ እድሳት ሕጋዊ አሠራሩን ተከትሎ በተያዘው ጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ እንደሚጀመርም ገልጸዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን የከተማዋ ነዋሪዎች የዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ እንዲሆን አሠራሩን የማዘመን ሥራ ይቀጥላል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት የራሳቸው መለያና ምሥጢራዊነት ያላቸው መታወቂያ ለመስጠት የሚያገለግሉ ወረቀቶች በመታተም ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ በቀጣይ ለነዋሪው የመስጠት ተግባር የሚከናወን መሆኑን አቶ ጥራቱ ተናግረዋል።

የመታወቂያ አሰጣጥን አስመልክቶ የሚፈፀሙ ሕገ ወጥ አሠራሮች ሲስተዋሉ ኅብረተሰቡ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ የድርሻውን እንዲወጣ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።





# ቢክ ኢትዮጵያ የ5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዩሮ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የቢክ ኢትዮጵያ በግብርና ቴክኖሎጂና በግብርና ንግድ ዘርፎች የተሰማሩ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማገዝ የአምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዩሮ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ። ፕሮጀክቱ እንደ አገር ለተያዘው የሥራ ፈጠራ እቅድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታውቋል።

ፕሮጀክቱ ይፋ በሆነበት ወቅት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን እንደገለጹት፤ የቢክ ኢትዮጵያ ድጋፍ በአገራችን በግብርናው ዘርፍ እንደ አገር ለተያዘው የሥራ ፈጠራ እቅድ የሚኖረው ድጋፍ ከፍተኛ ነው።

አቶ ንጉሡ እንዳሉት ፕሮጀክቱ፤ ለአራት አመት የሚቆይ አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዩሮ ፕሮጀክት ይፋ ማድረጉ በሁሉም ዘርፍ የሥራ አጥነትን ቁጥር ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የአውሮፓ ሕብረት ዘርፉን ለመደገፍ ላደረገው ድጋፍም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

እንደ አቶ ንጉሡ ገለጻ፤ በተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ያለው የሥራ አጥነት መጠን ከፍተኛ ነው። ይህን ከፍተኛ የሥራ አጥነት ሁኔታን በተጨባጭ ለመለወጥ እንደ አገር የሥራ ክፍተቶችን በማስተካከል ለሁለት ሚሊዮን አዲስ ገቢዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። ይህ በመንግሥት አቅም ውስንነት የሚሳካ ባለመሆኑ የአጋር፣ የግሉ ዘርፎችና ሌሎች አካላት የነቃ ተሳትፎ ያስፈልጋል።

የቢክ ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ዳይሬክተር ክርስቲያን ቤክ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚውል ከአውሮፓ ሕብረት የተገኘ አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዩሮ ተመድቧል። በግብርና ቴክኖሎጂና በግብርና ንግድ ዘርፎች የተሰማሩ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማገዝ እንዲውል በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በዚህ ፕሮጀክት አራት የተለያዩ ሥራዎች ይሠራል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የአቅም ግንባታ፣ በግብርና ቴክኖሎጂና በግብርና ንግድ ዘርፎች የተሰማሩ የሥራ ፈጣሪዎችን ማቋቋም፣ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግና የግንኙነት መድረኮችን መፍጠር መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከዚህም ባሻገር አስራ አምስት የሥራ ሃሳብ ፈጣሪዎችን ወደ ቢዝነስ እንኪዩቤተሮች፣ ለሰባት መቶ ወጣቶች የሚሆን የመነሻ ካፒታል፣ ለሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አነስተኛና መካከለኛ ሰልጣኞች ስልጠና መስጠትና ለሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰዎች አዲስ የሥራ ዕድል መፍጠር የፕሮጀክቱ አካል መሆኑን ጠቁመዋል።

የቢክ ኢትዮጵያ ቡድን መሪ ኦሊቨር ፔትዞይት በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ በሥራ ፈጠራ ዘርፍ የሚውል ሲሆን፣ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በአውሮፓ ሕብረት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በጋራ በመሆን የሚተገበር ነው ብለዋል።

ይፋ የተደረገው የቢክ ኢትዮጵያ ፕሮጀክት በአውሮፓ ሕብረት ድጋፍ የተገኘ ሲሆን የተመደበው አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዩሮ አቅም የሌላቸውን ሥራ ፈጣሪዎችን የፈጠራ ሥራቸውን እውን በማድረግ የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል ብለዋል።



ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ

# ጉዳት የደረሰባቸው ውሃማ አካላት እንዲያገግሙ የሚያስችሉ አበረታች ሥራዎች ተሠርተዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት ጉዳት የደረሰባቸው ውሃማ አካላት እንዲያገግሙ ለማስቻል የተሠሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በተለይም ቀደም ሲል በእንቦጭና በኬሚካል ጉዳት የደረሰባቸው ሐይቆች ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ለመቀልበስ ማኅበረሰቡን ያሳተፈ ሥራ ሲከናወን ቆይቷል፡፡

በተሠሩ ሥራዎችም ምንም እንኳን አረሞችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባይቻልም በጣና እና ዝዋይ ሐይቆች ላይ ከማኅበረሰቡ ጋር በተደረገ ርብርብ አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን ተናግረዋል፡፡

በጣና ሐይቅ ላይ ይነሳ የነበረው የእንቦጭ ጉዳይ በአካባቢው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በባለቤትነት መንፈስ ከአረም የማላቀቅ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዝዋይ ሐይቅ ላይም የአካባቢውን ባለሀብቶች በማስተባበር አብዛኛውን የውሃውን አካል ከብክለት የማፅዳት እና ከእንቦጭ ነፃ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

መጤ አረሞች እና እምቦጭን የመሳሰሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሐይቆች ላይ የተለያዩ ጉዳቶችን ሲያደርሱ መቆየታቸውን አስታውሰው፣ ጣና ሐይቅ በእምቦጭ ምክንያት ለረጅም ጊዜ ሲጎዳ መቆየቱም የማይዘነጋ ነው ብለዋል፡፡

ጣና ላይ በተደረገው እንቦጭን የመከላከል ርብርብ አካባቢው የእኔ ነው ብሎ የሚሠራ ራሱን የቻለ ተቋም መፍጠር ተችሏል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ አብዛኛው የሚኒስቴሩ ሥራም ይህንን የተፈጠረ ተቋም በሃሳብና በተለያዩ ነገሮች የመደገፍ ሥራ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ ከአቅም በላይ እየሆነ የመጣው የዝዋይ ሐይቅ ጉዳት ደርሶበታል ያሉት ሚኒስትሩ የቆቃና የዓባያ ሐይቆችም በመጤ አረሞች ጉዳት እንደደረሰባቸው ተናግረዋል፡፡

የዝዋይ ሐይቅ ከከተማ አስተዳደሩ እና ከወረዳው እንዲሁም ከአካባቢው በተውጣጡ ማኅበረሰቦች በተሠራ ሥራ ጥሩ የሚባል ውጤት ተገኝቷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህ ዘርፍ የሠሩ ባሀብቶችን ዕውቅና በመስጠት ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሥራዎች እንዲሠሩ መሠረት ተጥሏል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ የ2014 በጀት ዓመት በሌሎች ጉዳት የደረሰባቸው ውሃማ አካላት ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ ትምህርት የተገኘበትና ዝግጅት የተደረገበት ዓመት ነውም ብለዋል፡፡

በዋናነት በትኩረት ሲሠራ የቆየው የውሃማ አካላት ደህንነት ጥበቃ ላይ እንደሆነ የገለፁት ሚኒስትሩ፤ በቀጣይም ውሃማ አካላት ላይ ብክለት እንዳይኖርና ብክለት ሲኖርም ብክለቱ የሚያደርሰው ጉዳት የሚቀንስበትን መንገድ ማመቻቸት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ገልፀዋል፡፡

በተለያዩ ውሃማ አካላት ላይ የተፈጠሩ እምቦጭን የመሳሰሉ አረሞችን በተለይ በሰው ኃይል ለማስወገድ የማይቻልባቸው እንዳሉ ያስታወቁት ሚኒስትሩ፣ ለአብነትም አዞን የመሳሰሉ እንስሳት በውሃማ አካባቢዎቹ መኖር በሰው አማካኝነት ለማፅዳት አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያና የሱዳን የመረጃ ተቋማት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣናን ሰላም ለማረጋገጥ ትብብራቸውን ለማጠናከር ተስማሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት እና የሱዳን ሪፐብሊክ ጄነራል ኢንተለጀንስ ሰርቪስ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣናን ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር የሚያከናውኗቸውን ሥራዎችና ስምሪቶች አጠናክረው ለመቀጠል በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ተገለጸ።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ በሱዳን ሪፐብሊክ ጄነራል ኢንተለጀንስ ሰርቪስ ዳይሬክተር ጄነራል ተቀዳሚ ሌተናል ጄነራል አሕመድ ኢብራሂም ሙፋደል የተመራ የልዑክ ቡድን ትናንት በተቋሙ ጉብኝት አድርጓል። ከጉብኝቱ በኋላ በነበረው መድረክም የሁለቱ አገራት እንዲሁም የቀጣናውን ወቅታዊ የጸጥታና ደኅንነት ጉዳዮች የሚመለከቱ አጀንዳዎች ተነስተው ምክክር ተደርጓል፤ የመፍትሄ አቅጣጫዎችም ተቀምጠዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ በመድረኩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ሱዳን ተመሳሳይ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት እንዲሁም ሰፊ ድንበር የሚጋሩ በመሆናቸው የሁለቱን አገራት ሕዝቦች ግንኙነት በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ አድርጎታል። ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚገኘውን ትሩፋት በጋራ በመቋደስም ትስስሩን ለማጠናከር ይሠራል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ከሱዳን ጄነራል ኢንተለጀንስ ሰርቪስ ጋር መረጃ በመለዋወጥና በአቅም ግንባታ መስኮች የሚያደርገውን ትብብር በማጠናከር ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች እንዲሁም ሕገወጥ የገንዘብ፣ የመሣሪያና የሰዎች ዝውውር የሚያስከትሏቸውን ተፅዕኖዎች ለመቀነስ በትብብር እንደሚሠራ አቶ ተመስገን ገልጸዋል።

በተለይ በቀጣናው ከፍተኛ ሥጋት የሆነውን ሽብርተኝነት ለመከላከል የሚካሄዱ የመረጃ ልውውጦችንና የጋራ ስምሪቶችን በማጠናከር በደም የተሳሰሩትን የሁለቱን አገራት ሕዝቦች ደኅንነት ለማረጋገጥና ተጠቃሚነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የትብብር አድማሶችን ለማስፋት ስምምነት ላይ መደረሱን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ የሱዳን ወሳኝ ስትራቴጂክ አጋር አገር ሆና እንደምትቀጥል መንግሥት በጽኑ እንደሚያምን ያነሱት የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር ጄነራል አቶ ተመስገን፤ በሁለቱ አገራት ብሎም በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በመረጃና በጸጥታ ተቋማቶቻቸው መካከል የሚደረገውን ትብብር እና አጋርነት በማጠናከርም የጋራ የደኅንነት ሥጋቶችን ለማስወገድ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

የሱዳን ሪፐብሊክ ጄነራል ኢንተለጀንስ ሰርቪስ ዳይሬክተር ጄነራል ተቀዳሚ ሌተናል ጄነራል አሕመድ ኢብራሂም ሙፋደል በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ የመረጃና ደኅንነት ተቋም ያደረጉት ጉብኝት በሪፎርሙ ሂደት ስኬታማ ተግባራት መከናወናቸውን ግንዛቤ እንደፈጠረላቸው አመልክተዋል።

ኢትዮጵያና ሱዳን በርካታ የሚጋሯቸው ጉዳዮች በመኖራቸው የሁለቱ አገራት የመረጃ ተቋማት የጋራ የደኅንነት ሥጋቶችን ለማስወገድ በትብብር መሥራታቸውን እንደሚያጠናክሩ የጠቆሙት ተቀዳሚ ሌተናል ጄነራል አሕመድ ኢብራሂም፤ በተለይ ቀጣናዊና ዓለምአቀፋዊም ሥጋት የሆነው ሽብርተኝነትን ለመከላከል የሚደረጉ የአጋርነት ሥራዎች እና ኦፕሬሽኖች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመልክተዋል። የመረጃ ልውውጥም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ስምምነት ላይ መደረሱን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያና ሱዳን የሚዋሰኑበት ድንበር ረጅም በመሆኑ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን ጨምሮ የተለያዩ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን መከላከል እንደሚገባ በምክክሩ መነሳቱን የጠቆሙት ተቀዳሚ ሌተናልጄነራል አሕመድ ኢብራሂም፤ የወሰን አካባቢዎችን ሰላም በማረጋገጥ የሁለቱን አገራት ሕዝቦች ተጠቃሚነት ለማሳደግና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በማጠናከር የሚገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ መግባባት ላይ መደረሱን አመልክተዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት እና የሱዳን ሪፐብሊክ አቻው ጄነራል ኢንተለጀንስ ሰርቪስ በቀጣይም ቋሚ የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ትብብራቸውንና አጋርነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ የላከልን መረጃ ያመለክታል።

# የአርብቶአደር አካባቢዎችን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ለተሻለ ኢኮኖሚ መጠቀም ይገባል

**አዲሱ ገረመው**



ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ



አዲስ አበባ፡- የአርብቶአደሩ አካባቢዎችን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ በማዋል ለተሻለ ኢኮኖሚ መጠቀም እንደሚገባ ተገለጸ። የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ልማት ፎረም መመስረቻ ጉባኤ ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ከመስኖና ቆላማ አካባቢዎች እንዲሁም ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ልማት ፎረም መመስረቻ ጉባኤን አካሂዷል። የፎረሙ ዓላማ የአርብቶ አደሩን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል ለአገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችል እንደሆነ ተመላክቷል።

በጉባኤው ላይም የአርብቶ አደሩን አካባቢዎች እምቅ የተፈጥሮ ሀብት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ በማዋል ኅብረተሰብንና  አገርን በተሻለ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ ተጠቅሷል።

የግብርና ሚኒስትር አቶ ኡመር ሁሴን፤ ለሰብል ልማት የተሰጠውን ያክል ትኩረት ለእንስሳት ሀብት ልማት ባለመስጠት ጥቅም ሳይገኝ መቆየቱን አንስተዋል። የእንስሳት ሀብትን በሚገባ ለማልማትና ጥቅም ላይ ለማዋል በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ የአርብቶአደሩ አካባቢዎችን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ በማዋል ለተሻለ ኢኮኖሚ መጠቀም ይገባል ብለዋል።

ሚኒስትሩ፤ ዓለም አሁን ከገባችበት የአየር ንብረት ለውጥ፣ የኮቪድ ወረርሽኝና የተለያዩ ግጭቶች ምክንያት የዓለም አገራት ኢኮኖሚ ተዛብቷል በማለት፤ ይህ ሁኔታ በተለይ ምርትን ከውጭ በማስገባት ዜጎቻቸውን ከረሀብ እየታደጉ ባሉ የአፍሪካ አገራት ላይ ችግሩ ይበልጥ እየተባባሰ እንዳለ አመላክተዋል። ኢትዮጵያ ካለባት የምግብ አቅርቦት ችግርና ተጽእኖ ሕዝቦቿን ለመታደግ ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት በመስጠት  እየሠራች እንደሆነ ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በግብርናው ዘርፍ ላይ አገራዊ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ያሉትን ሀብቶች በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል የመዋቅር ማሻሻያዎች ሥራ ላይ እየዋሉ ይገኛሉ።  ክልሎች ያላቸውን የተሻለ አቅም ለይተው ሥራ ላይ ማዋል እንዲችሉ እየተሠራ ነው።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ እንስሳት ሀብት ዘርፍ ለጠቅላላ አገራዊ ኢኮኖሚ ከ17 በመቶ በላይ ድርሻ የሚያበረክት ቢሆንም፤ ከእንስሳት አያያዝና አረባብ ሥርዓት አንጻር ግን ምርታማነቷ ዝቅተኛ ነው። በዚህም አገራዊ የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ነፍስ ወከፍ ፍጆታ አነስተኛ ሆኗል። በመሆኑም የእንስሳት ሀብት ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል። ለዚህም የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ፎረም መሠረት የሚጥል ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽነር ወይዘሮ ፍሬአለም ሽባባው፤ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን በሲስተም፣ በእውቀትና በመሠረተ ልማት አደራጅቶ በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ማከናወን አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል።

ፎረሙ፤ ለአገር የሚጠቅም የኢኮኖሚ አጀንዳ ለመቅረጽ፣ እንዲሁም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተጐጂ የሆኑ አርብቶ አደሮች አካባቢዎችን ወደ ተሻሻለ ኢኮኖሚ ለማሻገር ያስችላል ብለዋል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሀመድ በበኩላቸው፣ አርብቶአደርነት አዋጭ የኑሮ ዘይቤ በመሆኑ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶችን በተቀናጀ አሠራር ለመምራት ፎረሙ አስቻይ እንደሆነ ተናግረዋል።

# በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠረ የሳይበር ጥቃት በስምንት እጥፍ ጨምሯል

- በሦስት ወራት ከ1 ሺህ 600 በላይ የሳይበር ጥቃቶች ተፈጽመዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች ከ2012 ዓ.ም ከተደረጉ የሳይበር ጥቃቶች ጋር ሲነፃፀሩ የስምንት እጥፍ ጭማሪ ማሳየታቸውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ገለፀ፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን ሶካ እንደገለፁት፤ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች ላይ ያነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች በእጅጉ ጨምረዋል፡፡ ይህም በንፅፅር ሲታይ በ2014 ዓ.ም የተሞከሩ የሳይበር ጥቃቶች ከ2012 ዓ.ም የሳይበር ጥቃቶች ጋር ሲነፃፀር በስምንት እጥፍ ከ2013 ዓ.ም የሳይብር ጥቃት ደግሞ በሦስት እጥፍ ከፍ ብሏል፡፡

እንደ አቶ ሰሎሞን ገለፃ፤ በሦስት ዓመታት ውስጥ በተለይ ከሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ጦርነት ጋር በተያያዘ በሚመስል ሁኔታ በአገሪቱ የሳይበር ጥቃት ሙከራ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ በ2012 ዓ.ም አጠቃላይ የተሞከረው የሳይበር ጥቃት 1 ሺህ 80 ሲሆን ይህ ቁጥር በ2013 ዓ.ም ወደ 2 ሺህ 800 ከፍ ብሏል። የ2014 ዓ.ም አጠቃላይ የሳይበር ጥቃት ሙከራ ደግሞ 8 ሺህ 900 ደርሷል፡፡

የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተቃጡ የሳይበር ጥቃቶች ቁጥር 1 ሺህ 613 መድረሳቸውንም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። የተደረጉ ጥቃቶችም አብዛኞቹ ያነጣጠሩት በፋይናንስ ተቋማት ላይ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

የሳይበር ጥቃቶችን 97 በመቶ ያህል መከላከል መቻሉን ያነሱት አቶ ሰሎሞን፤ ሆኖም በ2014 ዓ.ም የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ በተሰነዘሩ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በቢሊዮን የሚቆጠር ኪሳራን ማስቀረት ቢቻልም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮችን አገሪቱ እንዳጣችም አክለው ገልጸዋል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሳይበር ጥቃት ማደግ ምክንያት ከሆኑት መካከል የሰው



**አቶ ሶሎሞን ሶካ**

ልጆች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ሆኖ እንደሚገኝ የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህን በመረዳትም አስተዳደሩ የአገርን የሳይበር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የአገሪቱን ቴክኖሎጂ ባለቤትነት ለማረጋገጥ ሰፊ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ማሳደግና የኢትዮጵያን የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ማረጋገጥ አገሪቱ ወደ ዲጂታላይዜሽን ለምታደርገው ጉዞ አስፈላጊ መሆኑንም አስገንዝበዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ፣ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ወደ ዲጂታላይዜሽን የምታደርገው ሽግግር ለአገሪቱ ሁሉን አቀፍ ልማት የሚኖረው ሚና የሚያጠያይቅ ባይሆንም የዲጂታል ሽግግሩን የሚመጥን የሳይበር ደህንነት ሥራዎች መሥራት ካልተቻለ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ብለዋል፡፡

ለዚህም እንደ ማሳያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሳይበር ምህዳሩን የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር መጨመርን ተከትሎ በግለሰቦች እና ተቋማት ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶች ያደረሱትን ኪሳራ ማንሳት በቂ እንደሆነም አቶ ሰሎሞን ጠቁመዋል።

# 38 ዓይነት ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ታገዱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- 38 ዓይነት ምርቶች ኤል ሲ ተከፍቶላቸው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በጊዜያዊነት ታገዱ። ምርቶቹ የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ጉምሩክ ኮሚሽን በጥናት ለይቶ ይፋ ያደረጋቸው ናቸው ተብሏል።

በምርቶቹ ላይ እገዳ የተጣለው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሆነው ስላልተገኙና የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ገቢ ዕቃዎች በቂ የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ በማሰብ መሆኑን ተመልክቷል። ምርቶቹ ለሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት እንደሆኑም ብሔራዊ ባንክ ገልጿል፡፡

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዢና ዋና ኢኮኖሚስት ፈቃዱ ድጋፌ እንደገለጹት፤ እገዳው ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ነው።

እገዳ የተጣለባቸው መጠጦች (ውስኪ ወይም ቢራ እና ሌሎች አልኮል መጠጦች)፣ ማስቲካ፣ ቸኮሌት፣ ውሃ፣ ሲጋራ፣ ሰው ሰራሽ ማጌጫዎችና መሰል ቁሳቁስ መሆናቸው ተጠቁሟል። በግለሰቦች ኤል ሲ ተከፍቶባቸው የሚገቡ መኪናዎችንም እገዳው ይመለከታል ነው የተባለው።

ለባንኮች አዲስ ኤል ሲ እንዳይከፍቱ ደብዳቤ እየተሰራጨ እንደሆነ ምክትል ዋና ገዢው ተናግረዋል። ባንኮች ከጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እንዲተገብሩም መመሪያ ተላልፏል፡፡

ጦርነቱና የውጭ ጫናዎች የሚፈጥሩትን አሉታዊ የኢኮኖሚ ተጽእኖ ለመቋቋም ለተወሰኑ ዓመታት ከውጭ የሚገቡ የቅንጦት ዕቃዎችና መኪናዎች ማቆም እንደሚገባ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ከዚህ ቀደም መክረዋል፡፡



ዋጋቸው እጅግ ውድ የሆኑ መጠጦች፤ ምግቦች፣ የመዋቢያ ዕቃዎችና ቅንጡ መኪናዎች ከውጭ እንዳይገቡ መከልከል አለባቸው ሲሉ የቆዩት የኢኮኖሚ ምሁራን፤ ለእነዚህ ምርቶች ሊወጣ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ ማዳን ቀላል እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

ምሁራኑም በተለይ የግብርናውን ምርታማነት በማሳደግና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች መተካት ላይ አተኩሮ መሥራት እንደሚኖርበት ጠቁመው፤ ሰፋፊ መስኖ ልማት ሥራዎች በማካሄድም ከውጭ የሚገቡ እንደ ስንዴና ፍራፍሬ ያሉ የግብርና ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት መሸፈን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

# «አንዳንድ ምዕራባውያን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ብሔር ከሌላው ብሔር ጋር በሰበብ ባስባቡ እርስበርስ እንዲጋጩ በማድረግም አገሪቱ ያላትን ሀብት ተጠቅማ እንዳታድግ አድርገዋል። በዚህ ረገድ አሸባሪው ቡድንም አገሪቱን ሲበዘብዝ መኖሩ አልበቃ ብሎ ለውጭ ጠላት አሳልፎ የሚሰጡ ተግባራትን ፈፅሟል።

‹‹ከዚህ በኋላ የውጭ ኃይሎች በእኛ ላይ ሊጫወቱብንና እንዳሻቸው ሊዘውሩን አይገባም›› ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ በተለይም ከአሸባሪው ቡድን ጋር ተያይዞ ያላቸውን ወደአንድ ጎን ያደላ አስተሳሰብ እስካልቀየሩ ድረስ ተደራደሩ ስላሉ ብቻ መቀበሉ አደጋው የከፋ መሆኑን ስጋታቸውን አስቀምጠዋል። ይልቁንም አገርን ለመበተን የሚሠራውን ይህንን ፅንፈኛ ቡድን እስከወዲያኛው ለማጥፋትም በህብረት መታገሉ ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል።

‹‹በእርግጥ እርቅ ጥሩ ነው፤ በበኩሌ ግን ከወያኔ ጋር እርቅ ይኖራል ብዬ አልገምትም፤ እርቅ የሚኖረው እኮ የሚቀበል አካል ሲኖር ነው። በዚህ ረገድ ወያኔዎች ጭንቅላታቸው ለፍቅርም ሆነ ለእርቅ የተዘጋ ነው። መቀበልም፤ መስጠትም አይችሉም›› ብለዋል።

እነዚህ ሰዎች ምን ያህል የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እንዳወደሙ መገንዘብ ይገባል ያሉት አቶ ጌታቸው፤ ለአመታት የፈፀሙት በደል እያለ ሕዝቡ ምህረት ቢያደርግላቸውም በደሃ ሕዝብ መዋጮ የተገዛውን የጦር መሣሪያ በመጠቀም ኢትዮጵያን ወግተው ዛሬ በ10 እና 20 ዓመታት ሊገነቡ የማይችሉ ትምህርት ቤቶችን እና የሃይማኖት ተቋማትን አፍርሰው መሄዳቸው ሊዘነጋ እንደማይገባም አሳስበዋል።

አቶ ጌታቸው እንዳሉት ‹‹በአሸባሪው ቡድን ምክንያት ለሞቱት ንፁሃን፤ በትግራይ ላለቀው ያ ሁሉ ወጣት ተጠያቂው ወያኔ ነው፤›› በአንድ በኩል በሰብአዊ መብት ተቋሞቻቸው ያለአግባብ ኢትዮጵያን እየከሰሱ በሌላ በኩል ሰላም ፍጠሩ እያሉ የሚወተውቱ አካላት ከምን ተነስተው እንደሆነ በአግባቡ መመርመር እንደሚገባ አሳስበዋል።

# በከተማ አስተዳደሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሕዝቡን፣ የፀጥታ ኃይሉንና የተለያዩ አደረጃጀቶችን በማቀናጀትና በመምራት የጠላትን ሴራ ማክሸፍ ችለናል ብለዋል። በተለይም በከተማዋ የተከበሩ የአደባባይ በዓላት ስጋቶቻችን ሳይሆኑ ፀጋዎቻችን መሆናቸውን ያየንበት ነው ብለዋል።

በዚህም 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ አካባቢውን እንዲጠብቅ በማድረግ የሰላም ሰራዊቱ፣ የደንብ ማስከበር፣ የፖሊስ ኃይልን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር የከተማዋን ሰላምና ጸጥታ ማስፈን እንደተቻለ ተናግረዋል። በተሠራው ቅንጅታዊ ሥራም የጠላትን የሽብር ሴራ ያነገቡ 3ሺህ 303 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል። ይህም ዘላቂ ሰላምና አብሮነት ለማጠናከር ከሕዝብ ጋር መሥራት አስፈላጊ መሆኑንም ያየንበት ተግባር ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ እና አጎራባች የኦሮሚያ ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን አስተዳደር ወሰን ሕገ-መንግሥቱንና የኦሮሚያ ክልል እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ በጋራ በተቋቋሙ ኮሚቴዎች እና በፌዴራል መንግሥት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እልባት በመስጠት ታሪካዊና ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደተቻለም አንስተዋል።

በሌላ በኩል ለከተማዋ ወጣቶች አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ከ36 ሺህ በላይ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል ብለዋል።

የከተማዋ ማህበረሰብ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን እንደ ባህል እየወሰደ ባለው በዚህ ወቅት በባለፉት የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ ከ284 ሺህ ለሚሆኑ አቅመ ደካሞች ድጋፍ ማድረግ መቻሉም ተገልጿል።

በዚህም ከ1.7 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት በማሰባሰብ 4628 ቤቶችን በማደስ ከ23 ሺህ በላይ አቅመ ደካማ ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

በሩብ ዓመቱ የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራምና ዩኒፎርም ተጠቃሚነት ሽፋኑን ወደ 708 በላይ በማሳደግ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በማድረግ በራስ አቅም የመጽሐፍት ዝግጅት ተጠናቆ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትንም በማሳደግ 94 በመቶ ሰልጣኞችን በመቀበል ስልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ በሪፖርቱ ተመላክቷል።

ከመንገድ መሠረተ ልማት አፈፃፀም አንፃር በ2015 የመጀመሪያው ሩብ አመት ውስጥ 20.12 ኪ.ሜትር የግንባታና 195.96 የጥገና ሥራዎች ማከናወን መቻሉን ተናግረዋል። ከአዲስ የመንገድ ግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ በበጀት አመቱ በ3 ቢሊዮን ብር በጀት 3 ግዙፍ የመንገድ ልማት ሥራ ለማከናወን አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንደተከናወነ ለምክር ቤት አባላት ቀርቧል።

በ2015 የበጀት ዓመት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ የሚገኘው የሜጋ ፕሮጀክቶች ሲሆን በዚህም ነባር ፕሮጀክቶችን በክረምቱ ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን፣ በአዲስ ሜጋ ፕሮጀክቶች አኳያ የከተማው የሴክቶራል ቢሮ ግንባታ፣ የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የሴቶች ተሃድሶ ማቋቋም ግንባታ ማዕከል፣ የሦስቱ ግብርና ምርቶች ገበያ ማዕከላት፣ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የገበያ ማዕከላት ግንባታ እና ሌሎችም ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር በቂ ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት የ40/60 እና 20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ዕጣ በማውጣት ሂደት ያጋጠመውን ችግር በመቅረፍ ለባለ ዕድሎች ዕጣ የማውጣት ሂደት በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

ምክር ቤቱ በትናንቱ ውሎው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ያቀረቧቸውን የተለያዩ ሹመቶች ያፀደቀ ሲሆን፣ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የነበሩትንና የከተማው ምክር ቤት አባል የሆኑትን የወ/ሮ ሀቢባ ዑመርን ያለመከሰስ መብትም አንስቷል።

# የግዥ እቅድ ያሳቀረቡ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ተቋማት የግዥ እቅዳቸውን ማቅረብ ያለባቸው በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ቢሆንም የበጀት ዓመቱ ሩብ ዓመት ተጠናቆም ማቅረብ አልቻሉም ብለዋል። ከእነዚህ የፌዴራል ተቋማት መካከል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እንደሚገኙበት ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት 169 ከሚሆኑ የፌዴራል ተቋማት ውስጥ 60 የሚሆኑት የፌዴራል ተቋማት የግዥ እቅድ አላቀረቡም። አሁን የበጀት ዓመቱን ሩብ ዓመት አጠናቀናል። ሕጉ የሚለው ደግሞ ቀድማችሁ እስከ ሐምሌ 30 አሳውቁ ይላል ሲሉም ተናግረዋል።

የሕዝብ እንደራሴዎች የአገሪቱን በጀት ካፀደቀ በኋላ ተቋማት እቅዳቸውን ከልሰው ይልካሉ። ልክ ይህ በጀት እንደተፈቀደ ተቋማት የግዥ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው ያሉት አቶ ሐጂ፤ ነገር ግን ብዙ ተቋማት ብድግ ብለው የግዥ እቅድ ያቀርባሉ። ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብለው በመጨረሻ አካባቢ ከፍተኛ ግዥ የሚያቀርብበት ምክንያትም አንዱ በዚህ የተነሳ ነው። በዚህ ወቅት ደግሞ ወደ ጨረታ አይሄድም፤ ወደ ልዩ የግዥ ፈቃድና ውስን ጨረታ፣ ለአንዱ ቀጥታ መስጠት ወደሚለው ይሄዳል። አልፎ አልፎ የተወሰኑ ተቋማት ደግሞ እቅዳቸው እና ሥራቸው ተናበ የሚሄዱ አሉ። በርካታ ተቋማት ግዥ የሚያካሂዱት፣ ስልጠና የሚሰጡት በዓመቱ መጨረሻ ነው። ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው ሲሉም ጠይቀዋል።

«አንዳንድ ተቋማትም ስልጠና የሚሰጡት ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብለው ግንቦት ላይ ነው። ይህ ዓላማ ቢስ፣ የባከነ፣ የሌብነትና ገንዘብ እንዳይተርፍ የሚሰጥ ስልጠና ነው። ማሰልጠን ካለብንና መጠናቀቅ ያለባቸው በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ወቅት መሆን አለበት» ብለዋል።

«እኛ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ስልጠና እንሰጣለን። በሁለተኛው ሩብ ዓመት የሰጠነው ስልጠና ውጤት ማምጣት መቻሉን ወጥተን ግምገማ እናደርጋለን። ሙስና መቀነስ አለመቀነሱን፣ የግዥ እቅድ መኖር አለመኖሩን እናያለን። እኛ ዘንድ የግዥ እቅድ የሌለው አካል አይስተናገድም። የገንዘብ ሚኒስቴር በጀታቸውን ሊለቅ ይችላል። አሁን ግን ደብዳቤ አዘጋጅተን እያሰራጨን ነው። ለፓርላማ፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር የግዥ እቅድ የሌላቸው ስለሆነ በጀታቸውን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ተቋማት ብለን እናሳውቃለን» ብለዋል።

የቀዳሚ መጽሄት

# አገልግል

## ‹‹ አሸባሪው ትሕነግ ጭንቅላቱ ለፍቅርም ሆነ ለእርቅ የተዘጋ ነው››

- አቶ ጌታቸው ተፈራ
የኢትዮጵያ የዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ

ገጽ 6






## ብርሃን በማዳረስ እየተጋች ያለችው ወጣት

ገጽ 13



## “አቅቶኛል መሸከምም ከብዶኛል”

- አባት አቶ ከድር አህመድ የሱፍ

ገጽ 16

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

## ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የኮርፖሬሽኑ የ1ኛ ሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርትና ግምገማ በወፍ በረር ሲቃኝ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በከተማዋ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ገደማ የተለያዩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞችን በመንደፍ ቤቶቹን ለቤት ዕድለኞች ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም ኮርፖሬሽኑ ለመምህራን የተሰጠውን አምስት ሺ ቤቶችን ጨምሮ በ20/80 ፣ በ10/90 እና በ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ-ግብር እስካሁን በጥቅሉ ከ256 ሺ 251 ቤቶች በላይ ሠርቶ በማጠናቀቅ ለባለ ዕድለኞቹ በማስረከብ ከአንድ ሚሊዮን 281 ሺ በላይ እማወራዎችን እና አባወራዎችን የቤት ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል።

ከዚህ ባሻገር ኮርፖሬሽኑ በ20/80 የቤቶች ልማት ፕሮግራም 100 ሺ 769 ቤቶች (የፓኬጅ 2A – 26 ሺ 613፣ የፓኬጅ 2B – 26 ሺ 203 እና የፓኬጅ 3 – 47 ሺ 952)፣ በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም 38 ሺ 240 ቤቶች (የፓኬጅ 2 – 17 ሺ 737 እና የፓኬጅ 3 – 20 ሺ 503) በድምሩ 139 ሺ 8 ቤቶችን በነባር ግንባታ እያከናወነ ይገኛል። እንዲሁም በ2012 በጀት ዓመት የተጀመሩ አራት ሺ 287 ቤቶች (በ20/80 የቤቶች ልማት ፕሮግራም – 826፣ በ40/60 የቤቶች ልማት ፕሮግራም ሦስት ሺ 21 እና በኪራይ 440 ቤቶች) በጠቅላላው 143 ሺ 295 ቤቶች ግንባታን በነባርና በአዲስ የቤት ልማት ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ኮርፖሬሽኑም እነዚህን በግንባታ ላይ የሚገኙ ቤቶችን አጠናቆ ለቤት ዕድለኞች ለማስረከብ እየተጓዘበት ያለው መንገድ ምን እንደሚመስል ከሰሞኑ የ1ኛ ሩብ አመት የአፈፃፀም ሪፖርትና ግምገማ አካሂዷል። የኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች እና የቡድን መሪዎች



**አቶ ሽመልስ ታምራት፤**

በተገኙበት የተቋሙ የ1ኛ ሩብ አመት የአፈፃፀም ሪፖርትና ግምገማ በቀረበበት ወቅት የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል። እርሳቸው እንዳሉትም፤ በአሁኑ ወቅት የሀገር መከላከያና ጥምር ጦሩ ውድ ሕይወቱን መስዋእት አድርጎ የሀገሩን ዳርድንበር ለማስከበር ጥረት እያደረገ ይገኛል። ሰላማዊ ቀጣና ውስጥ ሆነን የመንግሥት ሥራ የምንሠራ አካላቶች መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ቀልጣፋ አገልግሎት በአስተዳደር ዘርፉ በመስጠት በሌላ በኩል ደግሞ የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊው ተመዝግቦ ረጅም ጊዜ እየጠበቀ በመሆኑ እየተከናወኑ ያሉ ግንባታዎችን በማፋጠን ጥያቄውን ልንፈታለት ይገባል ብለዋል።

በመድረኩ የቅርንጫፍ አንድ እና ስድስት ጽሕፈት ቤቶች ዋና ዳይሬክተሮች በሞዴልነት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈፃፀማቸውን ያቀረቡ ሲሆን፤ እንደ ቅርንጫፍ በ1ኛ ሩብ ዓመት ያጋጠሙ አበይት ችግሮች የግብአት አቅርቦት፣ የኮንትራክተር አቅም ማነስ፣ አልፎ አልፎ በቡድን እና በጦር መሣሪያም ጭምር በመታገዝ ስርቆት ለመፈፀም ሙከራ ማጋጠሙ ተገልጿል። በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ ደረጃ ለችግሮቹ እልባት ለመስጠት የተወሰዱ እርምጃዎችን በዋና ዳይሬክተሮች የተገለፁ ሲሆን፤ ከአቅም በላይ የሆኑትን በማዕከል ደረጃ እንዲፈቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቃቸውንም ነው አመራሮቹ የተናገሩት።

በመድረኩም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የማዕከል ሥራ አፈፃፀምን በሚመለከት በኮርፖሬሽኑ የእቅድና በጀት ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ደንቦባ በዝርዝር አቅርበዋል። እርሳቸው እንደገለፁት፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የገጠሙ ችግሮች ብለው ያቀረቡት ከቅርንጫፎች ሪፖርት በወቅቱ ያለመድረስና ወጥ የሆነ የሪፖርት አላላክ ሥርዓት አለመኖር፣ መረጃዎችን በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፎ ያለመላክ እንዲሁም የቁጥር መፋለስ፣ መርህን የጠበቀ አሠራር ያለመከተል በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የሚታዩ ችግሮች እንደሆኑ አመላክተዋል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት በሪፖርቶቹ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ ከማዕከል እስከ ቅርንጫፍ መርህን የጠበቀ እና የተከተለ ወጥ አሠራር መከተል እንደሚገባና በእያንዳንዱ ዘርፍ ችግሮችን በመለየት በራስ አቅም መፍታት የሚቻለውን በመፍታት፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ለሚመለከታቸው የማዕከል አመራሮች በማሳወቅ ችግሮቹን እየፈቱ መሄድ እንደሚገባና ለነገ ተብሎ የሚተው ችግር ሊኖር እንደማይገባ አፅንኦት ሰጥተው አሳስበዋል።

በአስሩም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በቂ አመራር እና ባለሙያ የተመደበ ከመሆኑ አንፃር ለችግሮች መፍትሔ በመስጠት የግንባታ ሥራውን በማፋጠን ገንዘባቸውን ለረጅም ጊዜ እየቆጠቡ የቤት ዕድለኛ ለመሆን በጉጉት ለሚጠባበቁ በርካቶች ወገኖች ቤቶችን በማጠናቀቅ ልናስረክብ እንደሚገባ ዋና ዳይሬክተሩ ይጠቅሳሉ።

በውይይቱ ላይ የመልካም አስተዳደርና ብልሹ አሠራር የ1ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀምን የኮርፖሬሽኑ የሥነምግባርና ፀረ ሙስና መኮንን አቶ ሙላቱ ሰይፉ ባቀረቡት ሪፖርት፤ ከመልካም አስተዳደር አንፃር መሻሻሎች ቢኖሩም አንዳንድ የአገልግሎት ዘርፎች ላይ አሁንም እንግልትና ምልልስ እንደሚታይ ጠቅሰዋል። ከብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ የቡድን ስርቆቶች በአንዳንድ ቅርንጫፎች መስተዋላቸውንና የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ ጠንካራ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባ አመላክተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከክፍያ ጋር በተያያዘ ተቋራጮች የሚያነሷቸውን ችግሮች በአግባቡ ፈትሾ መፍትሄ እየሰጡ መሄድ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። በመድረኩ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ሰፊ ውይይቶች የተደረገ ሲሆን ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎችም በአመራሩ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹አሸባሪው ትሕነግ ጭንቅላቱ ለፍቅርም ሆነ ለእርቅ የተዘጋ ነው››

- አቶ ጌታቸው ተፈራ
የኢትዮጵያ የዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ

ማህሌት አብዱል

የዛሬው ‹‹የዘመን እንግዳችን›› በቀድሞው መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በመድፈኝነትና በስለላ ሥራ አኩሪ ተግባር የፈፀሙ ሰው ናቸው ።ካለፉት 30 ዓመታት ወዲህ ደግሞ ትሕነግን በመታገል ረገድ ከፍተኛ ሥራ በመሥራት ይታወቃሉ ።እንግዳችን የተወለዱት በቀድሞው አጠራር ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ቴፒ ከተማ ውስጥ ነው ።የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቴፒ አንደኛና መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም በነቀምት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በቀጥታ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በመግባት በውርሶ መኮንኖች ማሰልጠኛ ሰልጥነው የመቶ አለቃነት ማዕረግ አግኝተዋል።

አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በመካናይዝድ ብርጌድ ውስጥ በመድፈኝነትና በቅየሳ ወታደራዊ ሞያ በመድፈኝነት ከ46 ባላነሱ ግንባሮች ተሰልፈው የሃገራቸውን ዳር ድንበር በማስጠበቅ ወሳኝ ሚና መጫወታቸውን የሚናገሩት እኚሁ ሰው በተለይም በጅግጅጋ፣ ቶጎጫሌና ቀብሪደሐር ተሰልፈው ሃገር ሲወር የመጣውን ጠላት ድባቅ መምታቸውን ይጠቀሳሉ። እንዲሁም በራሺያና ኩባ ኤክስፖርቶች የተለያዩ ወታደራዊና የቅየሳ ስትራቴጂ ትምህርት ቀስመዋል ።በሰላም ሥራ ምስራቅ አፍሪካ ላይ የተለያዩ ወታደራዊ ግዳጆችንም የተወጡ ሲሆን በተሰለፉባቸው የውጊያ ዐውዶች አራት ጊዜ ያህል ተመትተው የመቁሰል አደጋ አጋጥሟቸው ነበር ።

በሀገሪቱ የመጣውን የሥርዓት ለውጥ ተከትሎ ሠራዊቱ ሲበተን ወደ ሱዳን ተሰደዱ ። ከዚያች ጊዜ ጀምሮ በተደረገው የፀረ-ወያኔ ትግል ውስጥ በሱዳን የጠረፍ አካባቢዎች ይደረጉ በነበሩት የሽምቅ ውጊያዎች ውስጥ ተሳትፈዋል ።በሱዳን ሰጥቂት ወራት ከቆዩ በኋላ በስለላ ሥራቸው ምክንያት ሕይወታቸው አደጋ ላይ በመሆኑ በሌሎች መንግሥታት እርዳታ ካናዳ ገቡ ።ካናዳ ከገቡ በኋላም ትግላቸውን አላቆሙም፤ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመሆን የለውጡ መንግሥት እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሀገሪቱን ከትሕነግ ቀንበር ለማውረድ በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡

በኮሎኔል ጎሹ ይመራ በነበረው የመድህን የፖለቲካ ድርጅት በአባልነት፣በጄኔራል ኃይሌ መለስ በሚመራው የኢትዮጵያ የነፃነት ግንባር በአባልነት እንዲሁም በኢንጅነር ዶክተር ቅጣው እጅጉ በሚመራው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ውስጥ ወታደራዊ ስለላና የመረጃ ከፍተኛ አማካሪ በመሆን በሀገር ውስጥና በውጭ ሐገር በሚደረጉት ፀረ ወያኔ ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል ።በተለይም በማስተባበር በኬኒያ፣ በሱማሌ ፣በሰሜን አሜሪካ ጭምር በመዘዋወር በአሜሪካ ኮንግረስና ሴኔት ውስጥ ከትግል አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እንዳይነካ በሚደረጉት የዲጂታል ዲፕሎማሲና የጎዳና ላይ ሰልፎች በአስተባባሪነት ባከናወኑት አኩሪ ተግባር ስማቸው ይጠቀሳል፡፡

እንግዳችን ሳለፉት 30 ዓመታት በቆዩባት ካናዳ ኮምፒውተር ቴክኖሎጂ እንዲሁም በፊልምና በቴሌቪዥን ፕሮዳክሽን ዲፕሎማ ያገኙ ሲሆን በባዮሎጂካልና በኬሚካል መሣሪያዎች ከአልበርታ ዩኒቨርሲቲ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ኮር ኢትዮጵያ የተሰኘውንና በዲያስፖራው የተቋቋመውን የትግል ድርጅት ውስጥ ወሳኝ ሚና የነበራቸው እኚሁ ሰው በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት የቦርድ አባልና ዋና ጸሐፊ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው ።በካናዳ የሊበራል ፓርቲ አባልና የደህንነት ተቋም ውስጥም በሙያቸው እየሠሩ ይገኛሉ ።አቶ ጌታቸው ተፈራን የዛሬው የዘመን እንግዳ ያደረግናቸው በሕይወት ተሞክሯቸውና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ነው ።



**አዲስ ዘመን፡- የሱዳንና የሱማሌን ሠራዊቶች በማሰልጠን ከፍተኛ ሥራ መሥራትዎ ይታወቃል፤ እስቲ ስለሥራዎ በጥቂቱ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ ጌታቸው፡-** በሠራዊቱ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በመንግሥት ኃላፊነት ተሰጥቶኝ በጆን ጋራንድ የሚመራውን የሱዳን ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ሠራዊት በጋምቤላ፣ አኮቦ፣ በአሶሳ፣ ጊዘን፣ በደባዚን አሰልጥኛለሁ። በተጨማሪም የሱማሌ ብሔራዊ ንቅናቄ ኩልኒስ የሚባለውን ድርጅት ጅግጅጋ ላይ ከፍተኛ ስልጠና አድርጌ ሀገራቸውን ነፃ እንዲያወጡ እርዳታ አድርጌያለሁ። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር ሱዳን ውስጥ በስለላ ሥራ ተመድቤ ኃላፊነቴን በሚገባ ተወጥቻለሁ ።በተለይም ከፍተኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን ለመከላከያም፤ ለኢትዮጵያ ደህንነት ተቋም ከቲያ ጀምሮ እስከ ገዳሪፍ ፤ ካርቱም ሁንዱርማን ድረስ ያልሄድኩበት የሱዳን ምድር የለም ።የኢትዮጵያ ዳር ድንበሮችን በመቃኘትና ከፍተኛ የስለላ ሥራዎች በመሥራት ኢትዮጵያ ከሚደርስባት ከፍተኛ ጉዳቶች በታሪክ የተመዘገቡ ብዙ ሥራዎች ሠርቻለሁ ።

**አዲስ ዘመን፡- ከሀገር የወጡበትን አጋጣሚ ምን ነበር?**

**አቶ ጌታቸው፡-** ከሃገር የወጣሁበት ምክንያት ትሕነግ ሃገሪቱን ሲረከብና ሠራዊቱ ሲበተን ነው። በውትድርናው ዓለም ያሰለጠኑኝ መምህሮቼ ለጠላት እጅ መስጠትን አላስተማሩኝም ፤ ለባንዲራዬም ቃል የገባሁ በመሆኔ ተመልሼ መጥቼ የመዋጋት እቅድ ስለነበረኝ ነው ከሃገሬ የወጣሁት ።እናም አሁን በሕይወት ከሌሉ የትግል አጋሮቼ ጋር በመሆን ታግለን ጠላትን ድባቅ መተን ነው ወደ ሱዳን ድንበር የገባነው ።በነገራችን ላይ ወደ ሱዳን ከተጓዝነው 150 አባላት ውስጥ ሰባት ብቻ ነን በሕይወት የተረፍነው ።በሱዳን ገዳሪፍ በነበርኩበት ጊዜ በካፒቴን ሐሰንና በኮማንደር ጣሰው በሚመራው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲ አሊያንስ የሚባል ድርጅት ስር ታቅፌ የተለያዩ ፀረ ትሕነግ ሥራዎችን አከናውኛለሁ። ይሁንና ሁኔታው ምቹ ባለመሆኑና በተለይ ደግሞ ሱዳን ውስጥ ከዚያ በፊት ሚሽን ተሰጥቶኝ በሠራሁት የስለላ ሥራ ሕይወቴ አደጋ ውስጥ ስለነበር በተለያዩ የዓለም መንግሥታት ድጋፍ በአስቸኳይ ሀገሪቷን ለቅቄ ወጣሁ ።በነገራችን ላይ ሱዳን ውስጥ የቆየሁት ዘጠኝ ወር ብቻ ነው፤ እንደነገርኩሽ በነበረኝ ሚና ምክንያት በፍጥነት እንድሄድ ነው የተደረገው ።ደግሞም ወቅቱ የመጨረሻው የገልፍ ጦርነት የተነሳበትና ሱዳን ውስጥ የነበሩ ኤምባሲዎች በሙሉ ሃገሪቱን ለቀው ወጥተው ስለነበር በተለይ ሱዳን ለኢራቅ ዋነኛ አደጋ ስለነበረች ለእኔ ቅድሚያ ተሰጥቶኝ የመጨረሻው በረራ ከአምባሳደሮች ጋር ይዘውኝ አምስተርዳም ሄድኩኝ፤ ከአምስተርዳም ወደ ካናዳ ገባሁኝ ።

**አዲስ ዘመን፡- ካናዳ ከገቡም በኋላ የትሕነግን ሥርዓት ለመጣል በርካታ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ እንደነበር ይታወቃል ።እስቲ ይህንን ያጫውቱን?**

**አቶ ጌታቸው፡-** ልክ ነሽ፤ ከሃገሬ ብወጣም ትግሌን አላቆምኩም ነበር ።በመሠረቱ እኔ ከሱዳን ራሱ መውጣት አልፈለኩም ነበር ።ምክንያቱም ተመልሼ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዲዩ) ከሚባለው ድርጅት ጋር በመሆን ትሕነግን መዋጋት ነበር እቅዴ ።ደግሞም የሕክምና ባለሙያም ስለነበርኩኝ ለኢዲዩ አባላት በሕክምና አገለግላቸው ነበር ።እንደገና ወደ ሱዳን ተመልሼ ውጊያ ጀምሬም ነበር ።ሆኖም በወቅቱ ሁኔታው ጥሩ ስላልነበር ዛሬ በሕይወት የሌሉት አንዳንድ ሰዎች ከሃገር ብወጣና ወደፊት ተመልሼ ብመጣ ሃገሬን እንደምጠቅም ስለሚያውቁ እንድወጣ አደረጉኝ ።እንደወጣሁም በመጀመሪያ ትግል የጀመርኩት በኮሎኔል ጎሹ ይመራ በነበረው የመድህን የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ነው፡፡

በዚህ የፖለቲካ ድርጅት አማካኝነት እዚህ ድረስ በመምጣት ታጋዮችን አደራጅ ነበር ።ለምሳሌ በቴፒ፣ በሚዛን ተፈሪ፣ ከአማን እስከ ጎንደር ጭልጋ ድረስ እየሄድኩኝ አንዳንድ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ወታደራዊ ስትራቴጂ ቦታዎችን ካርታዎች በማውጣት አቀርብ ነበር። በመቀጠልም ከዚያ ድርጅት በመውጣት ከጀነራል ሃይሌ መለሰ ጋር በመሆን በተለያዩ ዘመቻዎችና ኦፕሬሽኖች ውስጥ በመርዳት እገዛ አደርግ ነበር ።ከዚያም በኢንጂነር ዶክተር ቅጣው እጅጉ ይመራ በነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር ውስጥ ነው የገባሁት። በተለይም የኢንጂነር ቅጣው የቅርብ አማካሪ ሆኜ ስሠራ ነበር ።በተለይ በወታደራዊና በኢንተለጀንሲ አማካሪ በመሆን በኬኒያ፤ በኡጋንዳና በኢትዮጵያ መሬት የወረደ ሥራ ሠርቻለሁ ።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር ውስጥም ታጋዮችን በማደራጀትና የተለያዩ ዝግጅቶች በማድረግ ሥርዓቱን ለመገልበጥ ጥረት ስናደርግ ነበር ።በአጠቃላይ አሁን ልገልፅልሽ የማልችላቸው ወታደራዊ ተግባሮችን ፈፅመናል፤ ብዙ ውጤቶችንም አምጥተናል ።በዚያ ወቅት ኬኒያ ድረስ እየመጣሁ ኮማንደር አበረ አዳሙ ጋር ትግሉን በሚመለከት ግንኙነት እናደርግ ነበር። በመሠረቱ ኮማንደር አበረን ከኤርትራ ያስፈታነው እኛ ነን። እሱን ጨምሮ ብዙ ወታደሮች አስፈትተናል ።የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኬኒያ በተጉላሉበት ጊዜ የመጀመሪያውን የገንዘብ፣ መድኃኒትና የተለያዩ ቁሳቁሶች ድጋፍ ከካናዳ ይዤ የመጣሁት እኔ ነኝ ።እንዳልኩሽ የሙዚቃ ባለሙያዎችን በማስተባበር የተሰባሰበውን መዋጮ የድርጅቱ ተጠሪ ከነበሩት ከአቶ መላኩ ስዩም ጋር በመሆን ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይዘን መጥተናል ።ለኮማንደር አበረ ደግሞ ለአርበኞቹ ግንባር የሚያስፈልገውን የሳተላይት መሣሪያዎች ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ጋር በመሆን አሟልተን ትግላችን በሚገባ ቀጥለናል ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ድረስ በመምጣት በድፍረት የነበረውን ሥርዓት ለመገልበጥ ኅቡዕ ወታደራዊ ድርጅት በማቋቋም ሂደት ያጋጠመዎት አደጋ እንደነበር ሰምተናል ።እስቲ ስለዚህ አደጋ ይንገሩን?**

**አቶ ጌታቸው፡-** እውነት ነው፤ በርካታ ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር፤ እስር ቤቶችም ገብቼ የወጣሁበት አጋጣሚ አለ ።ትልቁና ከፍተኛ የሚባለው አደጋ ግን ዋቢሸበሌ ሆቴል ከተሰበሰብን በኋላ በምግብ አድርገው እንድመረዝ አድርገውኝ የነበረበት ጊዜ ነው ።በአስቸኳይ በኬኒያ አየር መንገድ በኩል በቀጥታ ናይሮቢ በመሄድ ቀጥሎም አምስተርዳም ከገባሁ በኋላ ካናዳ ደርሼ ሕክምና የተደረገልኝ ።በዚያ አደጋ ምክንያት ልቤ ክፉኛ የተጎዳ ሲሆን ለአንድ ዓመት ከስድስት ወራት ያህል እግሮቼ ሽባ (ፓራላይዝ) ሆነው ነበር ።ልቤን እዛው ካናዳ ታክሜ ብድንም እግሬ መዳን ባለመቻሉ እዚህ መጥቼ በፀበል ነው የተፈወስኩት ።ከተመረዝኩኝ በኋላ እስትሮክ(ድንገተኛ የአንጎል ደም መፍሰስ)እንኳን አራት ጊዜ አጋጥሞኝ ነበር ።ይህ ሊሆን የቻለውም የሰጡኝ መርዝ በጣም አደገኛ ስለነበር ነው፡፡

በነገራችን ላይ ይህ መርዝ ስሪቱ ከቻይና የሆነ ነው፤ ይህንን መረጃ እስካሁን ይፋ ሳይደረግ የቆየው የካናዳ መንግሥት የሕክምና ሕግ መሠረት ከእኔ በስተቀር መረጃውን ማስተላለፍ ስለማይቻል ነው ።ይህ ቢሆን ኖሮ ስልጣን ላይ የነበረውን የትሕነግን መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ መክሰስ የሚቻልበት እድል ነበር ። በመሠረቱ እኔ ብቻ ሳልሆን በርካታ የኢትዮጵያ ምሑራንና ፖለቲከኞች በእስር ቤት የነበሩ ዜጎች ይመረዙ የነበሩት ከውጪ በሚመጣ አደገኛ መርዝ አማካኝነት ነው። እነዚህ የመርዝ አይነቶች በምግብ መልኩ የሚሰጡ ሲሆኑ አዕምሮንም ሆነ ሌሎች የሰውነት አካላትን ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጭ የሚያደርጉ ናቸው ።ለዚህም ነው አብዛኞቹ የሃገራችን ፖለቲከኞች ይህንን መርዝ ተቀብለው ወጥተው ፈዘውና የተለያዩ አካል ጉዳተኛ ሆነው የሚቀሩት ።እኔ ግን በፈጣሪ እርዳታ የካናዳ መንግሥት በልቤ በኩል የሚደረገውን ሕክምና ካደረገልኝ በኋላ እግርና እጄን እዚህ መጥቼ ዳንኩ ።በአሁኑ ሰዓት እስትሮክ የሚባል ነገር የለብኝም፤ መላው ሰውነቴ ጤነኛ በመሆን እንዳሻኝ እንቀሳቀሳለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-ከኢንጂነር ዶክተር ቅጣው ጋር በሚታገሉበት ጊዜ የነበረውን ሥርዓት ለመጣል**

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ



**ነደፋችሁት የነበረው ስትራቴጂ ምን ነበር?**

**አቶ ጌታቸው፡-** እንደሚታወቀው ኢንጅነር ዶክተር ቅጣው ኢትዮጵያ ካጣቻቸው ትላልቅ ሰዎች ዋነኛው ናቸው ።በእሱ ይመራ የነበረው የፖለቲካ ድርጅትም ሃገሪቱን ከፅንፈኛው ትሕነግ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የሚያስችል በኢኮኖሚ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስ ስትራቴጂ ነድፎ ነበር ።በነገራችን ላይ በስትራቴጂ ደረጃ ከማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ቀድሞ የፖለቲካ ፕሮግራም የነበረው ድርጅት ነው ።እንዳልኩሽ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም ይህ ብቻ ሳይሆን የመከላከያን ስትራቴጂም ነድፈናል።በተለይም የመከላከያን አቅም ለማሳደግ በተነደፈው ስትራቴጂ በአየር ኃይልም ሆነ በእግረኛና በመካናይዝድ አቅም ሠራዊቱን ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ያለመ ነበር። ሳውዲዓረቢያን ጨምሮ ኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት ከተፈረጁ እነግብፅንም ሳይቀር መቆጣጠር የሚያስችል በቴክኖሎጂ የታነፀ ተቋም ለመገንባት አቅደንም ነበር ።

የሚገርምሽ በዚያ ጊዜ አሁን እየሠሩ ያሉትን የሳይበር ቴክኖሎጂ ሳይቀር ለመገንባት ስትራቴጂ ቀርፀን ነበር። አሁን ላይ እነዶክተር ዐቢይ የሚሠሩትን ነገር ስመለከት በእውነት ነው የምልሽ ቅጣው ቢሞት ዐቢይ ተተክቷል ብዬ እንድፅናና አድርጎኛል ።ኢንጅነር ቅጣው አስቧቸው ከነበሩት ሥራዎች መካከል ከፊሎቹ አሁን በአዲሱ ኃይል እየተሠራ መሆኑ በራሱ ትልቅ ደስታ ፈጥሮብኛል። ሰሞኑን የተመረቀውን የሳይንስ ሙዚየም ስመለከት በቀጥታ ኢንጅነር ቅጣው ፔንታጎን ውስጥ ያደርገው የነበረውን ገለፃ አይነት ያህል ነው የተሰማኝ ።

እንዳልኩሽ ትልልቅ ስትራቴጂዎችን ብንነድፍም ወደመሬት ማውረድ አልቻልንም ነበር ።ምክንያቱም ደግሞ በዚያ ወቅት ይደግፉን የነበሩት ምዕራባውያን እዚህ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ወደአንድ በማምጣት እንድናደራጅ ጠይቀውን እኛም ይህንን ማድረግ ስለተሳነን ነው ።የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች አብዛኞቹ ስልጣን ብቻ ናፋቂዎች በመሆናቸው እንደታሰበው አንድነቱን ማምጣት አልተቻለም ። እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች ቤተ-መንግሥት መግባት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይታያቸውም ነበር ።ሕዝብ ተኮር ቢሆኑና ወደአንድነት ቢመጡ ኖሮ ትልቅ ውጤት እናመጣ ነበር። ያ ቢሆን ኖሮ የእኛ ስትራቴጂ እንደታሰበውም ወያኔን ከመሠረቱ የሚጥል ነበር ።በወቅቱ ከከፍተኛ የአውሮፓ ማኅበረሰብ፤ ከአሜሪካ ኮንግረስ አባላት በመነጋገር የተለያዩ ድጋፎች ለማድረግ ፍቃዳቸውን አሳውቀውን የነበረ ቢሆንም የፖለቲካ ድርጅቶቻችን ወደአንድ ስላልመጡ እቅዱ ሳይሳካ ቀረ ።

**አዲስ ዘመን፡- የትግላችሁ ውጤት የሆነው ለውጥ ከመጣ በኋላ ከስልጣን የተወገደው የት ሕነግ ኃይል አሁንም ሃገሪቱን በጦርነት ውስጥ እንድትዘፈቅ ማድረጉ ሲያስቡ ምን ይሰማዎታል? ይህን ጽንፈኛ ኃይል ለማስወገድስ ምን መሠራት አለበት ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ጌታቸው፡-** ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ባለፉት 27 ዓመታትም በሃገሪቱ ላይ ምስቅልቅል ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ተደርጓል ።በተለይ በትሕነግ መራሹ መንግሥት ትውልድንና ሃገርን ከመገንባት ይልቅ ወደማፍረስ ተግባር ነው የተሄደው ።አንድ ብሔር ወይም ቋንቋን እያገነኑ ኢትዮጵያን ወደ መበታተንና ወደራሳቸው ጥቅም የሚሄዱበትና ሃገሪቷን ለምዕራባውያንና ለጠላቶች ከፍተው ሰጥተው ነበር ።እርግጥ ነው፤ እኛ ስር-ነቀል ለውጥ የምንሻ የነበረው ይሄ ጦርነት እንደሚመጣ አስቀድመንም እናውቀው ስለነበረ ነው ።ትሕነጎች ለኢትዮጵያ ምንግዜም እንደማይተኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ አለበት ።እኛ አሁን ትሕነግ ኢትዮጵያ ላይ የፈፀመውን በደል አስቀድመን እንደሚመጣ ስለተረዳን ነው ከመሠረቱ መጥፋት አለበት ብለን ተነስተን የነበረው።

በመሠረቱ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በነበርንበትም ወቅት ጦርነቶች ነበሩ ። በተለይም በምዕራብ ኢትዮጵያ ወለጋ አካባቢ አሁን እንደሚታየው አይነት እንቅስቃሴዎች ነበሩ ።ይሁንና እነዛን ጦርነቶች የምናከሽፋቸው እዛው አካባቢ ያለውን ኅብረተሰብ በሚሊሻ በማሰልጠን ነው ። መከላከያ ምዕራብ ዕዝ ቢኖርም ጦርነቱ ውስጥ የሚገባው በጣም ከባድና ከሕዝቡ አቅም በላይ ሲሆን ብቻ ነበር። ምክንያቱም ከባድ ካልሆነ በስተቀር እንደ አሊ በርኬ ያሉ ጀግናዎች ናቸው ሚሊሻውን እያንቀሳቀሱ ጠላትን የሚመክቱት። አሁንም መሥራት የሚገባን በኅብረተሰቡ ላይ ነው ። ኅብረተሰቡን ማንቃት፣ ማስተማር አለብን።ትሕነግን ከነጭራሹ በማጥፋቱ ሂደት የምክር ቤት አባላት፣ ሚኒስትሮች የኢትዮጵያ ባለስልጣኖች በሙሉ ዶክተር ዐቢይን ማገዝ አለባቸው ።በተለይ የሕዝቡን የልብ ትርታ በማድመጥ መሠረታዊ ችግሮችን ለመፍታት ሌት ተቀን መሥራት ይገባቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በተለያየ ጊዜ መንግሥትንና ትሕነግን ለማደራደር ሲደረግ የነበረው ጥረት በአሸባሪው ቡድን ቅድመ ሁኔታዎችን የመደርደርና የሰላምን በሮች የመዝጋት ሁኔታ ይስተዋላል። አሁንም በአፍሪካ ኅብረት አማካኝነት ለማካሄድ የታሰበው ድርድር ይሳካል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ጌታቸው፡-** ከዚህ በፊት ትሕነግ ደብረብርሃንና ሰላ ድንጋይ ሲደርስ ያንን ሁሉ የአማራና የአፋርን ሕዝብ ጨፍጭፎና ደፍሮ ሳለ ለምን ምዕራባውያኑም ሌላው አካል ተደራደሩ አላሉም? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለኝ ።ታስታውሺ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጦር ሜዳ እስኪዘምቱ ድረስ የትኛውም አካል ተደራደሩ አላለንም ። ምዕራባውያኑ መከላከያ ሠራዊታችን ትሕነግን ድባቅ ሲመታው ጠብቀው ተደራደሩ የሚሉት ለምን እንደሆነ ማጤን ተገቢ ነው ።በእኔ እምነት ከዚህ በኋላ የውጭ ኃይሎች በእኛ ላይ ሊጫወቱና እንዳሻቸው ሊዘውሩን አይገባም ።ምናልባት የኢትዮጵያን ደህንነት አይተው ሊመጡብን ይችላሉ፤ ግን ኢትዮጵያ ከኒውክሌር የበለጠ ስውር ኃይል አላት ።የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጀግና ነው ።ፈጣሪ ራሱ ለኢትዮጵያ የገባው ቃል በመኖሩ ለጠላቶቿ አሳልፎ ይሰጣታል ብዬ አላምንም፤ በመሆኑም ሃገርን ለመበተን የሚሠራውን ይህንን ጽንፈኛ ቡድን እስከወዲያኛው ለማጥፋትም በህብረት ልንታገል ይገባል ባይ ነኝ ።

በእርግጥ እርቅ ጥሩ ነው፤ በበኩሌ ግን ከወያኔ ጋር የሚደረግን እርቅ አልደግፈውም ።ደግሞም እርቅ ላይ የምትቀርቢው እኮ የሚቀበልሽ አካል ሲኖር ነው ።ትሕነግ ጭንቅላቱ ለፍቅርም ሆነ ለእርቅ የተዘጋ ነው ።መቀበልም መስጠትም አይችሉም ።ደግሞም እነዚህ ሰዎች ምን ያህል የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እንዳወደሙ መገንዘብ ይገባናል ።ለዓመታት የፈፀሙት በደል እያለ ሕዝቡ ምህረት ቢያደርግላቸውም በደሃ ሕዝብ መዋጮ የተገዛውን የጦር መሣሪያ በመጠቀም ኢትዮጵያን ወግተው ዛሬ በ10 እና 20 ዓመታት ሊገነቡ የማይችሉ ትምህርት ቤቶችን እና የሃይማኖት ተቋማትን አፍርሰው ሄደዋል ።

ለሞቱት ማነው ተጠሪ? በትግራይ ላለቀው ያ ሁሉ ወጣት ተጠያቂው ማነው? እርግጥ የውጭ ኃይሎች ሁልጊዜም ቢሆን የሕዝብ ቁጥር እንዲቀንስ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዳያድግ ነው የሚሠሩት ።በዚህ አካባቢው ያሉ ሃገራትም ስልጣኔ ያለው እዚህ ስለሆነ የኢትዮጵያን እድገት አይፈልጉትም ።ምክንያቱም በኢትዮጵያ የተደበቁ ሚስጥሮች በመኖራቸው ነገ የዓለም የበላይ ይሆናሉ የሚል ስጋት ስላለባቸው ነው ። በአጠቃላይ አሁን ተደራደሩ የሚሉን አካላት በእርግጥ ለእኛ አስበው ስለመሆኑ መመርመር አለብን ። እኔ ግን ጥርጣሬው አለኝ ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት አባልነትዎ ምክር ቤቱ የሃገርን ገፅታ በመገንባትና በዲፕሎማሲው መስክ ምን ያህል ሚናውን ተወጥቷል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ጌታቸው፡-** በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እናደርጋለን ።ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካ ኮንግረሶችን በማነጋገር ከከፍተኛ ባለስልጣኖችም ጋር ብዙ ሥራ ሠርተናል ።የተለያዩ መርሐ ግብሮች ሲዘጋጁ አቅም ለሌላቸው ዜጎች አስፈላጊ ድጋፍ አድርገናል። በተለይ በካናዳ በመንግሥት ደረጃ ያሉ ሰዎችን በመጠቀም ስለሃገራችን እውነታ እንዲገነዘቡ ጥረት ሳደርግ ነበር ።ሰልፍ ሲደረግም የትራንስፖርት ኩባንያ ስላለኝ ለሰልፈኞቹ የትራንስፖርት አገልግሎት በነፃ እሰጣለሁ ።በሌሎችም መድረኮች ዲፕሎማሲያዊ ትግሎችን እናደርጋለን ።አሁንም የተግባር ምክር ቤቱ ደብዳቤዎችን በመጻፍ፣ በተለያዩ የዓለም ብዙኃን መገናኛዎች በመቅረብ ስለኢትዮጵያ ትክክለኛ ገጽታ ያደረጋል ።የራሺያ መንግሥትም ኢትዮጵያን እንዲረዳት ከውጭ ሆነን ግፊት እናደርጋለን፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ባሉ ጠበብቶች ሁሉ የእኛ እጅ አለበት ።እዚህም በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ሌሎቹ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ ከጀርባ ሆነን ያለውን ውስጣዊ አሠራር እናከናውናለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዲያስፖራው ሃገርን በማሳደግ ረገድ ምንዓይነት ሚና ሊኖረው ይገባል ይላሉ?**

**አቶ ጌታቸው፡-** በተግባር ምክር ቤቱ ያሰብነው ሦስት መሠረታዊ ነገሮች አሉ ።ለምሳሌ በልማት ላይ እንደዜጋና አገራዊ ተሳትፎ ለማድረግ ዲያስፖራው በአገር ቤት ኢንቨስት እንዲያደርግ የተለያዩ ነገሮችን እናመቻቻለን ።የውጭ ዜጎችንም ጭምር እናበረታታለን። የገጽታ ግንባታም ሥራም በስፋት እንሠራለን ።በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ግለሰቦችና ጠላቶቻችን ሳይሆን ኢትዮጵያ ሃገራችን ለኢንቨስትመንትም ሆነ ለቱሪዝም አመቺ ሁኔታዎች አሏት ።በተለይ በዶክተር ዐቢይ እየተሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች ሁላችንንም ሃገራችን ላይ መዋለ ንዋያችንን እንድናፈስ የሚያግዙ ናቸው ።በግሌ ለዓለም አቀፍ ዲያስፖራዎች መናገር የምፈልገው ውጭ ሆኖ ከማየት ውስጥ ገብቶ ሃሳብ መስጠትና መደገፍ እንደሚገባቸው ነው ። ከሚሰሙት ነገር ብቻ ተነስቶ ክፉ ከመናገር ይልቅ መልካም ነገር አይቶ መልካም መናገርና ኅብረተሰብ ማሳደግ ያስፈልጋል ።ሃገር ሃገር ናት፤ አትለወጥም ።ዶክተር ዐቢይ የሚሠራው ለሀገር ነው፤ ለማንም አይሠራም ።ጊዜውን ሲጨርስ ይሄዳል ደግሞ ሌላ መሪ ይተካል፡፡ይህንን መገንዘብ ይገባል ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ የተመድ የሰብዓዊ መብትን አስመልክቶ ያወጣውን ሪፖርት ላይ ያልዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ጌታቸው፡-** በአጠቃላይ በሰብዓዊ መብት ጉዳይ ለመሥራት የተቋቋሙ የውጭ ድርጅቶች አድሏዊ ናቸው። ሪፖርቱ በእኔ በኩል ተቀባይነት የለውም ።የተግባር ምክር ቤቱም አይቀበለውም ። ከ1945 ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጨምሮ ማንኛውም ድርጅት ኢትዮጵያ ላይ አድልዎ ያደርጋሉ ።ሁሌም የኢትዮጵያን መከላከያ ይወነጅላሉ። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በዓለም በስነ-ምግባርና በብቃት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከሚቀመጡ ዋነኛው ነው። ደግሞስ የትግራይ ሕዝብን ለመጠበቅ ላለፉት 20 ዓመታት ልጁን፣ ቤቱንና ንብረቱን ጥሎ የሄደ ሠራዊት መሆኑን እንዴት ይዘነጋል? ።እነሱ እንደሚሉት ወንጀለኛ ከሆነ የሚማረኩትን የሚያበላው፣ የሚያጠጣው ለምንድን ነው? ።መቀሌ ለመግባት ያልፈለገው ሕዝብን ከአደጋ ለማዳን እንደሆነ ግልፅ ነው ።ኮንጎም ሆነ ኮሪያ ዘምተናል በዲሲፕሊናችንም በጀግንነታችንም የታወቅን ነን፤ አሁንም ድረስ ኮሪያ ውስጥ ሠራዊታችን የሚነሳው በመልካም ዝናው ነው ።በሶማሊያ፣ በደቡብ ሱዳን ሄዶ አገልግሏል ።ከአለባበስ ጀምሩ ጥሩ ዝና ስነ ምግባር አለው።

ተመድም ሆነ ሌሎች የምዕራብ ሃገራት እውነት ለፍትሕ የሚጨነቁ ከሆነ ለምን የታረደውን፣ የተረገጠውንና ታንክ የሄደበትን ሠራዊት፣ በአንድ ቤት የተቃጠለውን ሬሳ ለምን አልዘገቡትም? ።የሰብዓዊ መብትስ ድርጅቶቹ ያንን የአፋር ሕዝብ፣ የተጎዱ ልጆች፣ ሕጻናት አስከሬን ጡት ሲጠቡ የታየበትን ለምንድን ለተባበሩት መንግሥታት ያላቀረቡት? ።የአማራ ሕዝብ በማይፀብሪ፣ በጠለምት፣ በጭልጋ፣ በዳባት፣ በደባርቅና በተለያዩ ቦታዎች የሞተውን በፎቶ ግራፍ አስደግፈው ለምን አያቀርቡም? ።ይህንን ነው ሁላችንም መመርመርና መጠየቅ የሚገባን ።እርግጥ ጦርነት ላይ ትንሽ ስህተት ሊኖር ይችላል ። ደግሞም ሰው መርጦ አይመታም ።ማንኛውም አካል ጦር ሜዳ እስከተገባ ድረስ የማይመታበት ምንም ምክንያት የለም ።ምክንያቱም ሌላውም አካል ቢሆን ለመግደል ነዋ የሚመጣው ።እኔስ ብሆን ሊገለኝ እየመጣ ዝም እላለሁ እንዴ? ።ይሁንና ከሰብዓዊ ጥሰት፣ ሴት መድፈር፣ አልባሌ ነገር መፍጠርና መሰል ተግባራት ጋር ተያይዞ የቀረበበት ክስ ፈፅሞ የመከላከያ ሠራዊታችንን የሚመጥን አይደለም ። በኢትዮጵያ ታሪክ ሠራዊቱ አድርጎት አያውቅም ወደፊትም አያደርግም ።በአጠቃላይ በሰብዓዊ መብት ድርጅቱ የቀረበው ሪፖርት ፈፅሞ ከእውነት የራቀና ማንም ሊቀበለው የማይችል ነው ።

**አዲስ ዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎችና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ጌታቸው፤** እኔም እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ ።

# ማህደረ ጤና

## መካንነት ምንድን ነው?

እፀገነት አክሲሉ

መካንነት ማለት ከአንድ አመት በላይ ያለ እርግዝና መከላከያ በተደረገ የግብረስጋ ግንኙነት ለመፀነስ ያለመቻል ሲሆን፤ በዚህ መካከል ግን የሴት ዕድሜ 35 እና ከዛ በላይ ከሆነ መካን ለመባል የሚያስፈልግበት ጊዜ እስከ ስድስት ወር ነው፡፡

መካንነት 10 እስከ 15 በመቶ በሆኑ ጥንዶች ላይ የሚታይ ችግር ነው የሚሉት የተለያዩ የዘርፉ ጥናቶች ይህ ማለትም ዕድሜያቸው ከ 20 እስከ 45 ዓመት የሆኑት ጥንዶች ላይ በጣም የተለመደ ችግር ነው ። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን አብዛኞቹ ጥንዶች ሙሉ ጤነኛ ከሆኑ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እርግዝና ይፈጠራል፡፡

### የመካንነት ምክንያቶች

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኛውን ጊዜ በተለይም በሴቶች ላይ ለመካንነት መንስኤ ሆኖ የሚገኘው እድሜ ነው ።በመሆኑም የሴት ልጅ ዕድሜ ትልቅ ተፅዕኖ አለው ፤ በተለይ ወደ 30 እና 40ዎቹ የደረሱ እንስቶች ከፍ ያለ ጫና ያለው መሆኑንም ጥናቶቹ ይናገራሉ ። ለጤነኛ ሴት በ20ዎቹ ዕድሜ ወይም የ30 መጀመሪያ አመታት እርግዝና የመፈጠር እድሉ በየወሩ ከ 25 እስከ 30 በመቶ ሲሆን፤ በ40ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ያለች ሴት ግን የማርገዝ ዕድሏ 10 በመቶ ወይም ከዚያ ያነሰ ስለመሆኑ ይነገራል ።

እድሜዋ ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት በወር ውስጥ አንዴም እንቁላል (የሴት ዘር) ካልለቀቀች የማርገዝ ችግር ያጋጥማታል ።ይህንን ችግር ሊያመጡ ከሚችሉ ችግሮች መካከል ደግሞ የእንቅርት ህመም፣ የሆርሞን ችግሮችና polcystic ovary syndrome (PCOS) የሚባል በሽታ መሆኑን ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪ የወር አበባ በትክክል በየወሩ የማያዩ ሴቶች ይህ ችግር ያጋጥማቸዋል። እንዲሁም ከመጠን በላይ ውፍረት መጨመርና ክብደት መቀነስ የየራሳቸው አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖራቸውም ተገልጿል፡፡

### የማህፀን ቱቦ መጎዳት ወይም መዘጋት

የማህፀን ቱቦዎች ከማህፀን ጋር የተገናኙ ሲሆን፤ የወንድ ዘር እና እንቁላል የሚገናኙበት ቦታ ነው ።የማህፀን ቱቦ መዘጋት ወይም መጎዳት መካንነት ወይም ከማህጸን ውጭ እርግዝናን ሊያስከትል ይችላል፡፡

### የማህጸን ጨፍ ችግሮች

የማህጸን ጨፍ ችግሮች መካንነት ከሚያመጡ ነገሮች መካከል ተጠቃሾቹ ሲሆኑ፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ መካን የማድረግ እድላቸውም አናሳ ነው ።የማህፀን ጫፍ ችግር ፅንስ የማህፀን ግድግዳ ላይ ተለጥፎ እድገቱን እንዳይጀምር ያደርጋል ።

### የሆድ እቃ ችግሮች

ሆድዕቃ ችግሮች የሚባሉት ሆዳችን ውስጥ ያሉት የሰውነት ክፍሎች ( ኦርጋንስ)የሚሸፍን ጠባሳ ወይም Endometriosis (ኢንዶሜትሪዮሲስ) ማለት ሲሆን ማህጸን ላይ የሚገኘው ቲሹ ( tissue ) በሌላ ቦታ ላይ ሲበቅል ነው ።ይሄ ቲሹ (pelvis) ፔልቪስ ውስጥ በሚገኘው በማንኛውም አካል ላይ አቫሪም ላይ ሊበቅል የሚችል ነው ።በመሆኑም እነዚህ ነገሮች በሴቶች ላይ በሚከሰቱበት ጊዜ መካንነትን ያስከትላሉ ።

### የወንድ መካንነት


አንድ ሶስተኛው የሚሆነው የጥንዶች መካንነት ችግር በወንዶች ምክንያት ሲሆን፤ ሌላው አንድ ሶስተኛው ደግሞ የመካንነት ችግር ደግሞ በሁለቱም ጥንዶች በአንድ ላይ የሚከሰት ችግር ነው ።ወንዶች መካን የሚሆኑባቸው ምክንያቶች የወንድ ዘር አለመስራት ወይም የወንድ ዘር አለማመንጨት ናቸው፡፡

### ምክንያቶቹ ያልታወቀ የመካንነት ችግር

ከ10 በመቶ እና ከዛ በላይ የሚሆኑ መካኖች የሚታወቅ ምክንያት የላቸውም፤ ይህም ምክንያቱ ያልታወቀ የመካንነት ችግር ይባላል ።አልፎ አልፎም እነዚህ ችግሮች በህክምና ሊታገዙ ይችላሉ፡፡

የመካንነት ችግር በጥንዶች ላይ ተከሰተ የምንለው በየጊዜው የወሊድ መከላከያ ሳይጠቀሙ ለአንድ አመት ግንኙነት ቢያደርጉም ጽንስ መፈጠር ካልቻለ ነው ።ይህ ችግር የወንድም ሆነ የሴት ችግር ሊሆን ይችላል ። ከዚህ ጋር ተያይዞ እድሜያቸው ከ40 ዓመት እድሜ በላይ በሆኑ ጥንዶች ላይ ይህ ችግር የማጋጠም እድሉ የጨመረ ነው፡፡

አጋላጭ ምልክቶች




**በእድሜ ከ40 ዓመት በላይ መሆን ፣ የወርአበባ መብዛት ሲከሰት ፣ በቤተሰብ መውለድ ወይም የመካንነት ችግር ሲኖር፣ የማህፀን ኢንፌክሽን ተከስቶ ከነበረ፣ የአባላዘር በሽታ ካጋጠመ ፣ ለማንኛውም ዓይነት ካንሰር የጨረር ወይም ኬሞቴራፒ ህክምና ከተደረገ፣ የማህፀን እንዲሁም የዘርፍሬ ሳንባ ነቀርሳ (Tb) ተይዘው ከነበረ እንዲሁም ያልታከመ ሳንባ ነቀርሳ ተይዘው ከነበሩ፣ በወንዶች የፕሮስቴት የዘር ፍሬ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የስንፈት ወሲብ ችግር ካለና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች እንደመንስኤ ይጠቀሳሉ**

ለመካንነት ችግር ለመጋለጥ የዘረመል ችግር (genetic problem) ዋና ምክንያት ሊሆን ይችላል ።ይህ ደግሞ ምንም አጋላጭ ምክንያቶች ሳይኖሩ ሊፈጠር የሚችል ነው ።ይህ አይነት መካንነት (primary infertility) ወይም እርግዝና ተከስቶ የማያውቅበት አይነት የመካንነት አይነቶች ውስጥ ዋናው ነው፡፡

በሌላ በኩልም የዕንቁላል ማጠራቀሚያ ወይም ዕንቁላል ችግር፣ የወንድ የዘርፍሬ አፈጣጠር፣ መጠን እንዲሁም የዘርፈሳሽ አወራረድ ችግር፣ በተለያዩ ምክንያቶች የማህፀን ቱቦ መደፈን፣ በሰውነት እድገት (hormone) መዛባት ምክንያት እርግዝና ያለመከሰት እድሉ ይሰፋል፡፡

### የመካንነት ምልክቶች

በእድሜ ከ40 ዓመት በላይ መሆን ፣ የወርአበባ መብዛት ሲከሰት ፣ በቤተሰብ መውለድ ወይም የመካንነት ችግር ሲኖር፣ የማህፀን ኢንፌክሽን ተከስቶ ከነበረ፣ የአባላዘር በሽታ ካጋጠመ ፣ ለማንኛውም ዓይነት ካንሰር የጨረር ወይም ኬሞቴራፒ ህክምና ከተደረገ፣ የማህፀን እንዲሁም የዘርፍሬ ሳንባ ነቀርሳ (Tb) ተይዘው ከነበረ እንዲሁም ያልታከመ ሳንባ ነቀርሳ ተይዘው ከነበሩ፣ በወንዶች የፕሮስቴት የዘር ፍሬ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የስንፈት ወሲብ ችግር ካለና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች እንደመንስኤ ይጠቀሳሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ከዘር ወይም ዘረመል ችግር አንዲት ሴት ወይም አንድ ወንድ ጽንስ መፍጠር ያለመቻል የሚመጣ መካንነት ውጪም በተለይ እርግዝና ተከስቶ የሚያውቅ አይነት (secondary infetlity) የሚያመጡ ምክንያቶችም አሉ፡፡

እነዚህ ምልክቶች በወንዶች ላይ ስኳር ፣ የአባላዘር በሽታ፣ ጆሮ ደግፍ እንዲሁም ኤች አይቪ ኤድስ የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የዘር ፍሬ ማስተላለፊያ ችግር የሚያመጡ በሽታዎች እንደ ቲቢ፣ባክቴሪያና ኢንፌክሽን፣ አልኮል መጠጥ መጠጣት ሲጋራ ወይም አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም ፣አንዳንድ ለደም ግፊት እንዲሁም ለኢንፌክሽን የሚሰጡ መድሀኒቶች በተደጋጋሚ መውሰድ፣ ፀረተባይ መድሀኒትና ጨረር የካንሰር መድሀኒቶች አካባቢ ተጋላጭ መሆን ይጠቀሳሉ ።

እነዚህ በሴቶች ላይም የራሳቸው መገለጫዎች ያሏቸው ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል እንቁላል ከእንቁላል የማጠራቀሚያው ወደ ማህፀን እንዲመጣ እንዲሁም ከወንድ የዘር ፍሬ ተጣምሮ በማህፀን እንዲቀበር የሚያደርጉ ሆርሞንስ (hormone) ችግሮች፣ የማህፀን እጢና የማህፀን የእንቁላል የማጣራቀሚያ ካንሰሮች፣ በተደጋጋሚ እንዲሁም በህክምና ተቋም በተገቢው መንገድ ያልተደረገ ውርጃ፣ ከእንቁላል ማጠራቀሚያ ወደ ማህፀን በሚወስደው ቱቦ ችግር (በኢንፌክሽን ፣በውርጃ እንዲሁም ቀዶ ጥገና ጊዜ የሚመጣ ጠባሳ)፣ ከሚጠበቅባት እድሜ በፊት አንዲት ሴት ቀድማ የማረጥ ጊዜዋ ሲመጣ፣ ማጨስ፣ አደንዛዥ እፅ መጠቀም፣ ፀረ ተባይ ጨረርና የካንሰር መድሀኒቶች መውሰድ፣ የክብደት በጣም መጨመር ወይም መቀነስ፣ ሀይለኛና አቅም የሚጠይቅ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠቀሳሉ።

በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው ብዛት ያላቸው ጥንዶች በተለያዩ ምክንያቶች የመካንነት ችግር ሊመጣባቸው ስለሚችል ያሉትን ችግሮች ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ መታየት፣ ምርመራዎችን ማድረግ ጠቃሚ መሆኑን ነው ።

አንዳንዴ ሁሉም ነገር ጤናማ ሆኖ እርግዝና ላይፈጠር ይችላል። ይህ የማይገለፅ መካንነት [Unexplained Infertility] ይባላል። ይህ ማለት ቴክኖሎጂ ያልደረሰባቸው ችግሮች አሉ ማለት ነው። 20 በመቶ የሚሆኑ ጥንዶችም ይህ ችግር የሚያጋጥማቸው ሲሆን በቴክኖሎጂ የታገዘ ሕክምና ሊደረግላቸው ይችላል።

መካንነት በተለይ አፍሪካ ውስጥ የተለመደ ችግር ነው ። በተለይ በአባላዘር በሽታዎችና በሌሎች ኢንፌክሽኖች የመካንነት ችግር ተንሰራፍቷል። የዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ከ15 እስከ 20 በመቶ ጥንዶች የዚህ ችግር ተጠቂ ናቸው። ሴቷም ሆነ ወንዱ በእኩል ደረጃ በመካንነት ሊጠቁ ይችላሉ፤ በመሆኑም በማኅበረሰቡ ሴቷ ላይ ብቻ ጣት የሚቀስረው በተሳሳተ አመለካከት ነው።

በአውሮፓዊያኑ 2016 የወጣው የኢትዮጵያ ሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው በተለያዩ ምክንያቶች በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የውልደት መጠን እየቀነሰ መሆኑን ያመለክታል። በከተሞች ደግሞ በ2000 ከነበረው 3ነጥብ 0 በ2016 ወደ 2ነጥብ 3 ዝቅ ብሏል።

በአጠቃላይ አንዲት ሴት መውለድ ካለባት አማካይ የውልደት መጠን በ2000 ከነበረው 5ነጥብ 5 በ2016 ወደ 4ነጥብ 6 መቀነሱን የዳሰሳ ጥናቱ ያመለክታል።

በአገራችን ይህንን የብዙ ጥንዶች ችግር የሆነውን የመካንነት ሁኔታ በህክምና ለመፍታት ከሚሰሩ የጤና ተቋማት አንዱ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ኮሌጅ ነው ።ሆስፒታሉ የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር ለመፍታት የመካንነት ሕክምና ማዕከል አስመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ 2011 ዓ.ም ነው።

አገልግሎት መስጠት በጀመረ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥም ከ 60 ሺህ በላይ ጥንዶች የመካንነት ሕክምና የተከታተሉ መሆናቸውን በሆስፒታሉ የሥነ ተዋልዶ ማዕከል የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

ከእነዚህ መካከል 1ሺ 400ዎቹ በቴክኖሎጂ የታገዘ የመካንነት ሕክምና ለማግኘት የተመዘገቡም ነበሩ። ቀሪዎቹ ደግሞ ወደዚህ ሕክምና ከመግባታቸው በፊት ሌሎች ሕክምናዎችን በመከታተል ሂደት ላይ ነበሩ ።ጥንዶች በተለያየ ኑሮና የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ከተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የመጡ ናቸው።

በዚህ መንገድ እናቶች ልጃቸውን ሲያቅፉ በደስታ ያለቅሳሉ። በጋብቻ መሃል ልጅ አላዩም ነበር። ልጅ ይናፍቁ ነበር። ልጅ ለማግኘት በዕምነት ቦታዎችና የባህል መድሃኒት ፍለጋ ሲንከራተቱ ነው የቆዩት። ከማኅበረሰቡ የሚደርስባቸው ጫናም ቀላል አልነበረም። ይህን ሁሉ አልፈው ልጅ ሲያቅፉ የተሰማቸውን ሊቆጣጠሩት የማይችሉት የደስታ ስሜት ነው። በደስታ ሲፈነጥዙ ነው የሚታየው በማለት ከሆስፒታሉ ድረ ገጽ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

ሕክምናው የሚሰጠው በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ባስተማራቸው የሕክምና ባለሙያዎች ነው። ይህ የሕክምና አገልግሎት መሰጠት ከመጀመሩ በፊት የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶች ተደርገዋል።

"በማኅበረሰቡ ልጅ መውለድ፣ ቤተሰብ መመሥረት እንደ ሕይወት ግብ ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ፤ መካንነት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ያስከትላል። በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩም ሆነ በሌላ መልኩ መፍትሔ ሲያገኙ ጥንዶች ደስተኛ ይሆናሉ" ። ይህ የሕክምና አገልግሎት መጀመሩም መልካም ጅምር ነው።

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

## “የኢትዮጵያን ስም የተሸከሙ የሙያ ማኅበራት!?”

**ታሪካዊ ማነጻጸሪያ፤**

ቀዳማዊ ናፖሊዮን ቦናፓርቴ (1769 - 1821) እውቅ ፈረንሳዊ የጦር መሪና የሀገሪቱም ንጉሠ ነገሥት እንደነበር ገድሉ ድምቆ ይተርክልናል ። ይህ ዝነኛና ብርቱ መሪ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ግድም አብዛኞቹን የአውሮፓ ሀገራት አንበርክኮ ማስገበሩ በታሪክ ተመዝግቧል። ተጠቃሹ ወታደራዊ መሪ በዓለም ላይ ከተነሱት መሰል መሪዎች መካከል በላቀ ደረጃ ግለ ታሪኩና ጀብዱው ከ250 ሺህ በላይ በሆኑ መጻሕፍት የተዘገቡለት ገናና ገዢ ነበር ። ዛሬም ድረስ የዜና መዋዕሉ ግለ ታሪክ በመጻሕፍትና በልዩ ልዩ የጥበብ ሥራዎች ያለማቋረጥ እየተተረከለት ይገኛል ።

የፈጠራ ድርሰት የሚመስሉት በርካታ የውሎ ገድሎቹ በጽሑፍ ብቻም ሳይሆን በአሉ ተባባሉ የትርክት ዘዴ እየተነገረለትና እየተዘመረለት ዛሬም ድረስ መዝለቁ ሌላው የናፖሊዮን አስገራሚ ታሪክ ነው ። ከዚሁ ገድለኛ መሪ የመረጥናቸውን ሁለት አስገራሚ “የነበር ታሪኮች” ለመንደርደሪያነት ጠቅሰን ወደ ራሳችን ዋና ጉዳይ ዘልቀን እንቆዝማለን ።

አንድ፡- ናፖሊዮን ቦናፓርቴ አውሮፓን ለመውረር በዘመተበት አጋጣሚ በተዋጊ ጦረኞቹ ፍልሚያ መካከል አንድ ክስተት ይፈጸማል ። ፍርሃት ያንዘረዘረው አንድ ወታደር የውጊያውን መፋፋም ሲያስተውል የሚመራውን የሠራዊት አሀድ ሜዳ ላይ በትኖ እግሬ አውጭኝ ብሎ ሲፈረጥጥ በጦር ሜዳ መነጽሩ አሻግሮ ይመለከተዋል ። አይቶት ብቻ ዝም አላለም ። ከወታደሮቹ መካከል ጥቂቶቹን መርጦ ያን ወታደር የፊጥኝ አስረው እንዲያመጡለት ያዛቸዋል ።

በትዕዛዙ መሠረትም ፍርሃት ያራደው ወታደር ተይዞ ወደ ናፖሊዮን ፊት እየተንቀጠቀጠ ቀረበ ። “ለመሆኑ ስምህ ማነው? ለምንስ በተፋፋመው ጦርነት መካከል ሠራዊቱን ከድተህ ለመሸሽ ሞከርክ?” አዋጊው ጄኔራል ናፖሊዮን ይጠይቀዋል ። “ጌታዬ ስሜ “ናፖሊዮን” ይባላል። የሸሸሁትም ነፍሴ አሳስታኝ እንዳልሞት ፈርቼ ነው ።” በማለት ሳይዋሽ እውነቱን ፍርጥ አድርጎ ነገረው ።

ናፖሊዮንም እንዲህ በማለት ውሳኔውን አሳወቀው፤ “ፈርተህ በመሸሽህ አልገልህም ወይንም አላስርህም ። አንድ ነገር እንድትፈጽም ግን አዝሃለሁ ። እንደ እኔ እንደ ጀግናው ናፖሊዮን በጽናት ተዋግተህ በጠላትህ ላይ ድልን ተቀዳጅ ። ይህ የማይሆንልህ ከሆነ ግን “ናፖሊዮን” የሚለውን ስምህን በአስቸኳይ መልስልኝ ።” የወታደሩ መጨረሻ ከምን እንደደረሰ ለጊዜው በወረቀት የሠፈረም ሆነ አፈ ታሪኩ የሰጠን ምንም ፍንጭ ስለሌለ የታሪኩን መደምደሚያ በእንጥልጥል መተውን መርጠናል ።

ሁለት፡- ናፖሊዮን ወደ ሥልጣነ መንግሥት መሰላል ላይ የወጣው የዘመኑ ባህል በሚፈቅደው መሠረት ዘሩን ከነገሥታቱ የደም ሀረግ ስለመዘዘ አልነበረም ። አመጣጡ ለዚህን መሰሉ ክብር የታደለ ባይሆንም ዕድልና ጊዜ ተገጣጥሞለት የዘመኑን ገናና አውሮፓዊ ሀገር የፈረንሳይን መንበረ ዙፋን ለመቆናጠጥ የበቃው “በሀገሩ ምድር ተቀጣጥሎ የነበረው አብዮት” ረድቶት ነው ። “የደሙ ንጥር” የመነጨውም ከወደ ጣሊያን እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል ። ያውም የሥልጣን ደረጃቸው ዝቅተኛ ከሆነ ቤተሰብ ።

ይህንን የናፖሊዮን ዘር ጠቀስ ታሪክ የሚያውቁ የወቅቱ የሚዲያ ባለሙያዎች አልፎ አልፎ በሽሙጥና በምፀት ወጋ ሲያደርጉት የሚሰጣቸው መልስ ከበቀል ይልቅ ብልሃት በተላበሰ ዘዴ እያዋዛ ነበር ። “ጀግና ለበቀል አይቸኩልም” የሚለው ብሂል እውነትነት ሳይኖረው ይቀራል? ለማንኛውም በሁለተኛነት በመረጥነው ታሪክ ዙሪያ ከጋዜጠኞች ጋር የገባበትን እሰጥ አገባ በተመለከተው ታሪክ ላይ እናተኩር ።

“ጀግናው ንጉሠ ነገሥታችን! የነገሥታት ዝርያ ሳይኖርህ እንደምን ወደ ተከበረው የፈረንሳይ መንበረ ዙፋን ከፍታ ላይ ልትደርስ ቻልክ?” በአንድ ወቅት የቀረበለት ጥያቄ ነበር ይባላል ። “እርግጥ ነው” አለ ናፖሊዮን ሲመልስ፤ “የነገሥታቱ ደም ከደሜ ጋር አልተዋሃደም ። የአመጣጤ ታሪክም ከዚህ እውነታ በጣም የራቀ ነው ። ነገር ግን በአንድ አጋጣሚ በፓሪስ አውራ ጎዳናዎች ላይ ስንሸራሸር አንድ ዘውድ በመንገዴ ላይ ወድቆ አገኘሁ ። ያንን የከበረ ዘውድ ዝቅ ብዬ በእጆቼ ለማንሳት ስለተጠየፍኩ እንዳያደናቅፈኝ ፈልጌ ከመንገዴ ላይ ለማስወገድ በእግሬ ወደ ሰማይ አጉኜ ለመወርወር ስሞክር ዘውዱ ቁልቁል ተምዘግዝጎ በአናቴ ላይ አረፈ ። ከዚያ ክስተት በኋላ የታላቋ ፈረንሳይ ገዢ ሆኜ ራሴን አገኘሁት ።” - የተራቀቀበት ድንቅ ምፀታዊ አባባል ነበር ። በንጉሥ ቃል ላይ ስለማይጨመር ወይንም ስለማይቀነስ፤ “እንቆቅልሹን ፍቱ?” ብዬ አንባብያንን ሳልሞግት ወደ መነሻ ሃሳቤ አቀናለሁ ።

> ዋናውና መሠረታዊው ጉዳይ የስማቸው ክብደት ወይንም የተቋቋሙበት ዓላማ ግዝፈትና ውሱንነት ሳይሆን በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ምን ዘመን ተሻጋሪ አሻራ አኖሩ የሚለው ይሆናል ። በተለይም ሀገር እንደ ዛሬው መከራ ላይ ስትወድቅ “ስሟን የተሸከሙት ማኅበራት ምን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው?” ብለን ብንጠይቅ ሊያስኮርፍ ወይንም ሊያስቀጣ አይገባም

**“የኢትዮጵያን ስም ተሸክመው የሚያነክሱ የሙያ ማኅበራት፤**

“የኢትዮጵያ” የሚል ክቡር ስም እየታከለበት የሙያ ማኅበራትን ለመመስረት አቅም ቢኖረንም ባይኖረንም ባህላችን ቸርና ደፋር አድርጎናል ። እንኳን ራእያቸው ገዝፎ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ “ጠብታ” ሊያክሉ ቀርቶ እግራቸው ራሱ በቀዬአቸው ድክ ድክ ለማለት ልምሻ የያዘው አንዳንድ የሙያ ስብስቦች ለማኅበራቸው ስም ሲያወጡ “በኢትዮጵያ ስም ለማሽሞንሞን” ምን ያህል ደፋሮች እንደሆኑ ዕድሜና ተሞክሮ በሚገባ አስተምሮናል ።

በመንፈሳዊ ሕይወት በጎ ምሳሌነታቸው የማከብራቸው አንድ አባት በጭውውታችን መካከል ይህ ርዕሰ ጉዳይ ድንገት በተነሳበት አንድ አጋጣሚ የተናገሩት ንግግር ፈገግ ማስደረግ ብቻ ሳይሆን ትልቅ “መገለጥ ሆኖ” ትምህርት የሰጠኝ ጭምር ነበር ። እንዲህ ነበር ያሉት፡ - “የኢትዮጵያን ስም አልከስክሰው የተሸከሙ አንዳንድ የሀገራችን የሙያ ማኅበራት፤ የሃይማኖታዊውን የጽዋና የሰንበቴ ማኅበራት ያህል እንኳን አቅም ቢኖራቸው ለሀገራችን ወቅታዊ ፈተናዎችና ችግሮች ከፍ ያለ በጎ አሻራ ማሳረፍ በቻሉ ነበር። ብዙዎቹ የኢትዮጵያን ስም ያነገቡ ‹የሙያ ማኅበራት› ተብዬዎች ስማቸው አምሮ ግብራቸው ግን ኮስምኖ “በተከድኖ ይብሰል” መታለፋቸው የሚመለከተውን ክፍል ሊያስወቅስ ይገባል ።” - ጸሐፊውን የሚያስማማ ትክክለኛ ገለጻ ነው ።

**የሙያ ማኅበራቱን በተመለከተ የጸሐፊው ምደባ፤**

ለግርድፍ ቅኝት እንዲመች “የኢትዮጵያን ስም ከተሸከሙት” ማኅበራት መካከል የተወሰኑትን ብቻ መርጠን ለማሳያነት እንዲረዳን አቧድነን እንዳስሳቸው። እርግጥ ነው አንዳንድ የሙያ ማኅበራት ስማቸውም ሆነ ግብራቸው ገዝፎ አንቱታን ማትረፋቸው አይካድም። በሚያሳዩት ሀገራዊ መልካም ውጤትም መመስገን የሚገባቸው ቢሆንም ። ችግሩ የዚያኑ ያህል በርካታ ቁጥር ያላቸው የሙያ ማኅበራት “ስማቸው እኩል፤ ሥራቸው ስንኩል” እንዲሉ “ሲያነክሱ መኖራቸው ነው። ለማንኛውም ውጤታቸውን ሳይሆን የማኅበራቱን ሙያ ነጥለን በቡድን በቡድን እያቀናጀን ጥቂት ምልከታ እናድርግ ።

ብዙዎቹ ማኅበራት የሚቋቋሙት የአባላቱንና የሙያቸውን ክብርና ጥቅም ለማስጠበቅ መሆኑ አይካድም፤ ትክክልም ነው ። ከዚህ ባለፈ ግን ሙያቸው “ስሟን ለተሸከሙት ኢትዮጵያ” አንዳች ፋይዳ ያለው ሀገራዊ አስተዋጽኦ የማያበረክት ከሆነ ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ሆኖ “ዶሮ ከጋጥ፤ አህያ ከቆጥ”ን ብሂል ማስታወሱ አይቀርም ።

እንቀጥል፡- አንዳንድ የሙያ ማኅበራት የአባላቶቻቸውን ጥቅም ከማስከበር በዘለለ ከኢኮኖሚ ፋይዳ አንጻር ልንመድባቸው እንችላለን ። ለምሳሌ፡ - የአታሚዎችና አሳታሚዎች ማኅበር፣ የቡና ላኪዎች ማኅበራት፣ የአትክልት፣ ፍራፍሬና አበባ ላኪ ማኅበራት፣ የምህንድስናና የአርክቴክት ባለሙያዎች ማኅበራት ወዘተ. እንደምንመኘው ይሁኑም አይሁኑ ለሀገር የሚያበረክቱት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በቀላል የሚታይ አይደለም ። ብርታት ጥንካሬያቸው እንዳለ ሆኖ ።

አንዳንድ ማኅበራት “የኪነ-ጥበባት ማኅበራት” የሚሰኙ ናቸው ። የተውኔት ማኅበራት፣ የደራስያንና ደራስያት ማኅበራት፣ የሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ማኅበራት፣ የሙዚቃ ማኅበራት ወዘተ. ትኩረታቸው ወደ ማዝናናቱና ማስተማሩ ስለሚያመዝን በጥበቡ ጎራ መቧደናቸው አግባብ ይሆናል ። ንቃተ ኅሊናን ከፍ በማድረግና ሀገራዊ ህጸጾች እንዲታረሙ በማስተማሩ ረገድ ለማሕበረሰቡ ፋይዳ ያለው አስተዋጽኦ ለማድረግ አቅም ይኖራቸዋል ተብሎ ከሚታመኑ የሙያ ማኅበራት መካከል ደግሞ የዳኞችና የዐቃቤ ሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት፣ የመገናኛ ብዙኃን ልዩ ልዩ ማኅበራትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህን ውስኖችን ብቻ ለአብነት ጠቀስን እንጂ በሕክምናው ዘርፍ፣ በንግድና በኢንቨስትመንት ወዘተ. የተደራጁትን እጅግ በርካታ “ብሔራዊ ማኅበራት” በተቋቋሙበት ተቀራራቢ ሙያቸው እያቧደንን በመዘርዘር ብንፈትሻቸው ብዙ ማለት ይቻላል ። ከሙያ ጉዳይ ውጭም በዕድሜ፣ በጾታና በአካል ጉዳተኝነት ወዘተ. የተደራጁትን ማኅበራት በመጠቃቀስ ዕይታችንን አስፍተን ብንወያይ ብዙ ገመናዎች ሊዘከዘኩ በቻሉ ነበር ።

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ዋናውና መሠረታዊው ጉዳይ የስማቸው ክብደት ወይንም የተቋቋሙበት ዓላማ ግዝፈትና ውሱንነት ሳይሆን በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ምን ዘመን ተሻጋሪ አሻራ አኖሩ የሚለው ይሆናል። በተለይም ሀገር እንደ ዛሬው መከራ ላይ ስትወድቅ “ስሟን የተሸከሙት ማኅበራት ምን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው?” ብለን ብንጠይቅ ሊያስኮርፍ ወይንም ሊያስቀጣ አይገባም ።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ከናፖሊዮን ቦናፓርቴ ሁለት ታሪኮች ጋር ለምን ለማጣቀስ እንደፈለግን ጥቂት ሃሳቦች እንፈነጣጥቅ ። በርካታ የሀገሪቱ “ብሔራዊ ማኅበራት” ስማቸው እንጂ ምን እንደሰሩ ወይንም ምን ሊሰሩ እንዳቀዱ ስሟን ያዋሰቻቸው “ኢትዮጵያ” በወከለችው ተጠሪ መንግሥታዊ ተቋም በኩል ያለመጠየቋ መልሰን የምንወቅሰው ራሷን “እምዬን” ነው ። ቢያንስ ልክ እንደ ናፖሊዮን “ወይ ስሜን መልሱ፤ አለያም የስሜን ልክ ያህል ቁምነገር ሥሩ” ብላ “መብቷን” ለማስከበር የዐይን አፋርነቷን “ዐይነ ርግብ” ለመግለጥ ለምን እንደማትፈልግ አልገባንም ። በዚህ ጉዳይ “ስሟን ተሸክመን ከመንገዳገድ ውጭ ምን ፈየድን” በማለት የየማኅበራቱ አባላት መሪዎቻቸውን ሊሞግቱ ይገባል ።

“ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ” እንዲሉ “በፍሬያቸው” መታወቁ እንኳን ቢቀር “እንክርዳዳቸው” በዝቶ ሀገሪቱን ለራስ ምታት ባይዳርጉ ይበጅ ይመስለናል ። በግልጽ እንጠይቅ ። የኢትዮጵያን ስም የተሸከሙ ስንት የስፖርት ማኅበራት አሉ? ለምን የጋራ ዓላማ ቀርጸው አብረው መሥራት አቃታቸው? ስንት የሙዚቃ ማኅበራት አሉን? እኮ ለምን ተቀባብለው በጋራ ተደጋግፎ ለሀገር ቁም ነገር መዋል ተሳናቸው? ብዕር ያሰባሰባቸው ምን ያህል የድርሰት ማኅበራት አሉን? “ያለእኔ አይሆንም” የሚሉትን የመሪዎቹንና የአባላቱን ግልጽና ስውር ፍልሚያ ለጊዜው ትተው ስለምን ተቻችለው በአንድ ዓላማ ሥር ለመሰባሰብ ተሳናቸው? ስለምንስ የችግር ቀን ደራሽ ለመሆን ተልፈሰፈሱ? ብንጠያየቅና ብንተራረም አይከፋም ።

ሰብሰብ ብለው የጋራ አቅም በመፍጠር በወቅታዊ ችግሮች ላይ የሙያቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ቢሳናቸው እንኳን ማኅበራቱ በየግላቸው በዚህ ወሳኝ የሀገራዊ ፈተና ወቅት ስለምን የግላቸውን ጠብታ ለማኖር ራእያቸው ጨለመ? ይህ የገዘፈው ሀገራዊ ጉዳይ ለጊዜው ይቆይ እንኳን ብንል ለራሳቸው ለሙያ ባልደረቦቻቸው ወይንም አባላቶች “እዚህ ግባ የሚባል” ምን ተጠቃሽና ተጨባጭ ውጤት አስመዘገቡ ። ስለዚህም ነው “ስሜን መልሱልኝ!” በማለት “ራሷ ኢትዮጵያ” እንድትሞግታቸው የምንቀሰቅሳት ።

“ማኅበሬ የሚሉት ተቋም” እግሩን ሲጎትት አብረው ላለመደነቃቀፍ በመጨከን በራሳቸው የግል ጥረት ለኢትዮጵያ ወቅታዊ ጥሪ ምላሽ በመስጠት ጀግነው ያጀገኗት ባለሙያ ልጆቿ እንኳን በቁማቸው በሞታቸው እንዴት እንደተከበሩ ደጋግመን አስተውለናል ።

ድፍረት ካልሆነ በስተቀር ብዙ “ብሔራዊ” የሚል ቅጽል ስም የያዙ ማኅበራት የተቋቋሙት ልክ እንደ ናፖሊዮን በሚገባ አስበውበት ሳይሆን ባልተዘጋጁበት ሁኔታና በሆይ ሆይታ ሞቅታ “የሙያ” ማኅበር የመሆንን የዕድል ዘውድ” መንገድ ላይ ውድቆ ስላገኙ ይመስላል። ሜዳ ላይ ወድቆ ያገኙትን እድል ደግሞ መሪዎቻቸው “ባትጋሩን” በማለት የግል ኋዳ አድርገው አባላቱን ሲከፋፍሉና ሲያባሉ እያስተዋልን ነው ።

በዚህ ጸሐፊ እምነት የሀገራችንን የሙያ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶችን የሚያመሳስሏቸው በርካታ የጋራ ባህርያት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል ። አንድም፡- ፈጥኖ ለመከፋፈልና ለመካሰስ ሱሰኞች ናቸው ። ሁለትም፡- ለመደማመጥ ጆሯቸው የተደፈነ ብቻ ሳይሆን የመሪዎቹ ልብም የደነደነ ነው ። ሦስትም፡- አመራሮቹ ለውጤታማ ግብ ከመድከም ይልቅ “በግለሰባዊ አምልኮ” (Personal cult) በሽታ የተለከፉ ስለሆኑ የማኅበር መሪ ከመሆን ይልቅ ራሱን ማኅበሩን ካልሆንን በማለት በትዕቢት ያበጡ ናቸው። እነዚህ ሦስት ባህርያት የሀገራችንን የሙያ ማኅበራት በሚገባ ይገልጿቸው ይመስለናል ።

ኢትዮጵያ ሆይ! “ጽናቱን ይስጥሽ!” ብለን ብቻ አንደመድምም ። ይልቅስ ስምሽን ለማስከበር ኮስተር ብለሽ ፈትሻቸው ። “የኢትዮጵያ...የሙያ ማኅበር” ብለው ስምሽን አለቦታው ሲያውሉም “ወይ የስሜን ክብር ያህል ስሩ፤ አለያም ስሜን መልሱልኝ” በማለት ልትሞግቻቸውና ልታስሞግቻቸው ይገባል ። ስምሽን የሚጠቀሙት ራሳቸው ሊያጌጡበት ሳይሆን ለውጤታማ ተግባር መገለጫነት እንዲያውሉት መሆኑን “ለወከልሽው መንግሥታዊ መዝጋቢ ተቋም” ኮስተር ያለ ትዕዛዝና ውሳኔ ልታስተላልፊለት ጊዜው አልመሸም ። “ከሩቁ በቅርቡ፤ ከደረቁ በርጥቡ” ብሂልን ልብ ይሏል ። ሰላም ይሁን!

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ከችግር-መር ወደ ዕድገት አለኝታነት ማደግ ያለበት ማኅበራዊ ዕሴታችን

**ደበበ ካሳ**

አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን መገለጫችን ነው፡፡አኗኗራችንም ማኅበራዊ ነው፡፡በየዕለቱ ከሚፈላው ቡና ጀምሮ ማኅበር፣ በዓላት፣ ዝክር፣ ድግስና ግብዣ፣ ሰርግ፣ ለቅሶ፣ ዕድር...ነዋሪዎችን የሚያገናኙ፤ ለዘመናት ኅብረተሰቡን አስተሳስረው የኖሩና ያሉ ማኅበራዊነት ህያው ሆኖ እንዲኖር ያስቻሉ የኢትዮጵያውያን የአኗኗር ዘይቤ ልዩ መገለጫዎች ናቸው፡፡ታዲያ በዚህ ሁሉ ማኅበራዊነት ውስጥ አብሮ የሚነሳው የኅብረተሰቡ የእርስ በእርስ የመተባበርና የመደጋገፍ ባህል ነው፡፡

አዎ ሰው በደስታ ጊዜ በጋራ ይደሰታል፣ በኃዘን ጊዜም አብሮ ያዝናል፣ በችግር ጊዜ ይተባበራል፣ ኃዘንና ደስታውን ይጋራል፡፡ይህ በእርግጥም ልንጠብቀው የሚገባ ወርቃማ ባህል ነው፣ መልካምም ነው! ይሁን እንጅ በግሌ እንደታዘብኩት በእኛ ሃገርና ባህል በደስታም ይሁን በኃዘን የምንረዳዳው አንዳች ልዩ ክስተት ወይም ጊዜያዊ ሁነትን ጠብቀን ነው፡፡የምንረዳዳው በኑሯችን ውስጥ አንዳች ችግር ሲገጥመን ነው፡፡ትብብራችን አንድ ችግር ከደረሰብን በኋላ ለዚያ ችግር ጊዜያዊ ምላሽ መስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ሌላው ይቅርና የምንልሰው የምንቀምሰው እንኳን አጥተን፤ ክፉኛ ተቸግረን ቢሆን ፤ መቸገራችን አይንኑን አፍጥጦ፣ ጥርሱን አግጥጦ፣ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሶ፣ ችግራችን ከችግርነት አልፎ በሕልውናችን ላይ አንዳች ከባድ ስጋት ካልተጋረጠ፣ ገመናችን በአደባባይ ካልተገለጠ ሊረዳን የሚፈልግ የለም፡፡የመጨረሻው ተስፋ የመቁረጥ ደረጃ ላይ ደርሰን፣ በትግሉ ተሸንፈን፣ ለችግራችን እጅ ሰጥተን ካልታየን እጁን የሚዘረጋልን የለም፡፡

በሕይወታችን ውስጥ ችግር በርትቶ፣ በትግላችን የሚያግዘን አጥተን፣ ስቃያችን በዝቶ፣ ጉልበታችን ደክሞ፣ ጥንካሬያችን ተረትቶ፣ ሞራላችን ተመትቶ፣ ልባችን ተስፋ ቆርጦ ላንመለስ ተጎድተን በቁማችን ከሞትን በኋላ ግን አዛኝ ለመሆን የሚሽቀዳደም ይበዛል፡፡ከንፈራችንን እየመጠጥን "ውይ እከሌ/እከሊት እኮ እንዲህ ሆነ/ች" እያልን "እርዳታ" ለማሰባሰብ በራሳችን ተነሳሽነት ከሁሉም ቀድመን ከፊት እንቆማለን፡፡ችግሩ ወይንም በሽታው ተባብሶ እስከወዲያኛው የሚሞት ካለም የወገናችንን ቀብር "ለማሳመር" ለዘመናት በቆየውና በዳበረው የ"ትብብር" ባህላችን በዕድራችን አማካኝነት ሟችን "ለመርዳት" ሆ ብለን እንነሳለን፤ ያውም ከብዙ ኃዘንና ደረት መድቃት ጋር፡፡

ዋነኛው የትብብር ባህላችን ወካይ መገለጫ የሆነው የዕድር ዓላማም ይኸው ነው - በሞት ወይም በችግር ጊዜ መተባበር፡፡ዳሩ ምን ያደርጋል የሚረዳው አጥቶ በችግር ብዛት ተስፋ ቆርጦ ላይመለስ የተጎዳን የቁም ሟች ወይም በቁሙ እያለ የሚደርስለት ወገን አጥቶ በችጋርና በድህነት አልያም በበሽታ ተሰቃይቶ ሳያልፍለት ያለፈን ሟች መርዳት የይምሰል ነውና ከዚህ በኋላ የሚደረገው እርዳታ በከንቱ የሚቃጠል የቃየል መስዋዕት ይሆናል፡፡ከሞተ በኋላ ሰውን መርዳት አይቻልምና!

በመሆኑም ዛሬ በዚህ መጣጥፌ ላነሳው የፈለኩት ዋነኛው ጉዳይ "መተባበር የሚገባን በችግር ጊዜ ብቻ ነው ወይ?" የሚለውን የትብብር ባህላችንን መሰረታዊ ህፀፅ ነው፡፡ ምክንያቱም መልካም ስለሆነው ባህሌ የበኩሌን የማበርከት፣ ህፀፁን የማሳየት፣ ጉድለቱን የመሙላት በዚህም ወርቃማው የማኅበራዊ ኑሮና የትብብር ዕሴት የበለጠ ለኅብረተሰቡ ሁለንተናዊ ዕድገት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበትን መንገድ የማመላከትና የተሻለ የምለውን ሁሉ የማሳየት ሞራላዊ ግዴታ አለብኝና፡፡

እናም እጠይቃለሁ፤ ለመሆኑ ዓለም ያደነቀውና አንደኛው የኢትዮጵያችን መለያ የሆነው ወርቃማው የትብብር ባህላችን በኅብረተሰባችን ውስጥ ለዘመናት አብሮ የቆየ ከመሆኑ አኳያ ለምን የሚገባውን ያህል ለዕድገታችን አስተዋፅኦ አላበረከተም? ይሄ ለምን ሆነ ብዬ ስመረምር የደረስኩበት መደምደሚያ ለዘመናት የቆየው የማኅበራዊነትና የትብብር ባህላችን የዕድሜውን ያህል ለሃገር ሁለንተናዊ ዕድገት ያላገለገለበት ምክንያት የትብብር ባህላችን በጊዜያዊ ሁነት ላይ እንጅ በቋሚ ዕውነት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን ነው፡፡

የችግሩ ዋነኛ መንስኤም የትብብር ባህላችን ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ ምላሽ መስጠትን እንጂ ችግሮች ከመከሰታቸውና ሰዎችን ከጥቅም ውጭ ከማድረጋቸው በፊት በሰላም ጊዜ ማገዝን፣ መልካምም ይሁን ክፉ አጋጣሚዎችን ተከትለው የሚመጡ ጊዜያዊ ሁነቶችን እንጂ የኅብረተሰቡን ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታና መሠረታዊ የዕድገት ዕውነቶችን መሠረት ያላደረገ መሆኑ ነው፡፡ከእኛ አልፎ በዓለም ደረጃ የምንታወቅበትና ማኅበራዊነት ላይ የተመሠረተው መልካሙና ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረው አንጋፋው የትብብር ባህላችን መጥቀም የሚገባውን ያህል ያልጠቀመን ለዕድገታችንም ያላገዘን ከእውነታ ይልቅ በጊዜያዊ ክስተትና ችግር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ወይም ችግር-መር በመሆኑ ነው፡፡

እንደአንድ ሃገሩንና ባህሉን እንደሚወድ ዜጋ ስለችግሩና ስለ መንስኤው ብቻ ሳይሆን የዚህ ወርቃማ የትብብር ባህላችን ጉድለቶች ስለሚሞሉበትና በቀጣይ ዕሴቱ ለላቀ የህብረተሰብ ጥቅም ስለሚውልበት፣ ስለመፍትሔውም ያለኝን ሃሳብ እያካፈልኩ ልቀጥል፡፡"የዕድሜ ባለ ፀጋው" የትብብር ባህላችን የዕድሜውን ያህል በሥራውም ታላቅ እንዲሆን፣ እውነተኛ ፋይዳው በተግባር ተገልጦ ለሁለንተናዊ ዕድገትና ለጋራ ብልጽግና ጥቅም ላይ እንዲውል በዕድሜ ታላቅ መሆን የሚያስገኘውን ዋጋ ሳይረሱ ቁም ነገሩም ታላቅ እንዲሆን ዝቅ ብሎ በትህትና ቀና ብሎ በድፍረት መጠየቅ ይገባል፡፡

ይህንን ስናደርግ በማኅበራዊ ኑሯችን ውስጥ ሰፊውን ድርሻ እንደሚይዝ የሚታመነው የትብብር ባህላችን በተመለከተ ካስቆጠረው ረጅም ዕድሜ እና ሁለንተናዊ ዕድገትን ለማምጣት ካለው ከፍተኛ ፋይዳ አኳያ መጥቀም በሚገባው ልክ ጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑ አንዳች መሠረታዊ ችግር እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡የችግሩን መንስኤ ስንገነዘብ ደግሞ "የአንድን ችግር ዋነኛ መንስዔ ማወቅ ችግሩን ለመፍታት ግማሽ መንገድ እንደመጓዝ ነው" የሚለውን አባባል ትክክለኛነት አውቆ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበትን ዕድል እንፈጥራለን፡፡

በዚህ ረገድ በበኩሌ ለህሊናዬ ታምኜ፣ የሃገሬን ጥቅም መነሻና መድረሻ አድርጌ በአቅሜ በመረመርኩት መሠረት ወርቃማው የትብብር ባህላችን ከዘመናት የችግር-ተኮርነት የቆየ ልማዱ ተላቅቆ ለሃገርና ለሕዝብ የሚገባውን ያህል መጥቅም እንዲችል መፍትሔ ሆኖ ያገኘሁት ችግሩ መኖሩን አምኖ ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ ፈቃደኛ መሆንን ነው፡፡ለዚህም ባህል የሚሻሻል፣ የሚለወጥና የሚያድግ መሆኑን ዘንግቶ፣ ጎጂ መሆኑንም እንኳን እያወቀ እንደ ዘመኑ ጭፍን ብሔርተኞች "የእኔን ባህል ሊያጠፉ፣ የራሳቸውን ሊጭኑብኝ፣ ሊውጡኝ...ቅብጥርስ ..." ከሚል የውሸት ተቆርቋሪነትና አጉል ግብዝነት ወጥቶ በንጹሕ ሕሊና ጥቅምና ጉዳቱን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ይህን ለማድረግ ደግሞ ከሁሉም በላይ ከዕውቀትም የበለጠ ቅንነት ያስፈልጋል፡፡ነገሮችን በዕውቀትና በቅንነት ከመመርመር በተጨማሪ ዕምነት ትልቅ ኃይል አለውና ራስንና ሌሎችን ማመን፣ መታመንና እርስ በእርስ መተማመንን ከነገር ሁሉ በፊት ከሁሉ አስቀድመን ሁላችንም ልንመራበት፣ ልንኖርበትም ይገባናል፡፡ያኔ ከከንቱ የባህል ተቆርቋሪነትና ከጭፍን የባህል ጠባቂነት ተላቅቀን የማይጠቅምን ልማድ በመለወጥና በአዲስ በመተካት፣ ዕድሜ ጠገቡንና ወርቃማውን የትብብርና የማኅበራዊ ኑሮ ባህላችንን ጉድለቶች በማረምና በአዳዲስ ጠቃሚ ሃሳቦች በማጎልበት ለሚፈለገው ሁለንተናዊ ዕድገትን የማምጣት ዓላማ ማዋል እንችላለን፡፡

በዚህም ሰዎች ችግር ደርሶባቸው ከተጎዱ በኋላ ሳይሆን ገና ችግሩን የማሸነፍ አቅም ላይ እያሉ እገዛ የሚያገኙበትንና ከችግራቸው በቀላሉ መውጣት የሚችሉበትን አዲስ የማኅበራዊ እሴትና የትብብር ባህል መፍጠር እንችላለን፡፡ ለችግር ምላሽ መስጠት ላይ ያተኮረ ሳይሆን ሰዎች የችግር ሰለባ ከመሆናቸው በፊት አግዞ ወደ ዕድገት ማምጣት የሚያስችል፤ ችግር ተኮር ሳይሆን "ዕድገት-መር" የትብብር ባህልና ማኅበራዊ ዕሴት መገንባት እንችላለን፡፡

# ዓለም አቀፍ

## መርማሪ ቡድኑ በትራምፕ ላይ መጥሪያ እንዲቆረጥባቸው ወሰነ

ባለፈው ዓመት የአሜሪካ ምርጫን ተከትሎ የተነሳውን ነውጥ ለመመርመር በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት የተዋቀረውና 9 አባላት ያሉት መርማሪ ኮሚሽን ትናንት ምሽት ምርመራውን አጠናቋል። በዚህ የመጨረሻ ነው በተባለ የምርመራ ውጤት የመርማሪ ኮሚሽኑ አባላት በትራምፕ ላይ መጥሪያ እንዲቆረጥና ስለሆነው ነገር ሁሉ ቃል እንዲሰጡ በሙሉ ድምጽ ወስነዋል።

'ለፈጸመው ተግባር ምላሽ እንዲሰጥ ግድ ይላል' ብለዋል የሚሲሲፒው ዲሞክራት ወኪልና የመርማሪ ሸንጎው ሊቀ መንበር የሆኑት ቤኒ ቶምሰን። ትራምፕ መጥሪያውን ቸል ካሉ ክስና እስር ይጠብቃቸዋል። ይህ መርማሪ ሸንጎ የትራምፕ ነውጠኛ ደጋፊዎች ካፒቶል ሒልን ሰብረው ያደረሱትን ጥፋት ሲመረምር ድፍን ዓመት አልፎታል። በዚህ ሸንጎ ከ 9 አባላት ሁለቱ ሪፐብሊካን፣ 7ቱ ደግሞ ዲሞክራቶች ናቸው።

የመርማሪ ኮሚሽኑ አባላት ትራምፕ መጥሪያ ተቆርጦላቸው ቃላቸውን እንዲሰጡ የወሰኑት ያለምንም ተቃውሞና ድምጸ ተአቅቦ በሙሉ ድምጽ ነው። ለትራምፕ



መጥሪያ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ተቆርጦ ይሰጣቸዋል። የዋዮሚንግ ግዛትና የሪፐብሊካን ተወካይ እንዲሁም የመርማሪው ሸንጎ ምክትል የሆኑት ሊዝ ቼኒ እንዳሉት አሜሪካውያን ለዚሁ ሁሉ ጥፋት መሠረት ነው ከሚባለው ሰው ሐቁን የመስማት መብት አላቸው።

ከትናንት ወዲያ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማታ 2፡00 ሰዓት የጀመረው የመርማሪ ቡድኑ 9ኛ ሸንጎ የመጨረሻ ምርመራ ሰነዶችና የቪዲዮ ማስረጃዎች የቀረቡበት ነበር። በርካታ አስደንጋጭ የተባሉ መረጃዎችም ለሕዝብ በቀጥታ ቴሌቪዥን እንዲታዩ ሆነዋል።

በዚህ የቪዲዮ ማስረጃ በተለይ ካፒቶል ሒል ውስጥ የነበሩ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት፣ አፈ ጉባኤ ናንሲ ፒሎሲን ጨምሮ ከቢሮ ቢሮ ሲሯሯጡ፣ ለዶናልድ ትራምፕ የቅርብ ሰዎች ስልክ ሲደውሉና በከፍተኛ ጭንቅ ከነውጠኞቹ ለማምለጥ ሲሞክሩ የሚያሳዩ አዳዲስ ቪዲዮዎች ለሕዝብ ይፋ ተደርገዋል።

እንደራሴዎቹ በተለይ የጋዝ መከላከያ ጭንብል ሲለብሱና በነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ ሁኔታ ሆነው ሲንቀሳቀሱ የቪዲዮ ማስረጃዎች የቀረቡበት ነበር የትናንት በስቲያው ምስክርነት። ዶናልድ ትራምፕ ይህን የመርማሪ ኮሚሽኑን ውሳኔ ፖለቲካዊ ብለውታል። 'አሜሪካውያን በዲሞክራቶች ቀሽም አመራር በተማረሩበት ወቅት የፖለቲካ ነጥብ ለማስቆጠር የተቀናበረ ነው፤ የእኔን ምስክርነት ከፈለጉ ለምን በምርመራው መጀመሪያ አልጠየቁኝም?' ብለዋል ትራምፕ።

ዶናልድ ትራምፕ በ2024 በድጋሚ ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር ፍላጎት እንዳላቸው ፍንጭ ሰጥተዋል። አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይህ የምርመራ ቡድኑ ውሳኔ ከወር በኋላ ከሳምንታት በኋላ የሚደረገው 'ሚድተርም' ምርጫ ላይ ዲሞክራቶች ሊደርስባቸው የሚችለውን ሽንፈት በመስጋት መራጮችን ለማማለል ሆን ተብሎ የተደረገ ነው ይላሉ።

ይህ በሕዝብ እንደራሴዎች የተቋቋመው መርማሪ ቡድን ሙሉ የምርመራ ውጤቱን ከሁለት ወራት በኋላ ይፋ ያደርጋል። ለዓመት ያህል በዘለቀው ምርመራ የአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን፣ የደህንነት ሰዎችን፣ ሚኒስትሮችን፣ የዶናልድ ትራምፕ የቀድሞ ረዳቶችን፣ የጸጥታ አካላትን ጨምሮ ከአንድ ሺህ አሜሪካውያን በላይ ምስክርነት ሰምቶ መርምሯል።

በዚህ መርማሪ ቡድን ሁለቱ ብቸኛ የሪፐብሊካን ፓርቲ አባል የሆኑት ሊዝ ቼኒ እና አዳም ኪዚንግር ትናንት ትራምፕ የምስክርነት ማዘዣ ተቆርጦባቸው ቃላቸውን እንዲሰጡ ድምጽ በመስጠታቸው በፓርቲያቸው ዘንድ ከፍተኛ ውግዘት ደርሶባቸዋል። በባለፈው ዓመት የትራምፕ ነውጠኛ ደጋፊዎች የካፒቶል ሒል አመጽ 850 አሜሪካውያን ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ተመድ ለ54 ታዳጊ የዓለማችን ሀገራት የእዳ ስረዛ እንዲደረግላቸው ጠየቀ

የእዳ ስረዛው ለታዳጊ ሀገራቱ ካልተደረገ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ወደ አስከፊ ድህነት ይወርዳሉ ተብሏል፡፡የእዳ ስረዛ እንዲደረግላቸው ከተጠየቁት መካከል 25ቱ የአፍሪካ ሀገራት ናቸው፡፡የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለ54 ታዳጊ የዓለማችን ሀገራት የእዳ ስረዛ እንዲደረግላቸው ጠየቀ።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር የሆነው የልማት ድርጅት ወይም ዩኤንዲፒ በመባል የሚጠራው ተቋም የገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ለታዳጊ ሀገራት ባበደሯቸው ብድር ዙሪያ ሪፖርት አውጥቷል። ድርጅቱ በሪፖርቱ እንዳመለከተው ለ54 የዓለማችን ታዳጊ ሀገራት የብድር ስረዛ እና ተጨማሪ የመክፈያ ጊዜ ወይም እፎይታ እንዲሰጣቸው ጠይቋል።

የብድር ስረዛ እንዲደረግላቸው ከተጠየቁት የዓለማችን ሀገራት መካከል 25ቱ የአፍሪካ ሀገራት እንደሆኑ ተቋሙ በድረገጹ ባወጣው ሪፖርት ላይ አስታውቋል።ድርጅቱ አክሎም ለበለጸጉ ሀገራት እና ለአበዳሪ ተቋማት ትንሽ ነገር ቢያደርጉ ለታዳጊ ሀገራቱ ግን ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት አስታውቋል።

አበዳሪ ተቋማት እና ሀገራት ለታዳጊ ሀገራት የብድር ስረዛ እና እፎይታ ካልሰጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ወደ አስከፊ ድህነት ሊወርዱ እንደሚችሉም ተገልጿል።እንዲሁም አበዳሪ ተቋማት እና ሀገራት ብድሮቻቸውን ለድህነት ቅነሳ ሥራዎች እንዲያውሉ ሊያበረታቱ ይገባል ሲልም ድርጅቱ አስታውቋል። ኮሮና ቫይረስ፣ ግጭቶች እና የአየር ንብረት ለውጥ በርካታ የዓለማችን ሀገራትን የግድ ቢሆንም ታዳጊ ሀገራት ግን የበለጠ ተጎጂ እንደሆኑም ተገልጿል።



የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት መከሰት በማገገም ላይ የነበረውን የዓለም ኢኮኖሚ ወደ ባሰ ጉዳት በመዳረግ ላይ እንደሆነ የገለጸው ድርጅቱ ታዳጊ ሀገራት በነዳጅ እና ምግብ ዋጋ መጨመር ምክንያት የበለጠ ተጎጂ እንደሆኑም መገለጹን አልዐይን ዘግቧል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ሁለቱ ድምጾች

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ድምጽ እንዴት ሊቆጠር ይችላል? ምላሹ አስቸጋሪ ይመስላል። ለዛሬው ተቆጥረው የሚገኙ ሁለት ድምጾችን እንመለከታለን። የምናብ ታሪካችን "ሁለቱ ሰዎች" በማለት ይጀምራል። ሁለቱ ሰዎች አብረው ይራመዳሉ፤ በተመሳሳይ ፍጥነት፤ በተመሳሳይ ዝግታ፤ በተመሳሳይ ቁመት፤ ነገርግን በተለያየ እርቀት ።አንዱ ሲቀድም ሌላው ይከተላል። አንዱ ዋና ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ጥላ ሆኖ ይታያል። ጥላውም ዋናውም መሬቱ ላይ እኩል ሲሄዱ ይታያሉ፤ ሁለት ሰዎች፤ አንዱ ሰው በሁለትነት ።

ልጆቹ እንደወትሯቸው ግለሰቡን እያዩ ይጠቋቆማሉ። ግለሰቡ የአእምሮ ህመምተኛ መሆኑን ማህበረሰቡ ደምድሞ "እብዱ" እያለ የሚጠራው ። በሰፈሩ ውስጥ ያለውን ግሳንግስ ሁሉ ተሸክሜ ካልዞርኩ የሚል ። እናቱ ጋር ሲደርስ ግን የተለመደውን መልእክት በትኩረት የሚያስተላልፍ፤ የሁሌ መልእክቱን።

እናቱን በጥሞና ትኩር ብሎ ያያቸውና "እማዬ ሌላስ የምሸከመው ነገር ይኖር ይሆን?" ይላል ።እናቱም "ልጄ የተሸከምከው ከበቂ በላይ ነው፤ እባክህ ሸክምህን አራግፈው።" ይሉታል ።የእናቱን ምላሽ ሳይጠብቅ ፈጥኖ ወደ መንገድ ይወጣና ሌላ ሸክምን ይፈልጋል ። ተመሳሳይ ጥያቄ፤ የእናትም የዘወትር ተመሳሳይ መልስ። ቀኑን ሙሉ ሰፈሩን ሲያስስ የሚሸከመውን ሲመርጥ፤ የተሸከመውን ይዞ ጉዞ ሲያደርግ ይውልና አንዱ ጋር ይተኛል ። በሃያ አራት ሰዓት አንድ ጊዜ ግን እናቱ ካሉበት ቤት መጥቶ ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርቦ፤ የተሰጠውን ምላሽ ሳይሰማ በመጣበት ፍጥነት ይመለሳል ።

ሌላው የዘወትር ተግባሩ የገበያ መሃል ንግግሩ ነው። በአካባቢው በሚቆመው በሰኞ ገበያ ቀን ድንገት ይመጣና የሚሸከመውን ተሸክሞ በገበያው መሃል ቆሞ "ሸክሙ የእኔ ብቻ ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል፤ ሸክሙ የሁለታችንም ነው"ይላል ።እብድ ተብሎ ስም የወጣለት ሰው ሊቀርበው የማይፈቅደው አይነት ሰው ነውና "ሁለታችሁ" ማን እና ማን ናችሁ ብሎ የሚጠይቀው ሰው ግን የለም ።አንድ ቀን ግን ከገበያተኞቹ መካከል አንድ ሰው ቀርቦ "ሁለታችሁ ግን ማን እና ማን ናችሁ?" ሲል ጠየቀ፤ ምላሽ ሳይሰጠው አፍጥጦበትም ብቻ ሄዳ ።

ጥያቄ አቅራቢ ገበያተኛው ወደ ውስጡ ሲያዳምጥ በእርሱ ውስጥ ሸክም ተሸክመው የሚኖሩት ሁለቱ ሰዎች ታዩት፤ በሁለት አይነት ድምጽ ዘወትር የሚገኙቱ። ግለሰቡ ራሱን ሲያይ አንዳንዴ ራሱ ሁለት ሰው ሆኖ ያገኘዋል፤ ኸረ ለብዙ ጊዜ እንጂ ።በአንድ ሰው ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ።ተራ በተራ ሁለቱ የሚያወሩ፤ አንዳንዴ የሚጨቃጨቁ ግፋ ሲልም የሚጣሉ፤ የሚኮራረፉም፤ ሁለት ሰዎች ።እኒህን ሁለት ሰዎች በአግባቡ ማድመጥ መቻል አስፈላጊ እንደሆነ ገበያተኛው እያሰበ ወደ ገበያው ተመለሰ ።ወደ ተለመደው የገበያ ወግ፤ ወደ ጭቅጭቁ፤ የገዢና የሻጭ ጭቅጭቅ ።

የገበያ ውበቱ የገዢና ሻጭ ጭቅጭቅ ሆኖ እንዲሳል ያደረገ ጭቅጭቅ ዘወትር ይደረጋል ።የተለመደ መንገድ ነውና ጭቅጭቁ ቀጥሎ ሁሉም እንደ መሻቱ ገበያውን ፈጽሞ ይመለሳል ።ገበያው የሰመረለት አትርፎ ወደ ቤቱ ሲመለስ፤ ያልሰመረለት ከስሮም ሊወጣ ይችላል። እያንዳንዱ የገበያ ቀን ትርፍና ኪሳራ አለው፤ አንዳንዴም በመሰረቅም ሆነ በሌላ ሁኔታም ታጅቦ የሚውል ሰራተኛውም ሆነ ሌባውም የሚሰማሩበት ።

ገበያተኛው ጠያቂ ከገበያ ውስጥ ገበያ ተኮር ጭቅጭቅ በላይ አሻግሮ ያደመጠው እያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ ስላለው ጭቅጭቅ ነበር ።የማይሰማው፤ በለሆሳስ የሚሆነው፤ መነሻውም ሆነ መድረሻው ግለሰቡ ውስጥ የሆነው፤ በአግባቡ ካልተያዘ ጨርቅ አስጥሎ ወደ አደባባይ ሊያስወጣ ስለሚያስችለው የአንዱ ሰው ሁለትነት የሚያሳየው ጭቅጭቅ ።

አሽናፊው ማን እንደሆነ የማይታወቀው በመንታ መንገድ ውስጥ የሚፈጠረው ጭቅጭቅ ህይወትን ባልተገባ አቅጣጫ ሊመራ መቻሉ ግን እሙን ነው። ምነው ያቺን ቀን የሚሉ ሰዎች ለአፍታም

> ለአሁኑ ትውልድ የሚሆን ልማት መጪውን ትውልድ የሚጎዳ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግንም ይጠይቃል።ነገን ታሳቢ አድርጎ ጉዞ የሚያደርገው ሰው ወደ ውጤት እንዲደርስ ልማት ውስጥ ሲኖር የሚገባውን ዋጋ መክፈል ተረድቶ ለዋጋ መክፈሉ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል

ቢሆን በውስጣቸው ተፈጥሮ የነበረውን ጭቅጭቅ አይረሱትም። በቀጣይም ቀን በውስጣቸው ተሸክመው የሚሄዱት የትናንቱ ህይወታቸው ተጽእኖው ቀላል አይደለም። የቆጠርናቸውን ሁለት ድምጾች በመመልከት ውስጥ ሁሉም ስለተሸከመው ሸክም እንመልከት ።

አንደኛው ድምጽ፤ በትናንት ውስጥ የሚገኘው

አንተ ውስጥ የትናንት ሰው አለ፤ አንቺ ውስጥ ትናንት ላይ የሚኖር ሰው አለ፤ በሁሉም ሰው ውስጥ ከትናንት የተነሳ የተፈጠረ ሰው አለ፤ ድምጽ የሆነ ።በጊዜ ውስጥ እንደ ህጻናት መሆን አንችልም ።ቀን በቀን እንደ ህጻን ከመሆን እንደ አዋቂ እንሆናለን ።እንደ አዋቂ በመሆን ውስጥ ትርፍም እንዳለው ኪሳራም አለው ።ህይወት እንደ ህጻን መሆን በምትፈልግበት ነገር ላይ እንደ ህጻን መሆን ሲሳነን እናገኛለን ።ለምን?ምክንያቱም በትናንት ጉዞ ውስጥ የተፈጠረ ድምጽ እንደ አዋቂ እንድንቀሳቀስ ከውስጣችን ሆኖ ስለሚነግረን ።

ትናንት አንድን ነገር ሞክሮ ያልተሳካለት ሰው፤ ዛሬ አንድን ነገር ለመሞከር ሲያስብ ምን ሊያስብ ይችላል? ትናንት በሙሉ ነጻነት ቃላትን እየተጠቀመ ሲናገር የነበረ፤ በነጻነት በመናገሩ ዋጋን ከከፈለ በኋላ ዛሬም በዚያው መንገድ ሊገኝ ይችል ይሆን? ትናንት ከሰዎች ጋር በግልጽነት በመቅረብ ዋጋን የከፈለ ሰው ዛሬ በተመሳሳይ መንገድ ላይ የሚገኝ ይሆን? ምላሹ ለአንባቢው ቢተው ከአንባቢው ምላሽ ጋር ስምም የመሆን እድላችን ሰፊ ነው።

በትናንት ውስጥ ያለፍንበት ነገር በዛሬ ላይ ጥላ ማጥላቱ አይቀሬ ነው ።ይህን ሰው እንዴት እንያዘው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ህይወትን በጥበብ ለመምራት ወሳኝነት አለው ።በትናንት እስረኛ ለሆኑ ሰዎች መፍትሔው አንድ የሚዋጥ ኪኒን ነው ቢባል ኪኒኑን ለማግኘት የሚሰለፈው ሰው ሰልፍ የትየለሌ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ።

በትናንት ውስጥ ሆኖ የሚመክረው በውስጣችን ውስጥ ያለው አንደኛው ድምጽ ሌላኛውን ሰው የሚገነባ እንጂ የሚያፈርስ እንዳይሆን ማሰብ ያስፈልጋል ። የሰው ልጅ እድገት ውስጥ ዘወትር ቢያልፍ ይመርጣል። ባለበት ቆሞ መቅረትን የሚፈልግ ማንም የለምና። እድገት ደግሞ ወደፊት መራመድን ይጠይቃል። ወደፊት መራመድ ደግሞ በትናንት በመቆዘም ውስጥ አይሆንም፤ በተግባር መንቀሳቀስ በመቻል ውስጥ እንጂ ።

ያለፍንበት ትናንት ትምህርት ቤት ሆኖን የምንራመድበት እንጂ ወደ ኋላ የምንልበት ከእድገት የምንቀርበት እንዳይሆን ማሰብ ይኖርብናል ።ወደፊት መራመድ ነጻ ሆኖ ማሰብን፤ ያሰቡትን ወደ እቅድ መቀየርን፤ እቅድ ያደረጉትን መተግበር እንደሚችሉ መረዳት መያዝን፤ ወዘተ ይጠይቃል ።በትናንት ውስጥ በመቆዘም፤ እንደማይሆንልን በማሰብ፤ እጅና እግርን አጣጥፎ በመቀመጥ ውስጥ የትናንት ድምጽ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በትናንት ውስጥ ሆኖ ተስፋ አስቆራጭ መንፈስ እንደሚዋጋን ሁሉ በትናንት ውስጥ ትእቢትም ይዋጋናል። በትናንት ውስጥ አልጋ በአልጋ የሆነላቸው ሰዎች በውስጣቸው ሁሉንም ነገር እንዳሻቸው ማድረግ እንደሚችሉ የሚያስቡ ናቸው ።እንዳሻቸው ማድረግ መቻላቸው ከህግም ከሞራልም ውጪ እንዲኖሩ የሚገፋፉቸው ሆኖ የትእቢት እስረኛ ይሆናሉ ።የዛሬው ሰው በትናንቱ ሰው አማካኝነት መራመድን መፍራት እና በትእቢት መራመድ መፈለግን ሊያዳብር ይችላል። ትናንት ውልድ የሆነውን ድምጽ መግራት መቻል የጥበብ መንገድ ነው፤ በማይለወጠው ትና ንት በመልካም ሊሰራ የሚገባውን ዛሬን አለማበላሸት ።

**ሁለተኛው ሰው፤**

ወደ ነገ መራመድ የሚፈልገው በነገ ውስጥ ማድረግ የማንፈልገው ምን አለ ።ብዙ ነገር ገና ከፊታችን የሚሆን እንደሆነ ቆጥረን ትኩረታችንን ከፊታችን አድርገን እንኖራለን ።ወደ ፊታችን እንመለከታለን፤ ከፊታችን ምላሽን ለማግኘት እንፈልጋለን ።ያላገበው ሰው ከፊቱ ትዳርን ያስባል፤ ልጆች ሲወልድና ሲያሳድግ



ወዘተ ።በሥራ ላይ ያለ ሰው ወደፊት ስለሚሰራበት ትልቅ የስራ ቦታ በማሰብ ትኩረቱን በነገው ውስጥ አድርጎ ጉዞን ያደርጋል ።ስራን በመፈለግ ላይ ያለው የሚፈልገው አይነት ስራ ለማግኘት ጥረት በማድረግ ውስጥ እንቅስቃሴ ያደርጋል ።በነገ ውስጥ ሞትም አለ ።ከሞት ባሻገር ያለውን ህይወት የሃይማኖት መንገድ በሚለው በኩል ለማግኘት ሁሉም በየመንገዱ ይራመዳል ።በነገ ውስጥ እድገት እንዲሁም ሞትም አለ ። ሞትን በመፍራት፤ በተቻለው መጠን ከሞት ለማምለጥ ጥረት በማድረግ እድገትን ለማግኘት የሰው ልጅ ስራው ነው ።ሁሉም በየአቅጣጫው ያለው ስምሪት እድገትን ለማምጣትና ሞትን ለመሸሽ ነው ።የሞት ሽሽቱ በህክምና መስጫ ቦታዎች ላይ ሰዎች እንዲገኙ ያደርጋቸዋል፤ ባለመድህኒትነት ይፍለጋል ።እድገትን ለማምጣት ደግሞ ተማሪው በትምህርት ቦታው፤ ሠራተኛው በስራው ቦታ ይገኛል። ሁሉም በየፈርጁ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ድምር ውጤት የምድራችንን ህይወት ይህን ያስመስለዋል።

ሁለተኛው ሰው ወደፊት ከመቆም ራሱን መልሶ ጉዞ ማድረግ ይፈልጋል። ከጉዞው የሚያደናቅፈው አይፈልግም። ጉዞውን ዳር ማድረስ ይፈልጋል ።ጉዞው ላይ እንቅፋት እንዳይኖር ይፈልጋል። እንቅፋት ሲገጥመው ይበሳጫል፤ እንቅፋቱን ገለል ለማድረግ በህግም በሌላም መንገድ ይሄዳል። በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ወደ አመራር የሚመጡ ግለሰቦች በመንገዳቸው ላይ የሚመጣውን በብልጠትም ሆነ በጡጫ ወደ ጎን በማድረግ መድረስ የፈለጉበት ጋር ለመድረስ ጉዞ የሚያደርጉ መሆኑን መጽሐፍት ይነግሩናል ። በሌሎች ሀገሮችም ተመሳሳዩ መንገድ በብዙ የተተገበረ ነው። ከስልጣኔ ወደ ኋላ በቀሩት ሀገራት ደግሞ አሁንም መተግበሩ የጨመረ ነው። ወደ ግለሰብም ጉዳዩን ስናመጣው ነገ ውስጥ ማየት ከሚፈለገው አንጻር አንዱ በሌላው ላይ መጨካከንም ይስተዋላል ።ሃሳብን በመነጋገር ለመፍታት ጥረት ከማድረግ ጡጫን መጨመር አዲስ ነገር አይደለም፤ እስከ ህይወት ማጥፋት።

ዛሬ በውስጣችን ያለውን በነገ ውስጥ እድገትን ማምጣት የሚፈልገውን ሰው በጥንቃቄ እንድንመለከተው ያስፈልጋል። በውስጣችን ያለው ሰው ወደ ውጤቱ ለመድረስ እየተከተለው ያለው ምን አይነት መንገድ መሆኑን መመርመር አለብን። ወደ ውጤት የሚያደርሰን መንገድ ላይ ለመገኘት ራስን መግዛት አስፈላጊው ነገር ነው። ወደ እድገት፤ ወደ ውጤት፤ ወደ መሳካት፤ ወደ ህልምን መጨበጥ ወዘተ ላይ መድረስ የሚፈልገው ውስጣችን ያለው ሰው ከትናንቱ ሰው ጋር የሚያደርገውን ግጭት በአግባቡ መመርመር፤ ምርመራውን ወደ ውጤት ማድረስ እንዲቻል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግን ይፈልጋል ። ልማት የሚያስከፍለው ዋጋ እንዳለ የልማት ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለአሁኑ ትውልድ የሚሆን ልማት መጪውን ትውልድ የሚጎዳ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግንም ይጠይቃል። ነገን ታሳቢ አድርጎ ጉዞ የሚያደርገው ሰው ወደ ውጤት እንዲደርስ ልማት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ዋጋ መክፈል ተረድቶ ለዋጋ መክፈሉ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል ።

# ስኬት

# ብርሃን በማዳረስ እየተጋች ያለችው ወጣት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የሰው ልጅ በሕይወት መቆየት እንዲችል ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያና ልብስ የግድ ቢሆኑም፣ በተሻለ ሁኔታ ለማምረት፣ ኑሮን ቀላልና የተቀላጠፈ ለማድረግ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልጋል ።ኢነርጂ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል ለሰው ልጆች ብርሃን ከመስጠት ባሻገር ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታዎችን ያበረክታል ።

ከተማ ተወልዶ በማደግ ከሚገኙ የተለያዩ ጥቅሞች መካከል የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት አንዱ ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል ብርሃን ከመስጠት ባለፈ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን ይሰጣል ።በተለይም በከተሞች አካባቢ የእያንዳንዱ ሰው እንቅስቃሴ በኤሌክትሪክ ላይ ጥገኛ ከመሆኑ የተነሳ መብራት ሲጠፋ ሁሉም ነገር ቀጥ ይላል ቢባል ማጋነን አይሆንም ።

የኤሌክትሪክ ኃይል ፋይዳ ይህን ያህል ቢሆንም ታዲያ አብዛኞቹ በገጠር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የኤሌክትሪክ ኃይል አያገኙም፤ ከጨለማ የሚታደጋቸውን ብርሃን የሚያገኙበት መንገድ ኋላቀር ነው ።ዛሬም ድረስ በኩራዝ ጭስ፣ በማገዶ ጨለማውን ይገፋል፤ አጠቃላይ ሕይወቱንም እጅግ አስቸጋሪ፣ ፈታኝ፣ አድካሚና አሰልቺ በሆነ መንገድ እየመራ ይገኛል ።

የሰዎችን ሕይወት ቀላልና ቀልጣፋ በማድረግ ትልቅ ድርሻ ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል በመላው ሀገሪቱ ተደራሽ መሆን ባለመቻሉ መንግሥት በርካታ የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጮች ተግባራዊ እንዲሆኑ እየሠራ ነው ።በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ለመታደግ አቅዷል። ከንፋስ ኃይል በማመንጨት ላይም ይገኛል ።እንዲያም ሆኖ ፍላጎቱና አቅርቦቱ የሰማይና የምድር ያህል ነው፤ የተለያዩ የኃይል አማራጮችን መጠቀም የግድ ሆኗል። የጸሐይ ኃይልን በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ውስጥ ከተገባም ቆይቷል፡፡

ይሄ ሁሉ ተደርጎም ዛሬም ድረስ የኃይል አማራጭ የሆነውን ሶላር ማግኘት ያልቻሉ ኢትዮጵያውያን በርካታ ናቸው ።እነዚህ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለመድረስ ታዲያ መንግሥትን ጨምሮ የተለያዩ የግልና የውጭ ድርጅቶች ጭምር በርካታ ጥረቶችን አድርገዋል ።እንዲያም ሆኖ ታዲያ ተደራሽነቱ ገና ይቀራል ።

የሶላር ኢነርጂ ማመንጨት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብና በመገጣጠም ሥራ በርካታ ድርጅቶችና ዜጎች ተሰማርተዋል፤ ይህም ወደ ሀገሪቱ ገጠር አካባቢዎች ዘልቆ ገብቷል ።

የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎች አማራጭ የሆነውን ሶላር ተደራሽ በማድረግ፤ ጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎች ብርሃን መሆን ከቻሉ ድርጅቶች መካከል ግሪን ሲን /Green Scene/ የተባለው ድርጅት አንዱ ነው ።የድርጅቱ መሥራችና ማናጀር ረቂቅ በቀለ ትባላለች ።

ረቂቅ ተወልዳ ባደገችበት አዲስ አበባ ከተማ መብራት የማግኘት ዕድሉን ብታገኝም፤ ጭርሱኑ መብራት ምን እንደሆነ የማያውቁ ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ የሚል ግምት ግን አልነበራትም ።የከፍተኛ ትምህርቷን አጠናቃ ወደ ሥራ ዓለም በተቀላቀለችበት አጋጣሚ ይህንን እውነት ተረዳች ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው ረቂቅ፤ በኤሌክትሪካል ዲዛይን ለአንድ ዓመት ስትሠራ አሁን በደረሰችበት ደረጃ የኃይል አማራጭ የሆነውን ሶላር አከፋፍላለሁ የሚል ሀሳብ አልነበራትም ።ይሁንና ኢነርጂ ለሰው ልጆች የቱን ያህል አስፈላጊና የግድ እንደሆነ ግን በሚገባ መረዳት ችላለች ።

የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ ለዛሬ ሥራዋ መሠረት የሆነውን አንድ የሶላር ኩባንያ ተቀላቀለች ።ኩባንያው በአንድ የገጠር ወረዳ ሶላር ለማስገባት ለሚሠራው ሥራ ሠራተኞችን እያፈላለገ መሆኑን ትረዳለች ።ረቂቅ የኩባንያው አንዷ ሠራተኛ ሆና ተቀላቀለች ።

የመጀመሪያ ሥራዋም መብራት ባለውና ሁሉ ነገር በተሟላበት ቢሮ ውስጥ መሥራት ሳይሆን መብራት ከማያውቃት ገጠር ውስጥ ገብቶ ሶላር ማስገባት የመጀመሪያ ሥራዋ እንደነበር ታስታውሳለች ።

አካባቢው እጅግ ገጠራማና መብራት የሌለበት ነው፤ በወቅቱ ሶላሩ ይገባ የነበረው ለጤና ጣቢያ ብቻ ነበር። «ሥራውን ሠርተን እስክንጨርስ በቦታው ለአሥራ




የድርጅቱ መሥራችና ማናጀር ረቂቅ በቀለ

አምስትና ከዛም ላለፉ ቀናት መቆየት የግድ ነበርና በቆይታዬ ብዙ ነገሮችን ተማርኩ» የምትለው ረቂቅ፤ በዚሁ የሥራ አጋጣሚዋ የመብራትን ጥቅም በጥልቀት መረዳት ቻለች፡፡

ሶላር ለመግጠም የሄደችበት አካባቢ እጅግ የተዋበና በተፈጥሮ የታደለ ለምለም ነው፤ የግብርና ምርት በዓይነት በዓይነቱ ይገኛል ።ሁሉም ነገር ያላቸው እነዚህ ነዋሪዎች ግን መብራት አያውቁም ።የጤና ባለሙያዎች በምሽት ለሚመጣ ታካሚ የእጅ ስልኮቻቸውን በአፋቸው በመያዝ እንዲሁም በኩራዝ አገልግሎት ለመስጠት በብዙ ሲቸገሩ አስተውላለች ።በዚህ መጠን ለሚቸገር ማኅበረሰብ መፍትሔ መሆን መቻል ደግሞ የሚሰጠውን ደስታ መገመት አያስቸግርምና ረቂቅም ለዚሁ ትርጉም ላለው ሥራ ተሰጠች፡፡

ከቀጠራት ደርጅት ጋር ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ሶላር የምታስገባው ረቂቅ፤ በዚሁ አጋጣሚ የተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ከማወቅ ባለፈ ሥራውን በስፋት ለመሥራት ምቹ አጋጣሚን ተፈጠረላት ።ይህን አጋጣሚ ተጠቅማ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት በግሏ ኢነርጂ የማከፋፈል ሥራዋን «ሀ» ብላ ጀመረች ።በወቅቱ የፋይናንስ እጥረት ቢገጥማትም ለሥራው ከፍተኛ ፍላጎት፣ ተነሳሽነትና ቁጭት ስለነበራት ችግሩ አልታያትም ።ምክንያቱም መሰል የግል ድርጅቶች ካልተበራከቱ ችግሩን መፍታት እንደማይቻል ተረድታለችና ።

በተለያዩ የሀገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች በነበራት እንቅስቃሴ በተለያየ ጊዜና ቦታ በኩራዝ ምክንያት ልጆች ስለመቃጠላቸው፣ ቤት ንብረት ስለመውደሙና ሌሎችም በርካታ አደጋዎች ስለመድረሳቸው ከማኅበረሰቡ ተረድታለች ።ታዲያ የኤሌክትሪክ አማራጭ የሆነውን ሶላር እንዲህ ላለው ማኅበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ ከራሷ ጋር ተሸቀዳደመች ።ግሪን ሲን የተባለ ድርጅት በመክፈት ከውጭ ሀገራት ሶላር እያስመጣች ማከፋፈል ጀመረች። በሥራዋም ትርጉም ያለው ውጤት ተመለከተች። ለብዙዎች ብርሃን ለመስጠት ምክንያት መሆን በመቻሏ እርካታዋና ደስታዋ እየበዛ መጡ ።

ከውጭ ሀገራት የተለያዩ የሶላር አይነቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለብዙዎች ብርሃን መሆን የቻለችው ረቂቅ፤ 90 በመቶ የሚሆነው ዕቃ ከአገረ ቻይና እንደሚገባ ነው ያጫወተችን ።ሥራው ከፍተኛ ፋይናንስ የሚፈልግ መሆኑን ጠቅሳ፣ በእዚህ ላይ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት ድርጅቱ ከፍተኛ ችግር ገጥሞት እንደነበር ታስታውሳለች ።ያም ቢሆን ግን ሶላሩን ከማከፋፈል በተጨማሪ በዘርፉ አዳዲስ ሃሳቦችን በማምጣት፣ በመወዳደርና አሸናፊ በመሆን ተጠቃሚ ሆና ማንሰራራት ችላለች ።

«ኤሌክትሪክ ለሁሉም ነገር ትልቅ አማራጭ ነው» የምትለው ረቂቅ፤ በተለይም አርሶ አደሩ የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት ካልቻለ ሕይወቱን መለወጥ አይችልም። ኤሌክትሪክ በቤት ውስጥ ብርሃን ከመስጠትና ምግብ ከማብሰል ባለፈ የግብርና ሥራውን ያቀላጥፍበታል ትላለች ። ለአብነትም አነስተኛ የግብርና ሥራቸውን በማቀላጠፍ በሶላር ውሃ ከጉድጓድ አውጥተው እንዲያመርቱ፣ ምርቶቻቸውን በቀላሉ መሰብሰብና ማከማቸት እንዲችሉ ኤሌክትሪክ ከአማራጭም ባለፈ የግድ ነው በማለት ታብራራለች ።

በአሁኑ ወቅት 56 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ያላገኘ መሆኑን በመጥቀስ፣ በዚህም የተነሳ በርካታ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ይደርስበታል ትላለች ። ከዚህም ባለፈ የኃይል አማራጭ የሆነውን ሶላር በመጠቀም በኩል በተለይም ነጋዴው ያለዕውቀት በመሸጡ የሚፈጠር ችግር እንዳለ ነው ታነሳለች ።

የእሷ ድርጅትና መሰሎቿ ግን ከመንግሥት ጋር በመሆን እንደሚሠሩ ትናገራለች ። በአሁኑ ወቅት የሶላር ኢነርጂን ቁሳቁስ እያከፋፈለች ያለችው ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብና ከሲዳማ ክልሎች ጋር ስምምነት በመፍጠር ነው ።የእሷና መሰል ድርጅቶች የሶላሩን ጥቅምና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ በማስረዳት ተደራሽ ያደርጋሉ ።ሕጋዊ ሆነው በመሥራታቸውም ቢበላሽ እንኳ ሄደው ይጠግናሉ፡፡

ደንበኞቿ ሙሉ ለሙሉ መብራት የማያውቁ በመሆናቸው ቤታቸው በብርሃን ሲሞላ እጅግ ደስተኞች ሲሆኑ መመልከት የዓመታት ሥራዋ ሆኗል ።ክፍያውን በተመለከተም ጥሬ ከፍለው የሶላር መሣሪያውን ከመግዛት በተጨማሪ በአቅራቢያቸው ከሚገኙ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር በረጅም ጊዜ ክፍያ እንዲከፍሉ ሁኔታዎች አመቻችታላቸዋለች ።ሦስተኛው የክፍያ አማራጭ ደግሞ እየተጠቀሙ መክፈል ነው፤ ይህም መቆጣጠሪያ ሶፍትዌር በማበልጸግ እየተጠቀሙ መክፈል የሚችሉበት መንገድ ተፈጥሯል ።ተጠቅመው ገንዘቡ ሲያልቅ መብራቱ ይጠፋል ።በጠፋበት ፍጥነትም ጨለማውን አይፈልጉምና ክፍያቸውን ይፈጽማሉ ።

የሶላር አይነቶቹ የተለያየ አገልግሎት ያላቸው ሲሆን፣ አርሶ አደሩ እንደየአቅሙና ፍላጎቱ ይገዛል ።አነስተኛ ከሆነው አንስቶ ረጃጅም መስመሮች ያላቸውና በተለያዩ ክፍሎች መራዘም የሚችሉና የእጅ ስልኮችን ቻርጅ ማድረግም የሚያስችሉም አሉ ።ከዚህ በተጨማሪም ኢነርጂ በማግኘታቸው ቴክኖሎጂን መጠቀም ይችላሉ ።ለአብነትም በእጅ ስልኮቻቸው አማካኝነት በገቡት ውል መሠረት ክፍያ የሚፈጽሙ በርካቶች ናቸው ።የሶላር ኢነርጂ በመጠቀም የውሃ ፓምፕ እንዲሠራ ማድረግም ሌላው ቴክኖሎጂ ሆኗል፡፡

ኑሮውን በጨለማ ውስጥ ላደረገ ማኅበረሰብ ጨለማውን መግፈፊያ ብርሃን ከመስጠት ባለፈ የተለያዩ አገልግሎቶችን በሶላር ኢነርጂ እንዲጠቀም እየሠራች ያለችው ረቂቅ፣ የዛሬ ስድስት ዓመት ወደ ሥራው ስትገባ 20 ሺ ብር መነሻ ካፒታልና አንድ ጓደኛዋን በመያዝ ነበር። በአሁኑ ወቅት ካፒታሏ 13 ሚሊዮን ብር ደርሷል፤ ለ18 ሰዎችም የሥራ ዕድል ፈጥራለች ።

በስድስት ዓመት የሥራ ጉዞዋም ሱማሌ ክልልና ቤኒሻንጉል ጉሙዝን ጨምሮ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአማራና በሲዳማ ክልሎች 40 ሺ ለሚደርሱ ግለሰቦች አገልግሎቱን መስጠት ችላለች ።በእዚህ አገልግሎትም ዘጠኝ ሺ የሚደርሱ የተለያየ መጠን ያላቸውን ሶላሮች ተደራሽ አድርጋለች ።

«መንግሥት የኤሌክትሪክ ኃይልን በመላው የሀገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ ባለመቻሉ፤ የግል ዘርፉ ደግሞ በመዘግየቱ ምክንያት አብዛኛው ማኅበረሰብ ጨለማ ውስጥ ሊሆን ተገዷል፤ ስለዚህ መፍጠን ያስፈልጋል» የምትለው ረቂቅ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ባልደረሰበት ቦታ ሁሉ መድረስ ለነገ የሚተው ሥራ አይደለም፤ እጅግ አስቸኳይና አንገብጋቢ ነው ትላለች፡፡

ለዚህም መፍትሔው ቀላል መሆኑን ነው የምትጠቁመው፤ የኃይል አማራጭ የሆነውን የሶላር ኢነርጂ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች አሉ ።እነዚህን ወጣቶች ደግሞ ትልቅ ኃይል አላቸውና ምን እና ለምን እንደሚሠሩ የሚያውቁ በመሆናቸው እነሱን በመጠቀም ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ያላትን እምነት አካፍላናለች፡፡

በየአካባቢው ግዙፍ የሶላር ፓኔሎችን በመትከል ኤሌክትሪክ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ እየተጋች ያለችው ረቂቅ፤ በቀጣይ ሥራውን በስፋት ለማስራጨትና በፍጥነት ተደራሽ የመሆን ዕቅድ አላት ። ለዚህ ዕቅዷም የውጭ አገር ኢንቨስተሮችን በመሳብ ፋይናንስ እንዲያደርጉ ሥራ ጀምራለች ።ከዚህ በተጨማሪም የሶላር ኢነርጂ እቃዎችን በማከፋፈል በተንቀሳቀሰችባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች በሙሉ የግብርና ሥራ በስፋት ያልተሠራና ብዙ ማትረፍ የሚቻልበት የሥራ ዘርፍ እንደሆነ ተገንዝባለች ፡፡

ትዝብቷን በቁጭት ወደ ሥራ የመቀየር ልምድ ያላት ረቂቅ፣ አሁን የጀመረችውን የሶላር እቃዎችን የማከፋፈል ሥራ አጠናክራ በመቀጠል ሕዝቡ ሙሉ ለሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል እስኪያገኝ ድረስ የመሥራት ፍላጎት አላት፤ በተመሳሳይ ደግሞ በግብርናው ዘርፍ የመሰማራት አቅዳለች ።በየአካባቢው የተመለከተቻቸው የተፈጥሮ ሀብቶች እጅግ የሚያጓጉ እንደሆኑ ትጠቅሳለች፤ ከአፈሩ ጀምሮ አየሩና መሬቱ ለሁሉም ነገር እጅግ ተስማሚ መሆኑን የገለጸችው «ሀብት እያለን የምንራብ ዜጎች ነን» በማለት ነበር፡፡

በዙሪያችን በርካታ ችግሮች ስለመኖራቸው ያነሳችው ረቂቅ፤ «አይናችንን መግለጥ አለብን» ትላለች ።ከወጣቱ ብዙ የሚጠበቅ ነገር እንዳለ በማንሳትም ችግሮች ሁሉ ዕድሎች እንደሆኑ ነው የምታስረዳው ። ብዙ ችግር አለ ማለት ብዙ ዕድሎች አሉ ማለት ነውና እያንዳንዱን ችግር ወደ ዕድል በመቀየር መፍትሔ ማምጣትና ገቢ ማግኘት ይቻላል ትላለች ።ሁሉም ሰው ሥራ ፈጣሪ መሆን እንደማይችል በመጥቀስ ሥራ ከሚፈጥረው ጋር በመሆን ተቀጥሮ በመሥራት መፍትሔ መሆን እንደሚቻልም ትጠቁማለች ።በሚሠሩት ሥራም ያላቸውን ሙሉ አቅም በመጠቀም ከልባቸው መሥራት ይኖርባቸዋል። ያኔ እነሱም፣ የሚሠሩበት ተቋምም ውጤታማ መሆን ይችላሉ ።በማለት ወጣቶች ለሥራቸው ታማኝና ትጉ በመሆን ውጤታማ እንዲሆኑ መክራለች ።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ፕሮጀክት በፍጥነት የመጨረስ ማሳያው መልሶ ግንባታ

ቤዛ እሸቱ

**ምቀኛ ሸረኛውን ያዝልን አቦ**
**ሀገር አማን ይሁን**
**ወሎ አማን ይሁን**
**ኢትዮጵያ አማን ትሁን**
**ወታደሩ ሁሉ ይጠበቅልን**
**ገበሬ ከምርቱ ፤ዳኛ ከፍርድ ቤት ይሁን**
**ሀገር አማን ይሁን**
**እመቤቶቹም ደህና ይሁኑ ሁሉም ይጠበቅ**

ይሄ ከወሎ አባወራ የማይጠፋ የዘወትር ምርቃት ነው፤ ምርቃቱ በሚደረግበት የቡና ሥርዓት ላይ ታላቅ ሲመርቅ የተቀሩት «አሜን» እያሉ ምርቃቱን ይቀበላሉ። ፈጣሪ ምርቃቱን እንዲያደርሰውም ይለማመናሉ ።

ሁሌ የታሰበው አይሆንምና አምና በወሎ የከተማና የገጠር አካባቢዎች ላይ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ተፈጸመ ።በዚህ ወረራም ሕይወታቸው ካለፈው፣ የአካል ጉዳት ከደረሰባቸውና የመኖሪያ መንደራቸውን ለቀው ከተሰደዱት፣ ለስነ ልቦና ቀውስ ከተዳረጉት ነዋሪዎች በተጨማሪ በርካታ የመሠረተ ልማቶች በቡድኑ ወድመዋል፤ ተዘርፈዋል ።

በወረራው የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶና አሻሽሎ ለመገንባት ብዙ ቢሊየን ብር የሚጠይቅ መሆኑ በተለያዩ ወቅቶች የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ ።ለእዚህ መልሶ ግንባታም ሕዝቡ ርብርብ እንዲያደርግ ጥሪዎች ሲተላለፉ ቆይተዋል ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርም በአማራ ክልል በወረራው ከፍተኛ ውድመት የደረሰባቸውን ሰባት ከተሞች በመምረጥ በ18 ፕሮጀክቶች የመልሶ ግንባታ በማድረግ ባሳለፍነው ሳምንት አስመርቋል ።በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በወረራው በእጅጉ ተፈትነው የነበሩ የአካባቢዎቹ ነዋሪዎች የደስታ ምርቃት አድርሰዋል። መልካም ነገር ይጋባልና በከተሞች አካባቢ የተጀመረው ሌት ተቀን የልማት ሥራን የመሥራት ባህል በወረራው ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የወደመውን መልሶ በመገንባትም ተደግሟል ።

በደሴ በኮምቦልቻና በከሚሴ ከተሞች በተካሄዱት የፕሮጀክት የምረቃ ሥነ-ሥርዓቶች ላይ የተገኙት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደገለጹት፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከምንም በላይ ከተሞች ላይ ትኩረት አድርጎ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል። ከተሞች ውስጥ ደግሞ የግል መኖሪያ ቤቶችን ሳይሆን ለሕዝቡ ነገ ትልቅ ጥቅም የሚሰጡ የሕዝብ ተቋማትን፣ በተለይ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማትና ከፍተኛ የሥራ እድል መፍጠር የሚችሉ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማትን አውድሟል ።

ሚኒስትሯ ከአራት ወራት በፊት አካባቢውን በተመለከቱበት ወቅት በማኅበረሰቡ ዘንድ የነበረውን ቁዘማ አስታወሱ፤ በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ አንድ ወንበር እንኳን የማይገኝበት ኮምፒውተርና ዶክመንቶች በሙሉ ተቃጥለውና ወድመው ሕጻናት የሚማሩበት ወንበር ሳይቀር ወድሞ መመልከት ልብ እንደሚሰብር ገልጸዋል ።በዛ ቁጭት የወደሙትን መልሶ መጠገን ሳይሆን ከነበረው ከፍ ባለ ደረጃ ለመገንባት በመግባባት ከክልሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የተሻለ መገንባት እንችላለን በሚል ወኔ የመሠረት ድንጋይ መቀመጡን አስታወሰዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በቁጭት የበለጠ መነሳት ነባሩን ለመጠገን ወይም ለማደስ ሳይሆን አዳዲስ እንዲኖሩ ማድረግ ይጠበቃል ።ወራሪውንም ኃይል መበቀል የሚቻለው በውጤት የሚለካ ተጨባጭ ሥራን በመሥራት ነው ። «ማሸነፋችንን የምናረጋግጠውና መበቀል የምንችለው ይህን በማድረግ ነው» በሚል ስሜት የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት 150 ሚሊዮን ብር በመመደብ ወደ እንቅስቃሴ መገባቱን ሚኒስትሯ ይገልጻሉ ። የመሠረት ድንጋዩ ከተቀመጠ በኋላ እውነት በተባለው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ወይ? የሚል ፍራቻ እንደነበራቸውም ያስታውሳሉ ።ኢትዮጵያውያን ሲነኩ የበለጠ እንደሚበረቱ ጠቅሰው፣ በዚህ መልሶ ግንባታ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ከሚታወቀው ከስምምነቱ ውጪ ውልን በማራዘም ጊዜ ከመግዛት ተላቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ውሉ አራት ወር ሆኖ በሦስት ወር የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ማየት መቻሉን ነው ሚኒስትሯ የጠቀሱት ።ይህም የፕሮጀክቱን ሥራ ሲከታተሉ የነበሩ አመራሮችንና ባለሙያዎችን የሚያስመሰግን መሆኑን ጠቁመዋል ።

ሚኒስትሯ መሠረተ ልማቱን ያፈረሱ አካላት መሠረተ ልማቶቹ መልሰው መገንባታቸውን ሲመለከቱ ሕዝቡ ምን ያህል በወኔ የተሞላና በተስፋ ወደፊት መገስገስ የሚችል ወኔ ያለው መሆኑን እንደሚያዩበት ተናግረዋል ።ካሁን በኋላ እናጠፋለን ብለው ቢያስቡ ሕዝቡ ከዚህ የተሻለ መሥራት እንደሚችል እንዲገነዘቡ እንደሚያደርጋቸው ጠቅሰው፣ እንዲያውም እነሱን መነካካት ማሳደግ ነው ብለው እንዲያስቡና ተስፋ እንዲቆርጡ የሚያደርጋቸው ይመስለኛል፤ አሁንም ከዚህ የተሻለ መሥራት እንችላለን የሚል ፊት እያየሁ በመሆኑ ደስተኛ ነኝ» ብለዋል ።

የአማራ ክልል የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢያዝን እንኳሆነ በበኩላቸው የጠላት ኃይል በክልላችን በተለይ በምስራቁ አካባቢ ሁሉን አቀፍ ውድመት አድርሷል ይላሉ ።«ጠላት ሞራልንም የመግደል ተልኮ ይዞ ነው ወረራ የፈጸመብን ።» ያሉት ኃላፊው፣ ጠላትን መመከት ከተቻለ በኋላ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በከተሞች ሴፍቲኔት ፕሮግራም በኩል 150 ሚሊዮን ብር በመመደብ የወደመውን በሙሉ የመተካት ሳይሆን የተወሰኑ ተቋማትን መልሶ የመገንባት ሥራ መከናወኑን አስታውቀዋል ።በዚህም በሚኒስቴሩ ድጋፍ በሰባት ከተሞች ማለትም በሰቆጣ፣ ላሊበላ፣ ወልዲያ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ከሚሴና ሸዋሮቢት የ18 መሠረተ ልማቶች ፕሮጀክቶች መልሶ ግንባታ ሥራ መካሄዱን ገልጸዋል ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ስምንት 12 ክፍሎች ያላቸው ትምህርት ቤቶች፣ ሦስት ጤና ጣቢያዎች፣ ሰባት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት ።በሰቆጣ፣ ላሊበላ፣ ወልዲያ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ከሚሴና ሸዋሮቢት ከተሞች ላይ ግንባታቸው ተካሂዷል ።ፕሮጀክቶቹ ትልቅ ትምህርት የተወሰደባቸውና ለወደፊት መልሶ ግንባታ ሥራም መሠረት የተጣለባቸው ናቸው ። ለወደፊቱም ከዚህ ልምድ በመቅሰም የወደሙ ተቋሞችን መመለስና ጠላትን ማሳፈር የሚቻልባቸውን ሥራዎች ለመሥራት እያሰብን እንገኛለን ሲሉ አቶ ቢያዝን ጠቁመዋል ።

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የከተማ አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ፈንታ ደጀን እንዳሉት፤ የመልሶ ግንባታው መነሻ በወረራው መሠረተ ልማቶች የወደሙባቸው አካባቢዎች ናቸው ።ሌሎች አካባቢዎች በተሳለጠ መንገድ ሥራቸውን እየሠሩ በእነዚህ አካባቢዎች በወራሪው ቡድን የደረሰው ውድመት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሚዛን የሚያሳጣ፣ የድሆችን ተስፋ የሚያጨልምና የታዳጊ ህጻናትን የትምህርት እድል የሚነሳ በመሆኑ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር ፕሮጀክቶቹ ተገንብተው ለምረቃ እንዲበቁ አርጓል ።ሚኒስቴሩ በቀጣይም የተመረቁትን ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚከታተልና የሚደግፍ ሲሆን፣ ከተሞች ከደረሱበት የእድገት ደረጃ የበለጠ እንዲያድጉና ከገጠር ወደ ከተማ ያለውን ፍልሰት የሚሸከም አቅም እንዲኖራቸው ድጋፍ ይደረጋል ።

በክልሉ ሰባት የአንድ ማዕከል የአገልግሎት መስጫ ማእዕከላት ተገንብተዋል፤ የአማራ ክልል ሥራና ሥልጠና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አወቀ ዘመነ እንደሚሉት፤ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎቹ ሁሉንም አገልግሎት በአንድ ማዕከል ለመስጠት በማሰብ የተገነቡ ናቸው፤ በማዕከሉ በተለይ ለሥራ እድል ፈጠራ ትልቅ ትኩረት ይሰጣል ።

የሥራ እድል ፈጠራ የክልላችን ትልቅ ችግር ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፣ በወረራው የደረሰው ጉዳት የሥራ አጥነቱንም እያስፋፋው መሆኑን ይጠቁማሉ ።የሥራ አጥነትን ለመፍታት የማዕከላቱ ሚና ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል ።

እንደ አቶ አወቀ ገለጻ፤ በአንድ ማዕከል ሥራ ፈላጊዎችን በመመዝገብ የግንዛቤ ፈጠራና የሥራ ሥልጠና የሚካሄድ ሲሆን፣ በማዕከሉ ሥራ ፈላጊዎች እንዲደራጁ ይደረጋል። ሥራ ፈላጊዎችን ከቀጣሪዎች ጋር የማገናኘት፣ የገበያ ትስስር፣ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ፣ የብድር አቅርቦት፣ የሼድ አቅርቦትን ጨምሮ ሥራ ፈላጊዎች የሚያስፈልጋቸው አገልግሎት በሙሉ በማዕከሉ ውስጥ የሚያገኙ ይሆናል ።

የቀድሞዎቹ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች የታሰበውን በሙሉ ከመከወን አንጻር ውስንነት ነበረባቸው የሚሉት አቶ አወቀ፣ አዲስ የተገነቡትን የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ሞዴል ለማድረግ መታቀዱን ገልጸዋል ። ለዚህም ማዕከሎቹ የታሰበውን ሥራ እንዲሠሩ ግብዓት ለማሟላት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እንደሚሠራ ይጠቁማሉ ።

በደሴ ከተማ አቅራቢያ በሚገኙት የገራዶ አንደኛና መካከለኛ ደረጃና የደረቅ ወይራ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገነቡ የተማሪዎች መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ መጽሐፍት (ላይብራሪ) እና የላብራቶሪ ምርቃ ላይ የተገኙት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ እንደገለጹት፤ ትውልድን የሚያንጽና ሀገር የሚገነባ ትምህርት ቤት ምቹና ንጽሕናው የተጠበቀ፣ ልጆች እንዲወዱት ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት ።ሆኖም በርካታ ትምህርት ቤቶች በዚህ ደረጃ አይገኙም ።ስለሆነም ትምህርት ቤቶችን የመቀየር ቀሪ ሥራ መሥራት ይኖርበታል ።

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ማብራሪያ፤ አሸባሪው ሕወሓት በፈጸመው ወረራ ንጹሓን ዜጎችን ገድሏል፣ አቁስሏል፣ አፈናቅሏል፤ ንብረት አውድሟል፤ ዘርፏል። ሀብትና ንብረት ከተዘረፈበት አካባቢ አንዱና ትልቁ የሚገኘው የደሴ ከተማና አካባቢው ሲሆን፣ የወደመው ንብረት መልሶ እንዲተካ ከፌደራል መንግሥት ጀምሮ የሚገኙ የተለያዩ አካላት የሚችሉትን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ ።የክልሉ መንግሥትም ለአምስት ዓመት የሚቆይ የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት በማቋቋም ወረራና ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች ሁሉ ቢቻል ከነበረው በተሻለ መልሶ ለመገንባት እንቅስቃሴ ጀምሯል ።

በ90 ቀናት ውስጥ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በደሴና በአካባቢው ከተጎዱ ትምህርት ቤቶች በመምረጥ መማሪያ ክፍሎችን በአዲስ መንገድ በመገንባት ለመማር ማስተማሩ ሥራ ዝግጁ አድርገዋል ።

በእኛ ሀገር መጀመር ነው እንጂ በፍጥነት መጨረስ ገና ባህል አላደረግነውም፤ ፕሮጀክቱ ጀምሮ በፍጥነት ሥራን የማጠናቀቅ ማሳያ ነው ሲሉ ርዕሰ መስተዳድሩ ገልጸዋል ።ወደፊት የሚካሄዱትን ግንባታዎችንም በዚህ መንገድ በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረጉን ባህል አጠናክረን እንሄዳለን ሲሉ ገልጸዋል ።

በደረቅ ወይራ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ረሂማ ይመር በትምህርት ቤቱ ምረቃ ላይ ለተገኙት አመራሮች ትምህርት ቤቱ መታደሱ ጥሩ መሆኑን ጠቅሳ፣ የሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎችም እንዲታደሱና፣ ውሃና መብራት እንዲገባላቸው፣ መጸዳጃ ቤት እንዲሠራና የመማሪያ መጽሐፍትና የላብራቶሪ እቃዎች እንዲሟላ ጠይቃለች።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ለመገንባት ቃል ገብተዋል፤ የአካባቢው መስተዳድር ሚኒስቴሩ ለሠራው ትምህርት ቤት አስፈላጊው ቁሳቁስና የመማሪያ መጽሐፍት እንዲያሟሉ ውሃ እና መብራት እንዲያስገቡ አደራ ብለዋል። የከተማው ከንቲባም ለትምህርት ቤቱ ውሃና መብራት ለማስገባት በሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

ነዋሪነታቸው በደሴ ዙሪያ ገራዶ ቀበሌ የሆኑት አርሶ አደር ሸባባው አለማየሁ ፤ በሀገራችን በአንድ እጅ ክላሽ በሌላው እጅ ዶማና ማጭድ ተይዞ ልማቱ ሳይጓደል ጠላቶችን እየተከላከሉ በአጭር ጊዜ ይህን የመሰለ ሐውልት በመሠራቱ መደሰታቸውን አስታውቀዋል ።ይሄ ትምህርት ቤት ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ ሐውልት ነው ሲሉ ገልጸው፣ የተሠራውን ትምህርት ቤት የሰው ልጅ ማደጊያ ነው በማለት ደስታቸውን አመልክተዋል ።

በከሚሴ ከተማ የሚገኘው የሰኔ 29 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ሌሊሳ አመንቲ በከተማው በአሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ የሽብር ቡድኖች የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት እየተሠራ መሆኑን በመግለጽ፤ እርሳቸው የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ሦስት የመማሪያ ሕንጻዎች እንደተገነቡለት ይናገራሉ ።ትምህርት ቤቱ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በመገንባቱና ለምርቃት በመብቃቱም ተደስተዋል ።

በትምህርት ቤቱ ከአራት ሺ በላይ ተማሪዎች እንደሚማሩ በማንሳት በአጭር ጊዜ ግንባታው ተጠናቆ ለመማር ማስተማሩ ዝግጁ መሆኑን ጠቅሰው፣ ግንባታው የመማሪያ ክፍል ጥበትን እንደሚቀርፍና የተሻለ ትውልድ ለመፍጠር ሚናው የጎላ መሆኑን ያስረዳሉ ።

ሌላው በትምህርት ቤቱ ለረዥም ዓመታት ያስተማሩት መምህር መሐመድ ፋንታው በበኩላቸው አሸባሪው ሕወሓት ከሚሴን በያዘ ወቅት የትምህርት ቤቱን እንጨቶችና ወንበሮች ለማገዶ መጠቀሙን ገልጸው፣ ትምህርት ቤቱ በተደረገለት ጥገና የአካባቢውን ችግር መፈታቱን ይናገራሉ ።

የአማራ ክልል የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢያዝን በክልሉ የሚገኙ 228 ከተሞች በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ጉዳት ደርሶባቸዋል ።በሰባት ከተሞች የተሠራውን አድንቀው፣ በርካታ ከተሞች ተመሳሳይ ግንባታን እንደሚፈልጉም ይጠቁማሉ ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ ፕሮጀክቶቹ አድንቀው በተቋሞቹ የሚሰጠው አገልግሎትና በዚህም የሚገኘው የሕዝብ እርካታ የመጨረሻው ውጤት ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበው፣ ለዚህም አመራሩና ባለሙያዎች ኅብረተሰቡን ዝቅ ብሎ በማገልገል መጠናከር እንዳለበት አስታውቀዋል ።ፕሮጀክቶቹ የየአካባቢው ማኅበረሰብ መሆናቸውንም ተናግረው፣ኅብረተሰቡ ፕሮጀክቶቹን በቅርበት እንዲከታተልና እንዲደግፍም ጠይቀዋል ።

አመራር ከሕዝብ፤ ሕዝብ ከአመራር ጋር ከሆነ የማይፈታ ችግር የለም ።የሕዝብ ጥያቄዎች ይቀጥላሉ፤ ዛሬ ይሄን ስለሠራን ጥያቄዎችን በሙሉ መልሰናል ማለት አንችልም ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይሄ ሥራ ግን እንደ ስፕሪንግ ወደፊት የሚያስፈነጥረን ነው ብለን መውሰድ እንችላለን ብለዋል ።በአንድ እጃችን የአካባቢውን ጸጥታና የኢትዮጵያን ሕልውና እያስጠበቅን በሌላ እጃችን የልማት ሥራን በመሥራት አዲስ ምዕራፍ የጀመርን መሆኑን በመገንዘብ መቀጠል ይገባናል ሲሉም አስገንዝበዋል ።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ለአፍሪካ የሰላም አማራጭ የማመላከት ከፍ ያለ ሚና የተሰጠው የጣና ፎረም!

አፍሪካውያን በዘመናት ሂደት ውስጥ ሊሻገሩት ያልቻሉት አንድ ትልቅ ጉዳይ አላቸው፤ የሰላምና ፀጥታ ችግር። ይሄን ችግራቸውን ከማቃለል አኳያ ደግሞ ከራስ በላይ ለውጪ ኃይሎች የመፍትሄ ባለቤትነት ከፍ ያለ ግምት በመስጠት ዘመናትን የሰላምና ጸጥታ ችግሮቻቸውን ከአህጉሪቷ ውጪ ባሉ ኃይሎች ለመቀልበስ ይቻላል በሚል እምነት ሲሰሩ ቆይተዋል። ሆኖም ዘመን አልፎ ዘመን ቢተካም፤ ዓመታት ተከታትለው ቢያልፉም አፍሪካ ግን የሰላምና ጸጥታ ችግሮቿን ማቃለልም፤ መሻገርም ሳትችል ዛሬም ድረስ ግጭቶች ያለ እረፍት የሚከሰቱባት አህጉር ሆና ዘልቃለች።

በልምድና ተሞክሮ የተቃኘው "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" የሚል ድንቅ አገራዊ ብሂል ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያም የዚሁ ችግር ተጋላጭ አንዷ አፍሪካዊት አገር እንደመሆኗ፤ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ቀድማ በመገንዘብ በዛው ልክ አፍሪካውያንን ለማሳመንና ሊጋራ ችግራቸው በጋራ እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን አቅጣጫ መትለም ከጀመረች ዋል አደር ብሏል።

በዓድዋ የነጻነት ትግል ላይ ችግርን ተጋፍጦ በራስ አቅም መቀልበስ እንደሚቻል በተግባር የገለጠችው ኢትዮጵያ፤ አሁንም አፍሪካውያን በምንም ምክንያት ይሁን በምን በውስጣቸው ለሚገጥማቸው ችግር የመጀመሪያው ባለቤትና ባለመፍትሄ ራሳቸው አገራቱ ናቸው፤ አህጉራዊ ችግሩንም በአህጉሩ አገራት ትብብርና ሕብረት ሊፈታ ይገባል የሚል የይቻላል መንገዷን ለአፍሪካውያን በማስተጋባትም ግንባር ቀደም ናት።

ይሄን የይቻላል እምነቷን ሁሉም እንዲረዳውና ለተግባራዊነቱም መክሮ በጋራ እንዲሰራበት ለማድረግ ደግሞ አንድ የጋራ መድረክ ማመቻቸት ነበረባት። እናም ትኩረቱን ሰላምና ደህንነት/ጸጥታ ላይ አተኩሮ የሚመክር አፍሪካዊ ፎረም "ጣና ፎረም" በሚል በ2004 ዓ.ም እንዲመሰረት ተደረገ። ይሄ በኢትዮጵያ ሃሳብ አመንጪነት አፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካ መር የሆነ መፍትሄ ያስፈልጋቸዋል፤ የአፍሪካ የሰላምና ጸጥታ ችግሮችም በአፍሪካውያን መፍትሄ ሊበጅላቸው ይገባል በሚል መርህ የአፍሪካን ጉዳይ በአፍሪካ ምድር በጣናዋ ፈርጥ ባህርዳር ከተማ ላይ የተለያዩ የአፍሪካ መሪዎች፣ ባለሙያዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት የመጀመሪያው የፎረሙ ጉባኤ ተካሄደ።

አፍሪካውያን ስለ ሰላምና ደህንነታቸው ቁጭ ብለው የሚመክሩበት፤ የመከሩበትን ጉዳይም ወደ ተጨባጭ ተግባር የሚለውጡበትና ለችግሮቻቸው መፍቻ አድርገው የሚጠቀሙበት ይሄ መድረክ ታዲያ፤ የአፍሪካ መሪዎች፣ ምሑራንና ተመራማሪዎች፣ የጦር መሪዎች፣ ባለሀብቶችና ሌሎችም እየተሳተፉበት መዝለቅ ችሏል። ዘንድሮም ለአስረኛ ጊዜ ከጥቅምት 04 እስከ 06 በባህርዳር ከተማ እንዲካሄድ ቀን በተቆጠረለት መሰረት በአስረኛው ጉባኤው ሰላምና ፀጥታን ከማረጋገጥ አንጻር መንግስታት ከሚያከናውኑት ተግባር ባሻገር ዜጎች የሚኖራቸው ሚና ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይመክራል።

ዜጎች ይሄንን ሚናቸውን እንዲወጡ ከሚያግዛቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በሆነው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ግጭትን የመቋቋም አቅም እንዴት መፍጠር ይቻላል የሚለው ደግሞ የውይይቱ አስኳል ነጥብ እንደሆነም ተነግሯል። ከዚህ ባለፈም የፎረሙ አንድ አካል ሆኖ የዘለቀው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ሲሆን፤ በዚህም በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም ትልቅ አድናቆት እየተቸረው የመጣው የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ሂደትና ፋይዳው ላይም እንደሚመከር ታውቋል።

ፎረሙ በዚህ መልኩ ሰላምና ጸጥታን ዋና ማጠንጠኛው አድርጎ የአፍሪካ የሰላምና ጸጥታ ችግሮች በራሳቸው በአፍሪካውያን አቅም መፍትሄ ማግኘት አለባቸው ብሎ በዚህ ደረጃ ሲመክር፤ የአፍሪካ ህብረት ያስቀመጠውን አጀንዳ 2063 እውን ከማድረግ አኳያ የሚኖረው ሚና ተኪ የሌለው ነው። ምክንያቱም አጀንዳ 2063 በሁለንተናዊ መልኩ የበለጸገች አፍሪካን እውን ማድረግን ግቡ ያደረገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ ለዚህ እውን መሆን አፍሪካ እግር ከወርች ወጥረው የያዟት ችግሮቿ እልባት ሊያገኙ ይገባልና። ለምሳሌ፣ መሰረተ ልማት፣ የስራ እድል ፈጠራ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ትምህርትና ሌሎችም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እምርታዎች የአጀንዳው ተጠባቂዎች ናቸው። እነዚህን እምርታዎች ለማስመዝገብ ግን የአህጉሪቷን ሰላምና ጸጥታ ማረጋገጥ እና በኀብረቱ ግብ ላይ እንደተመላከተውም ከመሳሪያ ድምጽ የጸዳች አፍሪካን እውን ማድረግ የግድ ይሆናል። ይሄን ማድረግ ካልተቻለና አፍሪካ የኹከት፣ ብጥብጥና ግጭት ማዕከል ሆና በማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እያለፈች ያንን እውን ማድረግ አይቻልም።

የጣና ፎረም እውን መሆንም አንዱ ምክንያት ለዚህ ችግር እልባት መስጠት በሚቻልበት ነጥብ ላይ መምከር፤ የተመከረባቸውን ጉዳዮችም የጋራ አድርጎ ወደተግባር መቀየር እና አፍሪካን የተረጋጋች፣ ሰላምና ጸጥታ የሰፈነባት እንዲሁም የበለጸገች አህጉር ማድረግ ነው።

በመድረኩ የሚሳተፉትም ይሄንኑ እውን ማድረግ የሚያስችል ሃሳብን በጥናት አስደግፈው የሚያቀርቡ፤ ሃሳቡን ማሳለጫ የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርጉ፤ ለሃሳቡ መሬት መውረድ ፖለቲካዊም የፀጥታም ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን የሚያስተገብሩና የሚተገብሩ የአፍሪካ መሪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ባለሀብቶችና የፀጥታ ኃይሎች ናቸው። አስረኛው ፎረምም በዚሁ አግባብ በርካታ አካላት የተሳተፉበት እንደመሆኑ፤ ፎረሙ ለአፍሪካ የሰላም አማራጭ የማመላከት ከፍ ያለ ሚናውን ለማሳካት እንዲችል በመድረኩ የተቀመጡ ውሳኔዎችን ለመተግበር የተናበበና የተቀናጀ ኃላፊነትን መወጣት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## የትምህርት ጥራትን የማምጣት ውጥንና ለውጦቹ

ክብረ መንግስት

ትምህርት በሁለመናዊ ትኩረቱ በእውቀትም በክህሎትም አቅም ያለው ዜጋ ማድረግ፤ ምክንያታዊ ዜጋ መፍጠር ነው ። የትምህርት ፋይዳው በዚህ መልኩ ሊገለጽ የሚችለው ግን ተደራሽነቱን ከጥራት ጋር አሰናስሎ ማስኳዝ ሲቻል ነው ። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ባለፉት ሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት የነበረው የትምህርት ስርዓት ከዚህ እውነት የተፋታ ሆኖ ስለመቆየቱ በርካቶች በማሳያ አስደግፈው ሲናገሩ ይደመጣል ። ከዚህም ባለፈ የለውጡ ማግስት መንግስት ይሄንኑ እውነት ተገንዝቦ የጥራት ችግርን ለመፍታት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ርምጃዎችን ሲወስድ ተመልክተናል ። ምክንያቱም የቀደመው ሂደት የትምህርት ሂደቱ ቁጥር (በተመራቂም፣ በትምህርት ቤቶች ግንባታና ተደራሽነትም) ተኮር በመሆኑ ነው ።

በዚህ መልኩ ቁጥርን እንጂ ጥራትን መሰረት ያደረገ ስራ ያለመሰራቱ፤ ተመራቂ ተማሪዎች የሚፈለገውን እውቀትና ክህሎት ጨብጠው ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጭምር ስለማይወጡ ከግለሰብ ጀምሮ አገርና ሕዝብ ዋጋ ከፍለዋል። ምክንያቱም፣ ጥራት ባለው ትምህርት ውስጥ ያለፈ ተማሪ ሙሉ ስብዕናው የተስተካከለ፤ ራሱን፣ አካባቢውን፣ ማህበረሰቡን፣ አገሩንም በእውቀቱ የሚመራ፤ በማንነቱ ኮርቶ ሌሎችም እንዲኮሩበት የሚያደርግ ነው ። ሆኖም እውነቱ ከዚህ በተቃራኒ ሆኖ ተገልጿል ።

ለትምህርት ጥራት መጓደል እንደየሰው ምልከታ የተለያየ ምክንያት ሲሰጠው ይደመጣል ። ለምሳሌ፣ የትምህርት ጥራት የወደቀው በፖሊሲ ምክንያት ነው የሚሉ ምሑራን አሉ ። በአንጻሩ፣ ችግሩ ከፖሊሲው ሳይሆን ፖሊሲውን የመተግበር ሂደት የወለደው ነው የሚል ምክንያት ደግሞ ከደም ካለው መንግስት ሲደመጥ ቆይቷል ። በሌላ በኩል፣ ‹‹የልጄን ስነምግባር ያጎደለው ትምህርት ቤት በአግባቡ ስለማይቆጣጠሩት ነው›› የሚል ወቀሳ አዘል ምክንያት ከወላጅ ይደመጣል ። ትምህርት ቤቶች በተራቸው ‹‹ወላጆች ልጆቻቸውን በአግባቡ ስለማይቆጣጠሯቸው እኛን አስቸግረውናል›› ሲሉ፤ የዩኒቨርሲቲ መምህራንም እንዲሁ ‹‹አሁን ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ማንበብ ፣ መፃፍ አይችሉም›› በማለት ችግሩን ወደሌላ አካል የማዛመት ሂደት ውስጥ ይገባሉ ።

ተማሪዎችም ቢሆኑ ለድክመታቸው ምክንያት አያጡም ። ‹‹እንዴት ብለን እውቀት እንገብይ የስድስት ወር ትምህርቱ በሶስት ቀን ለብ ለብ ተደርጎ ይሰጠናል›› ሲሉ የመማር ማስተማር ሂደቱን ክፍተት ለመጠቆም ይጥራሉ። ምክንያቱ ያም ሆነ ይህ ግን ሁሉንም የሚያስማማ አንድ ነገር የትምህርት ጥራት ጉዳይ መውደቁ ነው ። ለዚህም ነው የለውጡ ማግስት መንግስት የትምህርት ጥራት ጉዳይ አንዱና ትልቁ አጀንዳው አድርጎ ሲሰራበት የቆየው፤ የፖሊሲና ተያያዥ ማሻሻያን በማድረግ ለተግባራዊነቱ ሲጥር፤ እና ይሄን ጥረቱን ለፍሬ የሚያበቁ ርምጃዎችንም ሲወስድ እየተስተዋለ ያለው ።

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በዋናነት ሶስት ትልልቅ ምሶሶዎች እንደሚያስፈልጉ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ ። እነዚህም ብቃት ያላቸው መምህራን፤ ጥራት ያላቸው የትምህርት ግብአቶችና ግብአቶችን የሚጠቀሙ ባለሙያዎች እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀና ለትምህርት ጥራት የተመቻቸ አካባቢ ናቸው ። ይሄንን የባለሙያዎች ምልከታ ይዤ፤ በኢትዮጵያ ያለው እውነት ምን ይመስላል? የሚለውን ለመመልከት ጥቂቶቹን በማሳያነት ልጠቃቅስ ወደድሁ ።

በቅድሚያ የመምህራንን ብቃት እንመልከት ። ብቃት ማለት እውቀት፣ ክህሎት እና ሰብዕናን ተጠቅመን የታሰበውን ወይም የተፈለገውን ውጤት ማምጣት መቻል ነው ። ስለሆነም ይህንን ብቃት የሚያሟላ መምህር አለ ወይ ስንል መልሱን አፍ ሞልቶ አዎ የማይባልበት ነው። ምክንያቱም በመምህሩ የተዘራውን ዘር በተማሪው አማካኝነት ፍሬውን እያየነው ስለሆነ ነው ። መምህሩ ሲማርም ሆነ ተማሪዎችን ሲያስተምር በአንድ አይነት መልኩ ነው ። የእርሱ ባህሪ ተማሪዎች ላይ ያጋባል ። በመሰል ስርዓት ውስጥ እንደማለፉም ማስተማርን በቸልታ የሚያየውም ቀላል አይደለም ።

ስለዚህም ነው ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ለመምህሩም ለተማሪውም ስለማይደርስ የትምህርት ጥራት ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ እንዲመጣ አድርጎታል ። መንግስትም አሁን ላይ ይሄን የመምህራን ብቃት ችግር ለማረም እንዲችል አቅምን ለመለየት የሚያግዘውን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና መጀመሩም ለዚሁ ነው ። በዚህም መምህራን በምን ደረጃ ላይ ናቸው የሚለውን ምዘናው ያሳየ ሲሆን፤ ጅማሮውም ብዙ ነገሮችን እንደሚያስተካክል ተስፋ ተጥሎበታል ። ምክንያቱም በዚህ መልኩ ነጥሮ የሚወጣ መምህር እውቀቱን የበለጠ እንዲያዳብር እና ተማሪዎችን በመደገፍና ማብቃት ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ።

በሁለተኛ ደረጃ የምናነሳው ጉዳይ ጥራት ያላቸው የትምህርት ግብአቶችና ግብአቶችን የሚጠቀሙ ባለሙያዎች የሚለውን ሲሆን፤ ከመምህራኑ በተለየ መልኩ የሚታይ አይደለም ። በእርግጥ እንደ አገር በርካታ ፈተናዎች ያሉብን እንደመሆኑ፤ በዛው ልክ የተሟላና ጥራት ያለው የትምህርት ግብዓት ማግኘት ፈታኝም ፈተናም ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል ። ግብዓቱ ከሌለ ደግሞ ባለሙያው ከየትም አይመጣውም ።

ወደ ሦስተኛው ምሰሶ ስንገባ ደህንነቱ የተጠበቀና ለትምህርት ጥራት የተመቻቸ አካባቢ መፍጠር የሚለው ነው ። እንደ መንግስት በዚህ ውስጥ በርካታ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች እንደተከናወኑ መመልከት ይቻላል ። አንዱ አዲሲቱ ኢትዮጵያ በሚል የተጀመረው የትምህርት ቤት ግንባታ ጉዳይ ሲሆን፤ በሁሉም ክልሎች ላይ ጅማሮዎቹ እየታዩ ናቸው ። ሌላው አዲስ የትምህርት ስርዓት ቀርጾ ወደ ሥራ መግባቱ ሲሆን፤ በዚህም በርካታ ለውጦች ከወዲሁ እየመጡ ናቸው ። ማለትም በ10 ዓመቱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ የተካተቱት ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን አገርንም ጭምር ከፍ የሚያደርግ እንደሆነ አመላካች ነገሮች አሉ ።

ለአብነት ተማሪዎች ታሪካቸውንና ባህላቸውን አውቀው በጥሩ ስብዕና እንዲማሩ ከማድረግ አኳያ ከአገር በቀል እውቀት የሚቀዳው ግብረገብነት እንደ አንድ የትምህርት አይነት ተደርጎ ይሰጣል ። ሌላው እንደ አገር ያስቸገረውና ዓመታትን ያስቆጠረው የስርቆትና ኩረጃ ጉዳይ መፍትሄ እንዲበጅለት የተደረገበት አዲስ ጅማሮም ከለውጡ ቱርፋቶች መካከል የምናስቀምጠው ነው ። ይሄን አስመልክቶ የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ያወጣው መግለጫ፤ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና አሰጣጥ በትምህርት ላይ እየመጣ ላለው ለውጥ አንዱ ማሳያ ስለመሆኑ ነው ያመለከተው ።

በመግለጫው እንደተመላከተውም ሀገራችን ኢትዮጵያ በለውጥ ጎዳና ውስጥ ከገባችበት ጀምሮ በርካታ ተቋማዊ እና የፖሊሲ ሪፎርም ርምጃዎችን ወስዳለች ። ከእነዚህ የለውጥ ርምጃዎች መካከልም አንዱና ዋነኛው የትምህርት ዘርፉ ሪፎርም ነው። ባለፉት ዓመታት ከተደራሽነት አንፃር መልካም ሥራዎች የተሠሩ ቢሆንም የትምህርት ጥራት ጉዳይ በእጅጉ ተዳክሞ ቆይቷል ። እናም መንግሥት የትምህርት ጥራትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ፓኬጆችን በመቅረፅ በርካታ የሪፎርም ርምጃዎችን ወስዷል ።

ከተወሰዱ ርምጃዎች መካከል የምዘና ሥርዓትን ማሻሻል አንዱ ሲሆን፤ ይህንን ለማሳካት የሚያስችለውን የመጀመሪያ ዙር የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የመልቀቂያ ፈተና በተለየ ሁኔታ በከፍተኛ ዝግጅትና ተቋማዊ ቅንጅት ተሰጥቷል ። ይሄም ከዚህ በፊት በብልሹ አሠራር፣ በስርቆት እና በማጭበርበር ይደረግ የነበረውን የፈተና ሂደት በማስቀረት ሁሉም ተማሪ እኩል የሚመዘንበት ዕድል እንዲፈጥር የሚያደርግ ነው ።

ተፈታኝ ተማሪዎችና የተፈታኝ ወላጆችም ቢሆኑ የዘንድሮውን የብሔራዊ ፈተና በመልካም ጎኑ አይተውታል። በምክንያትነት የሚያነሱትም ሁለቱም አካላት ተፈታኞች የላባቸውን የሚያገኙበት አጋጣሚ ይፈጥራል ብለው ማሰባቸው ነው ። ፈተናው ሲጠናቀቅ ደግሞ የሂደቱን ውጤታማነት የበለጠ መመልከት የሚቻልበት እድል መኖሩ እሙን ነው ። እናም ለውጡ እንዳለ ሆኖ ችግሮችን እያዩ መፍታት አሁንም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ በመጠቆም ለዛሬ ሃሳቤን በዚህ ልቋጭ ። ሰላም!!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# “አቅቶኛል መሸከምም ከብዶኛል”

- አባት አቶ ከድር አህመድ የሱፍ

እፀገነት አክሲሱ

ህይወት ብዙ ውጣ ውረድ አላት ። ለአንዱ ምቹ ለሌላው ደግሞ ጎርበጥባጣና እሾሃማ ናት ።ጫናዋ ከጫንቃ በላይ ይሆናል ።በእርግጥ ሁሉንም እንደ አመጣጡና ሁኔታው መቀበልና መሸኘት አስፈላጊም ግዴታም ቢሆንም አንዳንዴ ከአቅም በላይ ሆኖ “ምነው ይህ ሁሉ ለእኔ ብቻ “ የሚያስብልበት ጊዜ ብዙ ነው ።

ሰው በምድራዊ ህይወቱ ሊፈተን ግድ ነው፤ ምክንያቱ ደግሞ ከፈተናዎች ሁሉ በኋላ አንጸባራቂ ድልን መጎናጸፍ ስላለ፤ አንዳንዶች ይህንን የህይወትን ፈተና ለመሸከም ጫንቃቸው ብርቱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በትንሽ በትልቁ ስብር እንክት ሙትት ሲሉም ማስተዋሉ የተለመደ ነው ።ነገር ግን ለህይወት ፈተና እጅ አለመስጠቱ ሳይሻል አይቀረም ።

በተለይም ሶስተኛው አለም ተብሎ በሚጠራው አፍሪካ እንደ እኛ አገር ደግሞ ለማደግ ለመበልጸግ ሩጫ ላይ ባለች አገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ በኑሮ ውጣውረድ ይፈተን ዘንድ ግድ ነው ።ይህንን ፈተና ማለት ግን የአለም ፍጻሜ አለመሆኑን ከተበረታ ችግርን ማሸነፍ ጨለማን አልፎ ብርሃን ማየት ጽልሙቱ ተገልጦ ብሩህ ቀን ላይ መድረስም እንደሚቻል ማመን ግድ ነው ።

የዚህ ሃሳብ መነሻችን የአቶ ከድር አህመድ የሱፍ ታሪክ ነው ።አቶ ከድር ተወልደው ያደጉት በስልጤ ዞን አምቢቾ ወረዳ ገሶ ገበሬ ማህበር ነው ።አቶ ከድር ለእናታቸው አንድና ብቸኛ ልጅ ቢሆኑም አባታቸው ሌላ ትዳር መስርተው የወለዷቸው በርካታ እህትና ወንድም አሏቸው ።አቶ ከድር እንደ አገር እንደ ወግ ባህሉ የልጅነት እድሜያቸውን ከእኩዮቻቸው ጋር አሳልፈዋል። ያን ያህል የተደላደለና ያማረ ኑሮን መኖር ባይችሉም ሳይርባቸው ሳይጠማቸው ነው ያደጉት ።ኋላም ለአቅመ አዳም ደረሱና እሳቸውም ትዳር መሰረቱ ፤ ለእናታቸው ብቸኛ ልጅ የሆኑት አቶ ከድር ከአባታቸው ልጆች ጋር በተካፈሏት አነስተኛ የእንሰት ማሳም እንሰት እንዲሁም ሌሎች የጓሮ አትክልቶችን እየተከሉ ኑሮን ተያያዙት። ሳይደላቸውም ሳይከፋቸውም ከባለቤታቸው ጋር ልጆች እየወለዱ እናታቸውን እየጦሩ መኖር ቀጠሉ ።ነገር ግን በዛች የበሬ ግንባር በምታክል የእንሰት ማሳ ምክንያት ከአባታቸው ልጆች (ወንድሞቻቸው) ጋር መስማማት አቃታቸው ።

አቶ ከድር ሲወጡ ሲገቡ የሚያዩት፣ የሚሰሙት ሁሉ አላምር ቢላቸው እንዲሁም እየሆነባቸው ያለው ነገር ለጤናቸውም አስቸጋሪ ሲመስላቸው የእሳቸውን ህመም ወደጎን በመተው አቶ ከድር ልጆቻቸውን ማሳደግ ብቻ ነበር ህልማቸው፤ የጀመራቸው ህመምም እጃቸው ተንቀሳቅሶ ስራ እንዳይሰራ ወደማሰሩ ደረጃ ሊሄድ ሆነ፤ አቶ ከድር “እኔ ብሞት ልጆቼ ምን ይሆናሉ” ብለው በማሰብ በበሽተኛ እጃቸው ለልጆቻቸው አንገት ማስገቢያ ጎጆ ቀለሱ፤ ልጆቻቸውን በዛ ካሳረፉ በኋላም ወደ ህክምና ለመሄድ ወሰኑ ።

እዛው የተወለዱበት አካባቢ “አጣጥ ሆስፒታል” ህክምናቸውንም ጀመሩ ፤ በህክምና ላይ እያሉም ጤናቸው ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ ጭራሽም እጃቸው አልታዘዝ ብሎ ተቆላለፈ ።

“.....አገር ቤት ልጆቼን ለማሳደግ እንሰት እተክላለሁ የጓሮ አትክልትም ነበረኝ፤ በጠቅላላው ልጆቼን ሳላስርብ እያኖርኩ ነበር፤ነገር ግን ወንድሞቼ ብቸኝነቴን አይተው የሚያደርሱብኝን ጫና መቋቋም አቃተኝ፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ ታማሚ ሆንኩ ፤ከዛው እዛው አጣጥ ሆስፒታል ያደረኩት ህክምናም ለውጥ አላመጣ አለኝ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ የእህቴ ልጅ ለአረፋ በዓል ወደቤት መጣ ያለሁበትን ሁኔታ አይቶ በጣም በማዘን አዲስ አበባ ለህክምና አመጣኝ በዛው እዚሁ ቀረሁ” ይላሉ ።





አዲስ አበባ ያመጣቸው የእህታቸው ልጅም ሆስፒታል አስገብቶ ህመምተኛው እጃቸው ኦፕሬሽን እንዲሆን አደረገ ፤ የመጀመሪያው ኦፕሬሽን በቂ ስላለነበር ከስምንት ወራት በኋላ ዳግም ኦፕሬሽን ተደረገ ።በዚህ ሁሉ መካከል ግን አገር ቤት ጥለዋቸው የመጡት ቤተሰቦቻቸው ሁኔታ ያሳስባቸዋል ምን ሆነው ይሆን ምን በልተው ዋሉ አደሩ ትምህርታቸውስ የሚለው ነገር በጣም እንቅልፍ ይነሳቸው ነበር ።ፈጣሪ ፈቅዶም ጤናቸው መሻሻልን ሲያሳይ ልጆቻቸውን ለማገዝ ስራ ማፈላለግ ጀመሩ ፤ በዚህ መካከል የቅርብ ዘመዳቸው የሆነ በኑሮው ጥሩ ደረጃ ያለ ሰው “ና ከእኛ ጋር እየኖርክ ስራ “ ብሎ አስጠጋቸውና አብረው እየኖሩ ሰዎቹ ባላቸው ድርጅት ውስጥ እየሰሩ ልጆቻቸውን ማሳደግ ተያያዙት ።

ይህም ቢሆን ግን የአቶ ከድር የህይወት ፈተና በቀላሉ የሚያበቃ አልሆነም፤ አዲስ አበባ በስራ ላይ እያሉ የባለቤታቸውን በጠና መታመም ሰሙ ።በዚህ ጊዜ ስራቸውን ትተው ያሉበትን ሁኔታ ለማየት አገር ቤት ገቡ ።ያዩት ነገር ግን በጣም አሳዘናቸው ባለቤታቸው ትተዋቸው እንደሄዱት አልጠበቋቸውም፤ የኑሮ ጫና፣ ህመም፣የልጆች ኃላፊነት በጠቅላላው በጣም ተጎድተዋል ።በዚህን ጊዜ አቶ ከድር ባለቤታቸውን አዲስ አበባ አምጥተው ማሳከምና መንከባከብ እንዳለባቸው ወሰኑ እናም ይዘዋቸው መጡ ።

ባለቤታቸው ያለባቸው የመገጣጠሚያ ኢንፌክሽን ብዙ ህክምና የሚያስፈልገው የዶክተሮችን የቅርብ ክትትል የሚጠይቅ ሆነ ።አቶ ከድር ጥበቃ እየሰሩ ወዲህ ወዲያ ብለው የሚያመጧት ገንዘብ ሆድ ሞልታ ለህክምና የምትተርፍ አልሆነችም እናም አይናቸውን ጨፍነው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይዘዋቸው ሄዱ፤ የእድል ጉዳይ ሆኖም የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ባልደረቦች ባለቤታቸውን ተቀበሉላቸው ።በዚህም አንድ አመት ከስድስት ወራት ያህል ሆስፒታል ተኝተው የህክምና ክትትላቸውን አደረጉ ።

በዚህ መካከል ግን ሌላ የህይወት ፈተና በባልና ሚስቶቹ ዘንድ መጣ ።አገር ቤት ጥለዋቸው ከመጡት ልጆች መካከል ሶስተኛው ልጃቸው ሰዒድ ከድር ይባላል፤ የሚወዳቸው እናቱ ታመውበት አንድ አመት ከስድስት ወራት ሆስፒታል ሲተኙ እሱ ደግሞ በገጠር ያሉትን ታናናሽ እህትና ወንድሞቹን በሚችለው አቅሙ ይንከባከብ ነበር ።ለእህትና ለወንድሞቹ እናትም አባትም ወንድምም እየሆነ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የጉልበት ስራ እየሰራ ሆዳቸው አዳይጎል፣ ከትምህርት እንዳይቀሩ ብዙ ይለፋ ነበር ።አባቱ እናቱን በማስታመም እየደከሙ መሆናቸውን ተረድቶም እሱም ያቅሙን ያህል ቤተሰቡን ያግዛል ።

አባት በዚህ ጊዜ ጠሮ መስኪድ አካባቢ ማታ ጥበቃ ስራ እየሰሩ ቀን ባለቤታቸው ጋር እየሄዱ ባለቻቸው ትንሽ ጊዜ ደግሞ ሙስሊም ህጻናትን ሰብስበው ቁርዓን እያስቀሩ ኑሮን ተያይዘውታል ።ልጅም በበኩሉ የአባቱን ዱካ ተከትሎ ወንድም እህቶቹን ያግዛል ።

ነገር ግን ሰዒድ የሚሰራው ስራ እያለፈበት ያለው የህይወት ጎዳና ከአቅሙና ከእድሜው በላይ ነበርና ድንገት እሱም ሆነ ቤተሰቡ ያላሰቡት ነገር ገጠመው ።ሰዒድ በትንሽ በትንሹ የጀመረው ህመም ተባባሰ ።ይህም ቢሆን ግን እናቱና አባቱ የእሱን ሁኔታ ሰምተው እንዲጨነቁ አልፈለገም ።ህመሙን ደብቆ ሲሻለው እየሰራ ሲብስበት እቤት እየዋለ ኑሮን ቀጠለ። ይህ አካሄድ ግን ረጅም ርቀት አላስኬደውም ።ችግሩ እየተባባሰ ሰዒድ ከመቀመጫው ተነስቶ መራመድ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ ።ይህ ሁሉ ሲሆን አባት አቶ ከድርም ሆኑ እናቱ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ።

ሰዒድ ለብዙ ጊዜያት ህመሙን ችሎ ኋላም ደብቆ ቢቆይም ከአባቱ ጋር የሚገናኝበት አጋጣሚ ተፈጠረ። አባት አቶ ከድር ወንድማቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ሰምተው ወደ አገር ቤት ሄዱ ።ሲሄዱ ግን የገጠማቸው ነገር ለእሳቸው ራሱ የሞት ሞት ሆነባቸው። ቀልጣፋና ጎበዙ የእሳቸውን ቀንበር ተቀብሎ የቤተሰቡ ምሰሶ የነበረው ትንሹ ልጃቸው እንደ እድሜ እኩዮቹ መሯሯጥ መራመድ አቅቶት እጥፍጥፍ ብሎ ተቀምጦ አገኙት ።

ያዩትን ማመን ያቃታቸው አባት አቶ ከድር “ ልጄ ምን ሆነህብኝ ነው ፤ ምን አገኘብኝ?” ሲሉ ጠየቁ ልጅም “አባቴ ከታመምኩ ትንሽ ቆየሁ፤ አጣና ስሸከም ነው እንዲህ የሆንኩት፤ነገር ግን መታመሜን ብነግርህ ትጨነቃለህ ብዬ ነው” አላቸው ።አባት አዘኑ ልባቸው ተሰበረ፤ ምንም እንኳን ባለቤታቸውን አሳክመው የጨረሱ ባይሆንም ህመምተኛውን ትንሹን ጎበዝ ልጃቸውን እዛው ጥለውት መምጣት አልፈለጉም፤”ለምኜም ቢሆን አሳክምሃለሁ ና እንሂድ ብለው አዲስ አበባ ወደተከራዩት ቤት ይዘውት መጡ” ።

አቶ ከድር ሁኔታው እሳቸውንም በሽታ ላይ የጣላቸው ቢሆንም ለልጃቸው ሲሉ ግን ቆሙ ጠነከሩ ፤ ጥርሳቸውን ነክሰው መራመድ የማይችለውን ልጃቸውን በጀርባቸው አዝለው ሆስፒታል ለሆስፒታል መመላለስ ያዙ፤ ቆሞ እንደኩዮቹ እንዲሄድላቸው የሚችሉትን ሁሉ ሊያደርጉ ለራሳቸው ቃል ገቡ አላህን እየተማጸኑም ጉዟቸው ቀጠሉ ።

አባት አቶ ከድር ከአጠገባቸው የሚያግዛቸው ማንም የለም፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ የጥበቃ ስራቸውን ሙሉ በሙሉ እርግፍ አድርገው ትተው ታማሚ ልጃቸውን በጀርባቸው አዝለው በቀን አንዴ እየተመገቡ አቤት ሆስፒታል መመላለስ ስራቸው ሆነ ። አሁን ላይ ልጃቸው በደጋግ ኢትዮጵያውያን አማካይነት በአቤት ሆስፒታል ህክምና እየተደረገለት ቢሆንም ምስኪኑ አቶ ከድር ግን ፈተናቸው አላበቃም፤ እርሳቸው እዚህ እየተሰቃዩ ማየትን ያልመረጡት ባለቤታቸው ህክምናቸውን አቋርጠው ገጠር ገብተዋል ።በሌላ በኩል ደግሞ የሰዒድ ታላቅ እህት ሉባባ ከድር ትምህርት ቤት ወድቃ እጇ በመሰበሩና በወቅቱ መታከም ባለመቻሏ ችግር ውስጥ እንደሆነች ሰምተዋል ።


አቶ ከድር ምንም እንኳን እሳቸውም ጤና እያጡ ቢሆንም ይበሉት ይጠጡት ለልጆቻቸውም ይሰጡት ነገር የሌላቸው አዛውንት ቢሆኑም ሴቷን ልጃቸውንም አሳክመው ለማዳን አዲስ አበባ እንድትመጣ አድርገዋል።

“...አሁን ሰኢድ ልጄ በደጋጎች አማካይነት በአቤት ሆስፒታል ህክምና እያገኘልኝ ነው ።ነገር ግን ታላቅ እህቱ ደግሞ እጇ ተሰብሮ መማር አልቻለችም ።እሷንም ለማሳከም አምጥቻታለሁ ።ሰዒድ ከተሻለው እሷን ደግሞ አሳክማለሁ “ ይላሉ ።

ስራ ላቆሙት አባት ከድር ይህ ጊዜ በጣም ከባድ ነው፤ በመከራ ላይ መከራ እየተደራረበባቸው ነው፤ ልጃቸው አቤት ሆስፒታል ህክምና ቢደረግለትም አንዳንድ ተጨማሪ ምርመራዎች ያስፈልጉታል ይህንን ማድረግ ፤ መድሃኒትና ምግብ መግዣም የላቸውም ፤ ሴቷ ልጃቸውም መጥታለች፤ እሷን ለማሳረፊያ የሚሆን ቤት ቢከራዩም አሁን ላይ ኪራዩን መክፈል አቅቷቸዋል፤ አባት ከድር ይህንን ሁሉ ሲናገሩ እንባቸው እንደ ጎርፍ ይወርዳል፤ አታልቅሱ ሲባሉም ሴት ተቀን ስራዬ ምን ሆነና ይላሉ ።ከእንባቸው ሌላ አሁን ላይ ምንም አቅም የላቸውም ።

በሌላ ጎን ደግሞ ይህ ሁሉ ፈተና ቢወርድባቸውም የችግራቸውን ግዝፈት ያህል አያማርሩም፤እንደውም አላህን ደጋግመው ያመሰግኑታል፤ ለሰጪዬ ይስጥልኝ በማለትም የምርቃት መዓት ያወርዳሉ ።

# ስፖርት



## ሙክታር ኢድሪስ በነገው የዴልሂ ግማሽ ማራቶን ለአሸናፊነት ይጠበቃል


**ቦጋለ አበበ**

የረጅም ርቀት የምንጊዜም ምርጡ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ በአለም ምርጥ ከተባሉት የጎዳና ላይ ውድድሮች አንዱ የሆነው የዴልሂ ግማሽ ማራቶን አምባሳደር ተደርጎ መመረጡ ይታወቃል። ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ አምባሳደር ሆኖ በመመረጡ ደስተኛ መሆኑን የገለጸ ሲሆን፤ ነገ ውድድሩ ሲጀመርም በህንድ መዲና ኒው ዴልሂ ተገኝቶ የሩጫው ተሳታፊዎችን እንደሚያበረታታ የአገሪቱ የስፖርት መጽሄት ባስነበበው ሰፊ ዘገባ ገልጿል።

ኃይሌ አምባሳደር በሆነበት በዚህ እውቅ የጎዳና ላይ ውድድር ሌላኛው ጀግና ኢትዮጵያዊ አትሌት ሙክታር ኢድሪስ የውድድሩ ድምቀት እንደሚሆን አዘጋጆቹ የገለጹ ሲሆን፤ በግማሽ ማራቶን ውድድር ቁንጮ የሆነ የአለማችን አትሌቶች በሚያደርጉት ብርቱ ፉክክር የአሸናፊነት ግምት ከተሰጣቸው ኮከቦች አንዱ ሆኗል።

የሁለት የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች የአምስት ሺ ሜትር ቻምፒዮኑ ሙክታር በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች በሚደምቀው የግማሽ ማራቶን ውድድር አዲስ ታሪክ ለመጻፍ የሚፎካከር ሲሆን፤ ቀዳሚዎቹን ደረጃዎች ይዘው የሚያጠናቅቁ አትሌቶች ከተዘጋጀላቸው 268 ሺ ዶላር ሽልማት እንደሚቋደሱ ይጠበቃል።

ፈጣን ሰአት በሚመዘገብበት በዚህ ውድድር ሰአት ማስመዝገቡ ይታወሳል። በዚያ ውድድር አራት አትሌቶች የቦታውን የቀድሞ ክብረወሰን ሲያሻሽሉ ሙክታር አንዱ የነበረ ሲሆን፤ በሽርፍራፊ ሰከንዶች ተቀድሞ አራተኛ ደረጃን ይዞ ነበር ያጠናቀቀው።



ለሁለተኛ ጊዜ የሚሳተፈው ሙክታር ለመጀመሪያ ጊዜ በ2020 በተወዳደረበት ወቅት 59:04 የሆነ ፈጣን

"በተፈጥሮዬ እስከ ሶስት ባለው ደረጃ ውስጥ ለማጠናቀቅ ነው የምወዳደረው" በማለት በመጀመሪያ የዴልሂ ግማሽ ማራቶን ውድድሩ ሶስተኛ ሆኖ ባለማጠናቀቁ ቁጭት እንዳደረበት የጠቆመው ሙክታር፤ ዘንድሮ ግን በጥሩ ብቃት ላይ እንደሚገኝና ለዚሁ ውድድር ትኩረት ሰጥቶ ሲዘጋጅ እንደቆየ ተናግሯል። ሙክታር አክሎም የነገውን ፈተና ደስተኛ ሆኖ ለመጋፈጥ እንደተዘጋጀ ገልጿል።

በውድድሩ ከሙክታር ጋር ጠንካራ ፉክክር ያደርጋሉ ተብለው የሚጠበቁ በርካታ አትሌቶች ቢኖሩም ዩጋንዳዊው ኮከብ ጃኮብ ኪፕሊሞ የተሰጠው ትኩረት ከሁሉም የተለየ ነው። ይህ የርቀቱ ባለክብረወሰን አትሌት ግማሽ ማራቶንን ከ58 ደቂቃ በታች ሶስት ጊዜ ማጠናቀቅ የቻለ እንደመሆኑ የተለየ ትኩረት ቢሰጠው አይገርምም። የ2021 የበርሊን ግማሽ ማራቶን አሸናፊው ኬንያዊ አትሌት ፌሊክስ ኪፕኮይች ሌላኛው ጠንካራ ተፎካካሪ አትሌት ሲሆን ኢትዮጵያዊው ጫላ ረጋሳም ትኩረት ካገኙ አትሌቶች አንዱ ነው። ይህ ወጣት አትሌት ባለፈው አመት በባርሴሎና ግማሽ ማራቶን ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ያስመዘገበው 59:10 የራሱ ፈጣን ሲሆን የማራቶን ኮከቡ ኬንያዊ በ2019 ቬና ላይ አርባ ሁለት ኪሎ ሜትርን በ1:59 ሲያጠናቅቅ ስኬታማ አሯሯጭ ከነበሩት አትሌቶች አንዱ እንደነበር ይታወሳል።

በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድር የአለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የሶስት ሺ ሜትር አሸናፊዋ ለምለም ኃይሉ ለአሸናፊነት ከሚጠበቁ አትሌቶች አንዷ ነች። ባለፈው የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኦሪገን ላይ በሜዳሊያ ከደመቁ አትሌቶች አንዷ የነበረችው የሃያ አንድ አመቷ ለምለም የግማሽ ማራቶን ውድድርን ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የምትሮጠው። ያም ሆኖ ባለፉት ሁለት የውድድር አመቶች በ1500እና በ3ሺ ሜትር ወጥ በሆነ አቋም ከአንድ እስከ ሶስት ባለው ደረጃ ውስጥ የማጠናቀቅ አቅም ያላት አትሌት በመሆኗ በነገው ውድድር ትኩረት ሊሰጣት ችሏል። ከለምለም በተጨማሪ የቤንጋሉሩ 10 ኪሎ ሜትር ውድድር አሸናፊዋ ኬንያዊት ኢሪን ቺፕታይ ጠንካራ ተፎካካሪ ትሆናለች ተብሎ ይጠበቃል። ይህች አትሌት ባለፈው የበርሊን ግማሽ ማራቶን 58:57 በሆነ ፈጣን ሰአት ማሸነፍ እንደቻለች ይታወቃል።

ከተዘጋጀው አጠቃላይ 268 ሺ ዶላር ሽልማት ውስጥ በሁለቱም ጾታ አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች እያንዳንዳቸው የሃያ ሰባት ሺ ዶላር ተሸላሚ እንደሚሆኑ ከውድድሩ አዘጋጆች የተገኘው መረጃ ያመለክታል። እስከ አስር ባለው ደረጃ ውስጥ የሚያጠናቅቁ አትሌቶችም እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት የሚያገኙ ይሆናል። በተጨማሪም የውድድሩን ክብረወሰን ማሻሻል የቻሉ አትሌቶች የአስራ ሁለት ሺ ዶላር ጉርሻ ተዘጋጅቶላቸዋል።


### የኢትዮጵያ መንግስት የግምጃ ቤት ሰነድ
### የጨረታ ማስታወቂያ

1. በየ 2 ሣምንት የሚደረግ የግምጃ ቤት ሰነድ ጨረታ ቁጥር 910
2. ለሽያጭ የቀረበው ሰነድ ጠቅላላ ዋጋ ብር 45,000,000,000
3. ሰነዶቹ ለገበያ የሚቀርቡበት ጥቅምት 09 ቀን 2015 ዓ/ም
4. የሰነዶቹ ዓይነትና ለጨረታ የሚቀርበው የገንዘብ ልክ፤

| የሰነዱ ዓይነት | የገንዘብ ልክ | የሚከፈልበት ጊዜ |
|---|---|---|
| የ 28 ቀን | 10,000,000,000 | ኅዳር 07 ቀን 2015 ዓ.ም |
| የ 91 ቀን | 15,000,000,000 | ጥር 10 ቀን 2015 ዓ.ም |
| የ 182 ቀን | 10,000,000,000 | ሚያዝያ 11 ቀን 2015 ዓ.ም |
| የ 364 ቀን | 10,000,000,000 | ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ.ም |

5. የእያንዳንዱ የግምጃ ቤት ሰነድ መነሻ መደብ ብር 5,000 ሆኖ ከዚህ በላይ ለሚፈልጉ የመነሻ ብዛት ይሆናል።
6. ማንኛውም ተጫራች ለሁሉም ወይም ለየትኛውም የሰነድ ዓይነት መጫረት ይችላል።
7. የጨረታ ማቅረቢያ ቅጽ ከክፍያና የሂሳብ ማወራረጃ ሥርዓት ዳይሬክቶሬት ማግኘት ይቻላል።
8. የጨረታ ማመልከቻ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን ጥቅምት 09 ቀን 2015 ዓ/ም እስከ 5:30 ሰዓት ነው፡፡
9. የጨረታ ውጤት ጥቅምት 09 ቀን 2015 ዓ/ም ይገለፃል፡፡
10. ከግምጃ ቤት ሰነድ ጋር በተያያዘ የሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍ ከማናቸውም ዓይነት ታክስ ነፃ ነው።
11. ተጨማሪ መረጃ ከክፍያና የሂሳብ ማወራረጃ ሥርዓት ዳይሬክቶሬት ወይም ከባንኩ ድረ ገጽ www.nbe.gov.et ማግኘት ይቻላል።

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**



### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም፡ አቶ መብሩክ አህመድ የተሽከርካሪው አይነት ኮሮላ የሰሌዳ ቁጥሩ 2-11491 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር 000NZE120-0112155 የሞተር ቁጥር 2N2 4006529 ሰሌዳው ጠፍቶብናል በማለት በ20/12/2014 ዓ.ም አሳውቀውናል፡፡
በመሆኑም የጠፋው እቃ (ሰሌዳ) ወድቆ ከተገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ተይዟል የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለጽ/ቤታችን ሪፖርት እንዲያደርግ፣
ባያደርግ ግን ለባለንብረቱ ሌላ ሰሌዳ የሚተካለት መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የሰበታ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የባለንብረቱ ስም ወርቅነህ አስመራ አመንሲሳ የሰሌዳ ቁጥር 3- 25584 ኦሮ የሊብሬ ቁጥር 0152720 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ27/01/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የተሽከርካሪውን የፊት ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ የፊት ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሰሜን ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን (ፍቼ)**

የባለንብረቱ ስም ግርማ ዘሪሁን የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ የሰሌዳ ቁጥር 1-47319ኦሮ የሻንሲ ቁጥር MD6M14PKOH4A53861 የሞተር ቁጥር OK4AH4072899 የሊብሬ ቁጥር 0080576
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 1- 47319 ኦሮ ጠፋብን ብለው በ15/01/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**የምዕራብ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

ንብረትነቱ ራቸው ዋሪዮ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 3-35017 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H207P03805 የሞተር ቁጥር 4HG1-050032 የሆነ ታርጋ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለፅ በምትኩ ታርጋ እንዲሰጣቸው ጠይቀውናል፡፡ በመሆኑም ታርጋ ወድቆ፣ ተሰርቆ በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃውን ትእዛዝ ይዞ እንዲቀርቡ ይህ ካልሆነ ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የቦረና ዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤት**